ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 332 ነሐሴ 2 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# አካታችነት- ለተሳካ ሀገራዊ ምክክር

**ፋንታነሽ ክንዴ**

**ዜና ትንታኔ**

መንግሥት ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ችግሮችን ለመፍታት ያለውን ዝግጁነት በተደጋጋሚ አሳውቋል። ሰላምን መርጠው የመጡትንም እጁን ዘርግቶ እየተቀበለ ነው፡፡ ከግጭት ይልቅ በውይይት የጋራ መግባባትና አንድነትን ለመፍጠርም ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ በአሁኑ ጊዜም ኮሚሽኑ በአጀንዳ ማሰባሰብ ምዕራፍ ላይ ይገኛል፡፡ ምክክር ውጤታማ እንዲሆን ከሚያደርጉ ጉዳዮች አንደኛው አካታችነት መሆኑ ተደጋግሞ ይገለጻል። ከዚህ አንጻር በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ የታጠቁ ኃይሎችንና የተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ምክክሩ እንዲመጡ ለማድረግ ምን መሠራት አለበት? በሚለው ጉዳይ የተለያዩ ሃሳቦች ይነሳሉ፡፡

የሀገር ሽማግሌው አህመድ ዘካሪያ እንደሚሉት፤ ጦርነት የትኛውንም ወገን ተጠቃሚ አያደርግም፡፡ ብዙ ጦርነቶች በርካታ የሰውና የሀብት ጉዳት ካደረሱ በኋላ ብዙ ጊዜ መቋጫው ምክክር ነው የሚሆነው፡፡

ባለፉት አራት ዓመታት በርካታ ጦርነቶች አድርገናል። በዚህም ብዙ ጉዳት አስተናግደናል። እንደ ሀገር ያሉ ችግሮችን ለመፍታትና ወደ አንድነት ለመምጣት ሀገራዊ ምክክር እየተካሄደ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የታጠቁ ኃይሎችን ወደ ምክክር ለማምጣት በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች የተጀመረውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠልና በሌሎች አካባቢዎችም ተመሳሳይ ሥራዎችን በማከናወን ችግራችንን በውይይትና በንግግር ለመፍታት መሥራት እንደሚገባ ያብራራሉ፡፡

በጦርነት የሚገኝ የመጨረሻው ውጤት ጉዳት ነው

አካታችነት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# አንባቢ ትውልድ ለማፍራት

**ቃልኪዳን አሳዬ**

**ዜና ትንታኔ**

የንባብ ባህልን በማሳደግ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ መገንባት የቻሉ ተጠቃሽ ሀገራት አሉ። ከዓመታት በፊት በWorld Culture Score Index በተደረገ ዓለም አቀፍ ጥናት አንድ

አንባቢ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ግዙፍ ተቋማትን ዒላማ ያደረጉ እኩይ ዘመቻዎች

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

**ዜና ትንታኔ**

ኢትዮጵያ በሰላሟም ሆነ በችግሯ ጊዜ ከጎኗ የሚቆም ወዳጅ አጥታ ባታውቅም በተቃራኒ ሰላሟን ለማደፍረስ እሳት የሚተፉ፣ ችግሮች ሲፈጠሩ ከዳር ቆመው የሚያራግቡ፣ ዳግመኛ እንዳትነሳም በተቻላቸው ሁሉ የሚፍጨረጨሩ የቅርብም ሆነ የሩቅ ባላንጣዎች ያጋጥሟታል፡፡ ክንዳቸውን ያፈረጠሙ ባዕዳን በተለያዩ ዘመናት ከተፈጥሮ ሀብቷ ለመቀራመት፤ በሕዝቦቿ መካከል ልዩነትን ለመዝራት ሙከራ አድርገዋል፡፡ ይህ በተለያየ መልኩ ሀገራችን ላይ የሚያደርሱት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ዛሬም እንደቀጠለ አለ፡፡

ሀገራችን ላይ እኩይ ዓላማን ያነገቡ አካላት እንደ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና መሰል ጠንካራ ተቋማቶቻችንን ኢላማ ያደረጉ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎችና ስም የማጥፋት ዘመቻዎችን እያካሄዱ ይገኛሉ፡፡

ለመሆኑ እነዚህ ተቋማት ኢላማ የመሆናቸው መንስዔ ምን ይሆን? ለጥቃት የሚተጉ አካላትስ እነማን ናቸው? ለምንስ ተቋማቱ የጥቃት ኢላማ ሆኑ? ተቋሞቻችንን ከጉዳት ለመታደግስ ምን ይጠበቅብናል?

የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁሩ ደጉ አስረስ (ዶ/ር) እንዳብራሩት፣ ተቋማቱ ኢላማ የመደረጋቸው ቀዳሚ መንስዔ ከብሔራዊ ጥቅም ጋር የተቆራኙና ከፍተኛ አትራፊ ድርጅቶች መሆናቸው ነው። ተቋማቱ ከፍተኛ ገቢን የሚያስገኙ በሀገር ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥም ሰፊ ሚና አላቸው፡፡

ከዚህ በመነሳት ተፎካካሪ ሀገራትና ሌሎችም እኩይ አላማ ያላቸው ኃይሎች የተቋማቱን ገፅታ ለማበላሸት፣ ሀገራችን ከተቋማቱ የምታገኘውን ገቢ ለማሳጣትና ብሔራዊ ጥቅሟን ለመጉዳት ሲሉ እነዚህን ተቋማት የስም ማጥፋት ዘመቻ ኢላማ ያደርጋሉ ይላሉ፡፡

በቴክኖሎጂ በመታገዝ ለጥቃት የሚደረጉ ሙከራዎች ተቋማቱ የመረጃ ሥርዓታቸው እንዲዛባና ይህንን ለመቆጣጠር ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ ሊቆጣጠሩት የማይችሉት አይነት አደጋ እንዲገጥማቸው የማድረግ ሙከራዎችም ይኖራሉ፡፡

ከተፎካካሪ ሀገራት በተለየ ሁኔታ ደግሞ ለስርቆት

ግዙፍ ተቋማትን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

Ethiopian
የኢትዮጵያ

ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም





አቶ ዳዊት ሀይሉ

# በክልሉ ከ226 ሺህ በላይ ዜጎች የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሆኑ

## - ከ70 ሺህ በላይ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ተሰራጭቷል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ከ226 ሺህ በላይ ዜጎች የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የውሃ፣ መስኖና ማዕድን ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡ ከ70 ሺህ በላይ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ መሰራጨቱ ተጠቁሟል፡፡

የቢሮ ኃላፊ አቶ ዳዊት ሀይሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤በክልሉ በ2016 በጀት ዓመት ከ226 ሺህ በላይ ዜጎች የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ በዘርፉ በተሠሩ ሥራዎች ከ226 ሺህ በላይ ዜጎች የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ያሉት አቶ ዳዊት፤ ክልሉ በቅርብ ጊዜ የተዋቀረ ቢሆንም የሕዝብ የመሠረተ ልማት ጥያቄዎችን ምላሽ ለመስጠት በትኩረት እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ለአብነትም የወልቂጤ ከተማ የንጹህ መጠጥ ውሃ እጥረትን በአጭር ጊዜ ምላሽ ለመስጠት እየተሰራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

በተለያየ ዓመት የተጀመሩ የንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ ከፍተኛ ርብርብ መደረጉን ጠቅሰው፤ በዚህም በሃድያና በከንባታ ዞኖች የተገነቡ የንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ማሳያ ናቸው ብለዋል፡፡

የንጹህ መጠጥ ውሃ የሁሉም ህብረተሰብ ጉዳይ መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ እንዲሁም የውሃ ተደራሽነትን ለማሳደግ በርካታ ስራዎች ከተለያዩ አካላት ጋር በትብብር እየተሰራ እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡

ክልሉ በተወሰኑ አካባቢዎች በአጋጠመው የፀጥታ ችግርም በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ መጠናቀቅ የነበረባቸው ስራዎች እንዳይጠናቀቁ አድርጓል ብለዋል፡፡


እንደ አቶ ዳዊት ገለጻ፤ ቢሮው ለጤና ጣቢያ እንዲሁም ለተቋማት የሚሆኑ የተለያየ መጠን ያላቸው ከ10ሺህ በላይ የሶላር ኃይል ቴክኖሎጂ ተከላና ከ70 ሺህ በላይ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ አሰራጭቷል፡፡ በዚህም በክልሉ ገጠራማ አካባቢዎች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የአማራጭ ኢነርጂ ተጠቀሚ ሆነዋል፡፡

በተጨማሪም ቢሮው ኤሌክትሪክ ባልተዳረሰባቸው የገጠር አካባቢዎች የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ላይ በትኩረት እየሰራ መሆኑን አውስተው፤ ይህም ለህብረተሰቡ የኃይል ምንጭ ሆኖ ለምግብ ማብሰያ፣ ለመብራት፣ ለተፈጥሮ ማዳበሪያና ለሌሎችም አገልግሎቶች እንደሚውል ገልጸዋል፡፡

በዘርፉ ያጋጠሙ ችግሮችን በመቅረፍ በተያዘው አዲሱ በጀት ዓመት የህብረተሰቡን ጠቃሚነት ለማሳደግ መታቀዱን አመላክተዋል፡፡

# በአንድ ጀንበር ከ150 ሚሊዮን በላይ ችግኞች ይተከላሉ

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው የአንድ ጀንበር የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ከ150 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መሪ ሥራ አስፈጻሚ ፋኖሴ መኮንን ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የፊታችን ነሀሴ 13 በሚካሄደው በዘንድሮው የአንድ ጀንበር የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ከ150 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በ75ሺህ ሄክታር መሬት ላይ በመትከል በህንድ የተያዘውን ክብረወሰን ለመስበር ዝግጅቶች ተጠናቀዋል፡፡

ባለፈው ዓመት በአንድ ጀንበር 566 ሚሊዮን ችግኝ የተተከሉ ቢሆንም በጂኦሪፈረንስ ባለመለየቱ በጊኒየስ ቡክ ላይ ሳይሰፍር ቀርቷል ያሉት አቶ ፋኖሴ፤ በዘንድሮ ዓመት ችግሩን በመቅረፍ በአንድ ጀንበር የሚተከሉት ከ150 ሚሊዮን በላይ ችግኞች በጂኦሪፈረንስ በተለየ ስፍራ ላይ የሚተከሉ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሥራ አስፈጻሚው አክለውም በጂኦሪፈረንስ ባልተለዩ ስፍራዎችም የሚተከሉ በርካታ ቁጥር ያላቸው ችግኞች እንደሚኖሩ በመግለጽ፤ ችግኞች በጂኦሪፈረንስ ተለይተው መተከላቸው ምን ያህል ችግኝ በየትኛው ስፍራ ላይ ተተከለ የሚለውን ትክክለኛ መረጃ ለማቅረብ የሚያግዝ ነው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ፋኖሴ ገለጻ፤ በጂኦሪፈረንስ ያልተለዩ ስፍራዎች ላይ ችግኝ መትከል ምን ያህል ችግኝ እንደተተከለ እንኳን በውሉ ለማወቅ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ዓመትም ከ669 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በጂኦ-ሪፈረንስ ለመለየት የታቀደ ቢሆንም እስካሁን ባለው ሁኔታ ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በጂኦ-ሪፈረንስ መለየት ተችሏል፡፡

ላለፉት አምስት ዓመታት በተከናወነው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር የተመዘገቡ መልካም ውጤቶችን አጠናክሮ ለማስቀጠል የሚታዩ ጉድለቶችን ለማረም በርካታ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን በማንሳት፤ ከችግኝ ዝግጅት ወቅት ጀምሮ የተለያዩ ስነምህዳሮችን መላመድ የሚችሉ ችግኞች መተከል እንዲችሉ ጥረቶች እየተደረጉ መሆናቸውን ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል፡፡

በዚህም ስነምህዳርን የጠበቁ ችግኞች መዘጋጀታቸው የጽድቀት መጠንን ከፍ የሚያደርግ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ፋኖሴ፤ በተጨማሪም ለከተሞች ውበት ሊያጎናጽፉ የሚችሉና ከተለያዩ መሠረተ ልማቶች ጋር የሚጣጣሙ ችግኞች ለተከላ መዘጋጀታቸውን አንስተዋል፡፡

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር የሀገር በቀል ችግኞችን በመትከል ላይ ትኩረት በመስጠት የአፈርና የውሃ ሀብቶችን ከጉዳት ለመከላከል እየተሠራ ነው፡፡ ከሚተከሉ ጠቅላላ ችግኞችም 33 በመቶ የዓባይ ተፋሰስ ላይ በመትከል የዓባይ ግድብ በደለል ከመሞላት ለመጠበቅ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡

እንደ ቀደሙት ዓመታት ሁሉ ለብዝሀ ህይወት ቅድሚያ መሰጠቱን የጠቆሙት አቶ ፋኖሴ፤ 56 በመቶ በዘርፈ ብዙ የፍራፍሬ ችግኝና 44 በመቶ ለአፈርና ውሃ ጥበቃ አገልግሎት በሚውል የደን ልማት ችግኝ ለመሸፈን በትኩረት እየተሰራ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ በዘንድሮ ዓመት እየተከናወነ በሚገኘው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ከ6 ነጥብ 5 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል በማቀድ ወደ ተግባር መግባቷ የሚታወስ ነው።

# ለኮሪያ ዘማች አርበኞችና ቤተሰቦቻቸው የሚደረገው ድጋፍ በእጥፍ አደገ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ኮሪያን ነጻ ለማውጣት ለተዋደቁ ኢትዮጵያውያን አርበኞችና ቤተሰቦቻቸው ሲደረግ የነበረው ድጋፍ በእጥፍ እንዲያድግ መደረጉን የኮሪያ አርበኞች ሚኒስትር ካንግ ጁንኪ አይ አስታወቁ።

በኢትዮጵያ ለሦስት ቀናት ይፋዊ ጉብኝት ያደረጉት ሚኒስትሯ ካንግ ጁንኪ አይ እንደተናገሩት፤ ለኮሪያ አርበኞችና ቤተሰቦቻቸው መንግሥታቸው ሲያደርግ የቆየው ድጋፍ በእጥፍ እንዲያድግ ተወስኖ ተግባራዊ መሆን ጀምሯል፡፡

በፍላጎት ላይ ተመስርቶ በኃላፊነት ስሜት እየተደረገ የሚገኘው ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመው፤ የሁለቱ ሀገራት የሁለትዮሽ የልማት ትብብር እየተጠናከረ የመጣ፣ በጋራ ተጠቃሚነት መርህ የሚመራና በተለያዩ የልማት መስኮች ላይ እየተተገበረ የሚገኝ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያውያን አርበኞች ለኮሪያውያን ቤተሰቦቻቸው የህይወት መስዋእትነት ከፍለዋል ያሉት ካንግ፤ አርበኞች እና ቤተሰቦቻቸውን የምንደግፈው ደግሞ ወድደን እና ፈቅደን፣ ኃላፊነትም ስላለብን ነው ብለዋል።

ኮሪያ በልዩ ልዩ ዘርፎች ለኢትዮጵያ የምታደርገውን ድጋፍ አጠናክራ እንደምትቀጥል አረጋግጠው፤ ኢትዮጵያ ለኮሪያ በጣም አስፈላጊ ወዳጅ ሀገር ናት ሲሉ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት እንዲከፈት፣ ዘርፉም እንዲስፋፋና በርካታ ዜጎች ሙያቸውን እና ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ



ካንግ ጁንኪ አይ

የሚደረገውን ጥረት ከመደገፍ በተጨማሪ፣ የአርበኞች ልጆች የትምህርት ዕድል አግኝተው በኮሪያ እንዲማሩ እየተደረገ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

የኮሪያ ሪፐብሊክና የኢትዮጵያ ዘላቂ የልማት አጋርነት በሕዝብ ለሕዝብና በባህል ትስስርም እየተጠናከረ መምጣቱን የጠቆሙት ሚኒስትሯ፤ ግንኙነቱ አሁን ካለው በበለጠም ተጠናክሮ እንዲቀጥል በኮሪያ በኩል የሚደረገው ጥረት እንደማይቋረጥ አረጋግጠዋል።

በጠንካራ መሠረት ላይ ተገንብቶ ከ60 ዓመታት በላይ የዘለቀው የኢትዮጵያና የኮሪያ ግንኙነት በትራንስፖርትና ኢነርጂ፣ በገጠር ልማት፣ በጤናና አካባቢ ንጽህና እንዲሁም በትምህርት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

# “ነጋዴዎች በግብርና ምርት የዋጋ ጭማሪ እያደረጉብን ነው”

- ሸማቾች

## “የዋጋ ጭማሪው ከአቅርቦት እጥረት እንጂ ከማሻሻያው ጋር አይገናኝም”

-ነጋዴዎች

**ታደሠ ብናልፈው**



አዲስ አበባ፡- መንግሥት የማክሮ የኢኮኖሚ ማሻሻያ በማድረጉና የደመወዝ መጠን ሊያድግ ነው በመባሉ የአትክልትና የፍራፍሬ ነጋዴዎች በግብርና ምርት ላይ የዋጋ ጭማሪ እያደረጉብን ነው ሲሉ ሸማቾች ገለጹ፡፡ የዋጋ ጭማሪው ከኢኮኖሚው ማሻሻያው ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከምርት አቅርቦት እጥረት ጋር የሚገናኝ ነው ሲሉ የአትክልትና የፍራፍሬ ነጋዴዎች ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑት አቶ ኪዳነማርያም ሞልቶት ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያውንና የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪን የሰሙት ነጋዴዎች በግብርና ምርቶች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እያደረጉ ነው፡፡አንድ ኪሎ ሽንኩርት በፊት ከ30 እስከ 45 ብር ነበር፤ አሁን ከ80 እስከ 90 ብር እየተሸጠ ነው ብለዋል፡፡

የግብርና ምርቶች በተለይ አትክልትና ፍራፍሬ በቀንና በሰዓት ልዩነት የዋጋ ንረት እየታየባቸው መሆኑን ገልጸው፤የዋጋ ጭማሪው በዚህ የሚቀጥል ከሆነ የሰው ልጅ በልቶ ማደር ሊያቅተው ነው፤ መንግሥት አስፈላጊውን ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ሌላዋ የአዲስ አበባ ነዋሪ ወጣት ራሄል ኦሪዎት በበኩሏ፤ በቅርቡ ተግባራዊ ከተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያና የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ ይጨመራል ከተባለ ጀምሮ በግብርና ምርቶች ላይ ተገቢ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ እየተደረገ ነው ስትል ገልጻለች፡፡

ዕሮብ ነሀሴ 1 ቀን 2016 ዓ.ም ወደ አትክልት ገበያ ጎራ ማለቷን ገልጻ፤ አንድ ኪሎ ሽንኩርት 30 ብር የነበረው አሁን 90 ብር፤ 20 ብር የነበረ ቲማቲም 35 ብር፤ ቃሪያ 120 ብር ገብቷል ስትል ተናግራለች፡፡

ስግብግብ ነጋዴዎች የተለያዩ ምርቶችን በመደበቅ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ጭማሪ እያደረጉ ነው ሲሉ አቶ አብረሃም ፍሰሃ ተናግረዋል፡፡

ነጋዴዎች የዶላር ምንዛሬ ጨምሯል በማለት ቲማቲም ከ20 ብር ወደ 35፣ ሽንኩርት ከ45 ብር ወደ 90፣ ዘይት ከ800 ብር ወደ አንድ ሺህ 500 ብር በማሳደግ እየሸጡ ነው ብለዋል፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ ነጋዴ አቶ ጂላሎ ሰሀሊ በተለያዩ የአትክልት ምርቶች ላይ የዋጋ ጭማሪ መኖሩን አምነው፤ የዋጋ ጭማሪውም መንግሥት የኢኮኖሚ ማሻሻያ ከማድረጉና የመንግሥት ደመወዝ ጭማሪ ከማድረጉ ጋር የተገናኘ ሳይሆን ክረምት በመሆኑ ምክንያት የምርት አቅርቦት እጥረት በመኖሩ ነው ይላሉ፡፡

ምርቱ በሚመረትበት አካባቢዎች የጎርፍ አደጋ በማጋጠሙና የምርት እጥረት በመፈጠሩ በባለፈው ሳምንት 40 ብር የነበረው በአሁኑ ሳምንት ሽንኩርት 80 ብር ገብቷል ብለዋል፡፡

አቅርቦትና ፍላጎትን የሚያመጣጥን ምርት አለመኖር፤ ምርቱ ከማሳ ከ75 እስከ 80 ብር መግባት፣ የሰላም እጦት፣ የትራንስፖርት ዋጋ መጨመር በግብርና ምርቶች ላይ የዋጋ ንረት እንዲከሰት አድርጓል ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ የዋጋ ንረትን ለመከላከል ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ መሥራት አለበት ብለዋል፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ ነጋዴ የሆኑት አቶ ፍቅር አየለ በበኩላቸው፤ የዋጋ ንረቱ ከመንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ፤ ከዶላር ምንዛሬና ሥርዓትና ለመንግሥት ሠራተኛ ከሚደረገው የደመወዝ ጭማሪ ጋር የተገናኘ ሳይሆን የምርት አቅርቦት እጥረት ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል፡፡

በቂ ምርት አለመኖሩ በአትክልትና በፍራፍሬ ምርቶች ላይ የዋጋ ንረት እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል፤አንድ ኪሎ ሽንኩርትም 80 ብር እየተሸጠ ነው ብለዋል፡፡

የዋጋ ጭማሪው የተከሰተው በባለፉት ሦስት ቀን ጀምሮ ነው ያሉት አቶ ፍቅር፤ ችግሩ የምርት አቅርቦት ሲኖር የሚፈታ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ ባደረጉና ምርት ባሸሹ 769 የንግድ ድርጅቶች ላይ ርምጃ ተወሰደ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያን ተከትሎ ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ ያደረጉና ምርት ያሸሹ 769 የንግድ ድርጅቶች ላይ ርምጃ መወሰዱን የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ሰውነት አየለ ለኢትጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት ፣ ቢሮው መንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ካደረገ በኋላ አጠቃላይ የንግድ ሥርዓቶች በሕግ እንዲመሩ ለማስቻል የተለያዩ ሥራዎች እየሠራ ይገኛል፡፡

በዚህም ቢሮው በንግድ ሥርዓቱ ላይ ባደረገው ቁጥጥርና ክትትል እስካሁን በሕገወጥ ንግድ አሠራር ላይ ተሰማርተው የተገኙ 769 የንግድ ድርጅቶች ላይ ርምጃ መወሰዱን ገልጸዋል።

ከእነዚህም ውስጥ 346ቱ ያለአግባብ ዋጋ በመጨመር በመያዛቸው የታሸጉ ሲሆን 423 የሚደርሱት ደግሞ ምርት በመሸሸግና ዋጋ ዝርዝር ባለመለጠፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አቶ ሰውነት ቢሮው ከማእከል እስከ ወረዳ ባለው አደረጃጀት ጠንካራ የቁጥጥር ሥራን እያሰራ መሆኑ ገልጸው፤ በአዲስ አበባ ምርት ይሸሽግባቸዋል ተብሎ የታሰቡ መጋዘኖች ላይ ፍተሻ እየተደረገ መሆኑና ሲገኝም ርምጃ እየወሰደ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል፡፡

ቢሮው በሚያደርገው ክትትል ቁጥጥሩ በአዲስ አበባ ጠበቅ ሲል፤ አንዳንድ ነጋዴዎች ምርቶቻቸውን ወደ ሸገር ሲቲ ሲያሸሹ በማስተዋሉም ከሸገር ሲቲ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ርምጃ እየተወሰደ መሆኑን አንስተዋል፡፡ በዚህም በቡራዩ ምርት እየተጠራቀመባቸው የነበሩ መጋዘኖች መታሸጋቸውን ገልጸዋል።

ዳይሬክተሩ ከዶላር መጨመር ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው እንደ ጤፍና መሰል ምርቶች ላይ ጭምር የዋጋ ጭማሪ መስተዋሉን የገለጹ ሲሆን፤ እነዚህን ምርቶች በሚያቀርቡ ነጋዴዎች ላይም ቁጥጥር እያደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

አቶ ሰውነት ቢሮው ዋጋውን ለማረጋጋት ርምጃ ከመውሰድ በተጨማሪ የከተማ አስተዳደሩ ባስገነባቸው ኮልፌ ፣ አቃቂና ለሚኩራ የገበያ ማእከላት ላይ ምርቶች በስፋት እንዲቀርቡ በማድረግ ህብረተሰቡ የገበያ አማራጭ እንዲኖረው እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም የምርት እጥረት እንዳያጋጥም ከጉምሩክ ኮሚሽን ፣ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እንዲሁም ከኦሮሚያ ክልል ጋር በመሆን አዳማ፣ ጅግጅጋና ሰመራ ላይ ቆመው የነበረ ምርት የጫኑ ተሽከርካሪዎች እንዲጓጓዙ መደረጉንና በዚህ ሳምንትም 273 ዱቄት ፣ዘይትና ሩዝ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ምርቶቻቸውን አራግፈዋል ብለዋል፡፡

አንዳንዱ ነጋዴ የዋጋ ጭማሪ እያደረገ ያለው ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ በመሆኑ ቢሮው ስለ ማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ግንዛቤ የማስረጽ ሥራን እየሠራ እንደሚገኝ አቶ ሰውነት ገልጸዋል፡፡

# የካንሰር ሕሙማን አንገብጋቢ ጉዳይ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ሐተታ**

በሀገራችን ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች አድማሳቸው እየሰፋ መጥተዋል፡፡ በርካታ ኢትዮጵያዊያን የእነዚህን በሽታዎች ተጠቂ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ በሽታዎች መካከል የካንሰር ሕመም በግንባር ቀደምትነት ይነሳል፡፡

የካንሰር ሕመም እጅግ ከፍተኛና የብዙኃኑን ህይወት የሚቀጥፍ በሽታ ከመሆኑም በላይ መድኃኒቱ እንዲሁ በቀላሉ የማይገኝ በመሆኑ ሕሙማኑን ለተጨማሪ አእምሯዊና ሥነ-ልቦናዊ ጫና ውስጥ የሚከት ነው፡፡ እንዲሁም ለኢኮኖሚያዊ ቀውስ የሚያጋልጥ ነው፡፡

ታካሚ ሕሙማንም የዚሁ ገፈት ቀማሽ ከሆኑ ሰነባብተዋል፡፡ ኢፕድ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ የካንሰር ማዕከል በመገኘት ያነጋገራቸው የካንሰር ሕሙማኑ፤ በማዕከሉ ከፍተኛ የመድኃኒት እጥረት በማጋጠሙ ለተጨማሪ እንግልት እንዲሁም መድኃኒቱን ለማቋረጥ እየተገደዱ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

አሁን ላይ አቅም ያላቸው ታማሚዎች መድኃኒቱን ከውጭ ገዝተው እየታከሙ ቢሆንም የኢኮኖሚ አቅም የሌላቸው ደግሞ መድኃኒቱን በማቋረጥ ቁጭ ብለው ሞታቸውን እየተጠባበቁ እንደሚገኙም ይገልጻሉ፡፡

ሃናን ጀላን ትባላለች፡፡ የአንጀት ካንሰር ታማሚ ስትሆን በማዕከሉ ተኝታ መታከም ከጀመረች ከሰባት ወር በላይ አስቆጥራለች፡፡ በሆስፒታሉ እየተሰጠ ያለው አገልግሎት ጥሩ ቢሆንም ከመድኃኒት ጋር ተያይዞ ያለው እንግልትና ስቃይ ከፍተኛ መሆኑን ትናገራለች፡፡

የካንሰር መድኃኒት በሆስፒታሉ ባለመኖሩ ለስድስት ዙር የሚሆን መድኃኒት ከውጭ ገዝታ እንደታከመችም ነው የምትገልጸው፡፡

እስካሁን ስድስት ዙር ወስጃለው ከዚህ በኋላ ስድስት ዙሮች ይቀረኛል የምትለው ሃናን፤ ሰባተኛውን ዙር ለመውሰድ አንዱ መድኃኒት 50 ሺህ ብር ተብያለሁ፤ ይህ ገዝቶ የመጠቀም አቅም ስለሌለኝ ለማቋረጥ ተገድጃለው ትላለች፡፡ መድኃኒቱ በሆስፒታሉ አለመኖር ታካሚውን ለተጨማሪ ስቃይና እንግልት እየዳረገው ይገኛል፡፡

በሆስፒታሉ በቆየችባቸው ሰባት ወራት በርካታ የካንሰር ሕሙማን መድኃኒቱን ከውጭ የመግዛት አቅም ስለሌላቸው ሕክምናውን አቋርጠው እንደተመለሱ የገለጸችው ታካሚዋ፤ በተጨማሪም ከአንድ ቀን በፊት መታከም እያለባቸው ሳይታከሙ ወደ ቤታቸው የተመለሱ ሴት የካንሰር ሕሙማን እንደገጠሟት አክላለች፡፡

የካንሰር በሽታ በጣም እየተባባሰ በመምጣቱ መድኃኒቱ ተገዝቶ ሆስፒታል የማይገባ ከሆነ በሀገር ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ነው ባይ ናት፡፡

የካንሰር ሕሙማኑ አቶ ዱጋሳ ሚደቅሳ እና አቶ መኮንን ጌታቸው በበኩላቸው፤ በሆስፒታሉ የካንሰር መድኃኒት ባለመኖሩ ለከፍተና ችግር ከመጋለጥ በተጨማሪ ለአንድ ዙር ሕክምና ብቻ ከ15 ሺህ ብር በላይ በማውጣት ለኢኮኖሚያዊ ችግር መጋለጣቸውን ይጠቁማሉ፡፡

መድኃኒቱ ከአስር ዙር በላይ እንደምንወስድ ተነግሮናል፡፡ ነገር ግን መድኃኒቱን የመግዛት አቅም የሌለን በመሆኑ በማቋረጥ ሞታችንን ከመጠባበቅ ውጪ ሌላ አማራጭ የለንም የሚሉት ሕሙማኑ፤ ከእነርሱ በፊት የገቡትም ከውጭ ገዝቶ መጠቀም ባለመቻላቸው አቋርጠው ወደየቤታቸው መመለሳቸውን ያብራራሉ፡፡

ከሕመማቸው በላይ የመድኃኒቱ አለመኖር ትልቅ ቀውስ እየፈጠረባቸው ስለመሆኑ ከመናገር አልሸሸጉም፡፡

ከታህሳስ ወር ጀምሮ መድኃኒቱን ከውጭ እየገዙ መሆኑን የሚጠቅሱት ታካሚዎቹ፤ መድኃኒቱ ከፍተኛ ብር የሚጠይቅና ሕመምተኛው የማይችለው በመሆኑ መንግሥት በቻለው አቅም በሆስፒታሎች መድኃኒት እንዲኖሩ ቢያደርግ የሚል ተማጽኖ አቅርበዋል፡፡

በሆስፒታሉ ከፍተኛ የካንሰር መድኃኒት እጥረት በማጋጠሙ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አልተቻለም ያሉት ደግሞ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ የካንሰር ሕክምና ማዕከል ኃላፊና የካንሰር ሕክምና ስፔሻሊስት ዶክተር መሀመድ ኢብራሂም ናቸው።

በሆስፒታሉ ባጋጠመ የመድኃኒት እጥረት ታካሚዎች ለከፍተኛ እንግልት እየተዳረጉ ነው የሚሉት ዶክተር መሀመድ፤ለካንሰር ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና 54 የመድኃኒት ዓይነቶች ውስጥ አሁን ላይ በማዕከሉ የሚገኙት ከሁለትና ሦስት የማይበልጡ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

በማዕከሉ በርካታ ታካሚዎች በመኖራቸው የሚገቡ መድኃኒቶች በአጭር ጊዜ አልቀው ታካሚው መድኃኒቱን እንዲያቋርጥና የካንሰር መድኃኒቶች በጣም ውድ በመሆናቸው ለተጨማሪ እንግልት እየዳረገው ይገኛልም ነው ያሉት፡፡

መድኃኒቱ እንደገባ በአንድ ወር ውስጥ አልቀው ዓመቱን ሙሉ እንዲሁም ለስድስትና ለሰባት ወራት የማይኖሩ የካንሰር መድኃኒቶች አሉ የሚሉት ዶክተር መሀመድ፤ከዓመት እስከ ዓመት የደረሱት ከ54 ዓይነት መድኃኒቶች ከሦስት የማይበልጡ መድኃኒቶች ብቻ መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ የመድኃኒት ግዢ ለመፈጸም ከስድስት ወር በላይ መፍጀቱ እንዲሁም ተገዝቶ የገባው መድኃኒትም በትክክል ስርጭት ያለማድረግ እጥረቱን አባብሶታል ባይ ናቸው፡፡

በሆስፒታሉ በኩል ያለውን ችግር ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በዚህ በጀት ዓመት ዳግም እንዳይከሰት ሰፊ ውይይት መደረጉን ይናገራሉ፡፡ የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒዩኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አወል ሃሰን በበኩላቸው፤ የካንሰር ሕክምና ግብዓቶች ውድ መሆናቸው እንዲሁም ሀገር ውስጥ የተመዘገበ በቂ የሆነ አቅራቢ አለመኖሩ የካንሰር መድኃኒት እጥረት አባብሶታል ይላሉ፡፡

ከ72 ሚሊዮን ብር በላይ ግምት ያላቸው የካንሰር መድኃኒቶች ቢገኙም በተቋማት መካከል ባለው የመረጃ ክፍተትና ሆስፒታሎች የማይከፍሉት ውዝፍ እዳ ምክንያት ሳይሰራጩ እንደሚቀር ይናገራሉ፡፡

መድኃኒት ተገዝቶ የሚገባበት የጊዜ ገደብ የተንዛዛ እንዳይሆን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ተሰርቷል የሚሉት አቶ አወል፤በቀጣይም 240 ቀን የሚፈጀውን ወደ 90 ቀናት ለማውረድ ትኩረት ተይዟል፡፡

ሙሉ በሙሉ ችግሩን ለመቅረፍ መድኃኒቶቹ በሀገር ውስጥ ማምረት የግድ የሚል ቢሆንም፤ ሆስፒታሎች ያለባቸውን ውዝፍ መክፈል ካልቻሉ መድኃኒት መውሰድ እንደማይችሉ ይጠቁማሉ፡፡

# አካታችነት- ለተሳካ...

### ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚሉት የሀገር ሽማግሌው፤ መንግሥትም ለውይይት እንቅፋት የሆኑ ችግሮች መቅረፍና ጥያቄዎችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት የሚቻልበትን መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፡፡ በተለይ ወጣቶችን ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ በስሜታዊነት ወደጫካ የሚገቡበትን ሁኔታ ማስቀረት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

ይህን ዕድል የውጭ ኃይሎችም ፍላጎት ሊኖርበት እንደሚችል በመረዳት፤ ለጦርነት የሚውለውን ገንዘብ፣

ጉልበትና ጊዜ ለልማት እንዲውል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ለዚህ ሁሉ ችግር እየዳረገን ያለው እልኸኝነት ነው የሚሉት የሀገር ሽማግሌው፤ ጦርነት የሚያደርሰው ጉዳት ለማንም ግልጽ የሆነ ጥፋት ያስከትላል፡፡ በመሆኑም ከእልኸኝነት ወጥተን መደማመጥና የሰላም መንገድ ቀዳሚ ምርጫ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ያብራራሉ፡፡

ፍትሐዊነት የሰፈነበት ሥርዓት መዘርጋት፣ ሁሉን አካታች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ ነው የተናገሩት፡፡ ሰው ከሥራ ወደ ችግር የሚሄድበት ሁኔታ ስለማይኖር ከችግር መውጣት የሚቻልበትን የሥራ እድል መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

አሁን ላይ ኮሚሽኑ የአጀንዳ ማሰባሰብ ሥራ እያካሄደ መሆኑን ያስታወሱት አህመድ ዘካሪያ፤ ሁሉም ወገኖች ከእልኸኝነት ወጥተው ችግሮቻችንን በዘላቂነት የምንፈታበት መንገድ መፈለግ ያስፈልጋል። ታጣቂ ኃይሎችም ችግሩ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ኃላፊነታቸውን መወጣትና ሕዝባቸው እረፍት እንዲያገኝ ማድረግ አለባቸው ነው ያሉት፡፡

ማህበራዊ ሚዲያ ላይ የምናስተላልፈው መልእክት ሊያቀራርብና ሊያግባባ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ መሥራት እንደሚገባ የሚያስታውሱት የሀገር ሽማግለው፤ ለዚህ መሳካት ደግሞ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ መገናኛ ብዙኃንና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት በትብብር መሥራት እንደሚኖርባቸው ይጠቁማሉ፡፡

የኢትጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አባል መብራቱ አለሙ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የሀገራዊ ምክክር እንዲሳካ ከሚያደርጉ ሁኔታዎች አንዱ አካታችት ነው፡፡ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ የታጠቁ ኃይሎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ኃይሎች ወደ ምክክር እንዲመጡ ጥረቶች እየተደረጉ ነው፤ አሁንም ይህን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

በአማራ ክልል የሰላም ምክር ቤት ተቋቁሞ እንቅስቃሴ መጀመሩን የሚያስታውሱት ዶክተር መብራቱ፤ ተፋላሚ ኃይሎችም በራቸውን ለሰላም ክፍት አድርገው ለንግግርና ለውይይት ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና መገናኛ ብዙኃንም የታጠቁ አካላትም ሆኑ የተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሀገር አትራፊ ወደምትሆንበት ድርድርና ምክክር እንዲመጡ መወትወት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ያስገነዝባሉ፡፡

እንደ ዶክተር መብራቱ ገለጻ፤ ሀገራዊ ምክክሩ አካታችነት ላይ ክፍተት ከተፈጠረ አጠቃላይ ሂደቱ ላይ ችግር መፍጠሩ የሚጠበቅ ነው፡፡ በመሆኑም በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ድምፅ እንዲሰማ መሥራት ይኖርብናል፡፡ የኮሚሽኑ አማካሪ ምክር ቤትም በዚህ በኩል ትልቅ ሥራ መሥራት ይኖርበታል፡፡

እንደ ባለሙያዎቹ ማብራሪያ፤ የትኛውም ጦርነት ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም፡፡ የጦርነት መጨረሻው ድርድርና ምክክር ነው፡፡

በመሆኑም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ የታጠቁ ኃይሎች እስካሁን ከጠፋው የሰው ሕይወትና የሀገር ንብረት በላይ ተጨማሪ ጉዳት ሳይደርስ ወደ ምክክር መምጣት ይኖርባቸዋል፡፡ መንግሥትም ለውይይትና ምክክር ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለበት፡፡

አካታችነት ለሀገራዊ ምክክር መሳካት ጉልህ ሚና እንዳለው በመገንዘብ የሁሉም ባለድርሻዎች ድምጽ የሚሰማበት መድረክ መሆን ይኖርበታል፡፡

ይህን ማድረግ ሲቻልም ሰላሟ በዘላቂነት የተረጋገጠ፣ ዕድገትና ልማት የዋጃት ሀገር መገንባት ቀላልና ስኬታማ እንደሚሆን ነው የሚገለጸው፡፡

# ግዙፍ ተቋማትን ዒላማ...

### ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የተደራጁ ኃይሎችም እነዚህን ተቋማት ኢላማ ያደረገ ስርቆት ለመፈጸም ጥረት የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ። ጭምር በዚህ የስርቆት ወንጀል ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተቋማት የብሔራዊ ጥቅም ማስከበሪያ እስከሆኑ ድረስ ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ ጠንክሮ መስራት እንደሚጠይቅ ያስገነዝባሉ፡፡

እስካሁንም ተቋማቱን መጠበቅ የተቻለው ጠንካራ የደህንነት ሥራ በመኖሩ መሆኑን ያነሱት ደጉ (ዶ/ር)፤ ዓለም በየጊዜው ራሱን በቴክኖሎጂ እያበለጸገ በሄደ ቁጥር ክፉ አጀንዳ ያነገቡ አካላትም በዚህ ልክ ራሳቸውን እያዘመኑ መሄዳቸው አይቀርም፡፡ የተቋማቶቻችንን ደህንነትና የሀገርን ክብር የማስጠበቅ ሥራ በየጊዜው በቴክኖሎጂ እያደገ ሊሄድ እንደሚገባ አስተያየት ይሰጣሉ፡፡

የሕዝብ አስተዳደርና ፖሊሲ ባለሙያው ገመቹ አራርሳ (ዶ/ር) እንዳሉት ደግሞ፤ የአንዲትን ሀገር ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በተጻራሪ የሚመለከቱ ሀገራት ሀገሪቱን ለመጉዳት ኢላማ የሚያደርጉት ትላልቅ ተቋማትን ነው፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የዓባይ ግድብ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ኢትዮ ቴሌኮምን የመሳሰሉ ተቋማት ደግሞ ለሀገራችን የኢኮኖሚ መሠረት ብቻ ሳይሆን የሀገር መገለጫዎቻችንም ጭምር ናቸው፡፡

በተለይም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከሠንደቅ ዓላማችን ቀጥሎ ያለ ሠንደቃችን፣ ኢትዮጵያን ከፍ አድርጎ ያሳየ፣ ለአህጉራችን አፍሪካም ኩራት የሆነ ትልቅ ተቋም ነው፡፡ ስም የማጥፋት ዘመቻው መከላከያ ኃይላችንንም ጭምር መሆኑን ያስታወሱት ገመቹ (ዶ/ር)፤ ለሀገራችን መልካም ዕይታ የሌላቸው ጠላቶች፣ የተቋማቱን መልካም ገጽታ የማጠልሸት፣ ሀገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ጎልታ እንዳትታይና መልካም ገጽታ እንዳይኖራት በእነዚህ ተቋማት ላይ ይዘምታሉ፡፡

የሀገር መለያ በሆኑ ተቋማት ላይ መዝመት በሀገር ላይ እንደመዝመት ነው፡፡ ዓላማቸው መልካም ገጽታን ማጥፋት ብቻ ሳይሆን፣ የመንግሥትን የደህንነትና የኢኮኖሚ መሠረት ማዳከም ነው፡፡ ይህ ቢሳካላቸው ደግሞ የተቋማቱን አቅም የመሸርሸር፣ የመንግሥትን የኢኮኖሚ መሠረት የማዳከምና በሕዝብና በመንግሥት መሀል ያለው ግንኙነት የማሻከር እቅዳቸው ይሳካላቸዋል። ይህ በጦር ሳይሆን የተለያየ አይነት ጫና በመፍጠር የሚደረግ ጦርነት ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡

ማኅበራዊ ድረ ገጾችን እና የተለያዩ የቴክኖሎጂ አውታሮችን በመጠቀም የሚደረገውን ዘመቻ መከላከል የሚቻለው ደግሞ የተሻለ የደህንነት አቅምን በመገንባት ነው፡፡

በቴክኖሎጂ በሚደረገው ውጊያ በተለያዩ ጊዜያት ተቋማቶቻችን በርካታ የሳይበር ጥቃት ሙከራ እንደሚደረግባቸው ያስታወሱት ገመቹ (ዶ/ር)፤ ይህ ጥረት ምንጊዜም የተሳካ እንዳይሆን የመከላከሉን ሥራ የበለጠ አጠናክሮ መቀጠል እንደሚያሻ ይናገራሉ፡፡

ጤናማ አስተሳሰብ ያለውና ሀገሩን የሚወድ ሁሉ በርካታ ዓመታትን ፈጅተው፣ ብዙ ትውልድ ዋጋ ከፍሎባቸው ዛሬ ላይ የደረሱ ተቋማቶቻችንን ላይ የሚደረጉ ዘመቻዎችን የሚቀባበሉ ዜጎች ከዚህ ድርጊት ቢቆጠቡ መልካም እንደሆነ የሚመክሩት ገመቹ (ዶ/ር)፤ ከጠላት ጋር ከመዝመት መታቀብ ብቻ ሳይሆን ዜጎች በራሳቸው ተቋማት የገጽታ ግንባታ ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉም ይጠበቃል የሚል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

እነዚህ ተቋማት የአሰራርና ሌላም ክፍተትና ችግር ቢኖርባቸው እንኳ የራሳችን ተቋማት በመሆናቸው ቅሬታችንን ስናቀርብ ለሌሎች ተጻራሪ ኃይሎች አሳልፎ በመስጠት ወይም ለእነዚህ አካላት ምቹ ሁኔታ በሚፈጥር መልኩ መሆን እንደሌለበት ይመክራሉ፡፡

የታሪክ ምሁሩ አቶ አህመድ ዘካሪያ በበኩላቸው፣ በአጠቃለይ የኢትዮጵያ ጂኦፖለቲክስና ስትራቴጂካዊ አቀማመጧ ለዚህ ሰለባ ያደርጋታል። ቀይ ባህርም ሆነ ህንድ ውቅያኖስም ለንግድ ቀጣናው ከፍተኛ መተላለፊያና የዓለምን ንግድ የሚያስተናግዱ በመሆናቸው በዚህ ምክንያት ሀገራችን ላይ ብዙ ጫና ይደረጋል።

ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ የነጻነት ተምሳሌት መሆኗ ተፃራሪ አካላት ይህንን ገፅታዋን ለማበላሸትና ግፊት እንዲበረታባት ለማድረግ ምክንያት እንደሆነ ያነሱት አቶ አህመድ፤ የእኛ መተባበር የሚፈጥረው ጥንካሬ የትኛውንም ጫና ለመመከት ወሳኝ አቅም ነው በማለት አስረድተዋል።

ምሁራኑ እንዳስረዱት፤ ከኢትዮጵያ በተፃራሪ የሚሰሩ አካላት አንድም ፖለቲካዊ ኪሳራን ለማስከተል፣ አንድም ኢኮኖሚያዊ ጫናን ለመፍጠር በሌላ በኩል ደግሞ ለዝርፊያ አላማ ጠንካራ ተቋማቶቻችንን ኢላማ ያደረጉ ጥቃቶችን ለመፈፀም ይተጋሉ፡፡

ይህ እኩይ አላማን ያነገበ ዘመቻ እውን እንዳይሆን ተቋማቶቻችንም በጥንካሬያቸው እንዲዘልቁ እንደ ሀገር በቴክኖሎጂ የበለፀገ ደህንነትን የማስጠበቅ ሥራ ለብሔራዊ ጥቅም በአንድነት የመሰለፍ አቋም ያስፈልገናል።

# አንባቢ ትውልድ...

### ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ግለሰብ በአማካይ በሳምንት ውስጥ ለንባብ በሚያውለው የጊዜ መጠን ህንድ በ10 ሰአት ከ42 ደቂቃ አንደኛ ድረጃን ስትይዝ፤ ታይላንድ በ 9 ሰአት ከ24 ደቂቃ ሁለተኛ እንዲሁም ቻይና በ 8 ሰአታት ሦስተኛ ደረጃን ይዘዋል፡፡

ጥናቱ 30 የዓለም ሀገራትን በደረጃ ሰንጠረዡ ውስጥ ያካተተ ሲሆን፤ ከአፍሪካ ሀገራት መካከል ግብጽና ደቡብ አፍሪካ እንደየቅድመ ተከተላቸው 5ኛና 14ኛ ደረጃን አግኝተዋል፡፡ ወደሀገራችን ኢትዮጵያ ስንመጣ የንባብ ባህላችን ብዙ ስራ የሚጠይቅ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ፕሬዚዳንት አበረ አዳሙ እንደሚናገሩት፤ ንባብ ማለት የእውቀት በሮች ሁሉ መክፈቻ ቁልፍ ነው፡፡ ያላንባብ ሰው ምንም ሊሆን አይችልም፡፡ 50 ሚሊዮን የማይሞላ የሕዝብ ቁጥር በነበረበት በደርግ ዘመን አንድ መጽሐፍ እስከ 130ሺህ ቅጅ ድረስ ይታተም ነበር፡፡ አሁን ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ፣ ከ50 በላይ ዩኒቨርሲቲዎች እና በርካታ የተማረ የሰው ኃይል ባለበት ወቅት ስመጥር የሆነ ደራሲ 5ሺህ ከዛም ዝቅ ሲል 500 ቅጂ መጽሐፍ ብቻ ያሳትማል። ሁኔታው በሀገራችን የንባብ ባህል አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡

ለዚህም እንደ ምክንያት ከሚነሱ በርካታ ጉዳዮች መካከል የወረቀትና የህትመት ዋጋ መናር ተጠቃሾች መሆናቸውን የሚገልጹት አቶ አበረ፤ ጉዳዩን “በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ” ያደርገዋል ይላሉ፡፡ መጽሐፍ የማሳተሚያ ዋጋው ከፍተኛ በመሆኑ ደራሲያን ረቂቅ ጽሑፎቻቸውን ይዘው ቁጭ ማለታቸውንም ይናገራሉ፡፡

ማህበራዊ ሚዲያው ተገቢ ባልሆነ መንገድ አገልግሎት ላይ መዋሉ ዜጎች እውቀት በመገበያየት ፈንታ እርስ በእርስ የሚገፋፉበት ሜዳ እንዲሆን እንዳደረገው የሚገልጹት ፕሬዚዳንቱ፤ አጋጣሚውን እንደእንቅፋት ከመውሰድ ይልቅ ቻይናን ከመሳሰሉ ሀገራት ልምድ በመቅሰም በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

ህንዳውያን የማንበብና የመመራመር ባህላቸው የዳበረ በመሆኑ ከሀገራቸው አልፈው በዓለም ሀገራት ላይ ተሰማርተው በማስተማርና በመመራመር የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ሆነዋል፡፡ በፖለቲካቸውና በማህበራዊ ኑሮአቸውም የተረጋጉ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡

አቶ አበረ፤ የንባብ ልማድ ማጣታችን በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማህበራዊ ኑሮአችን ጉዳት እያደረሰብን ነው፡፡ ተማሪዎች የሚያስመዘግቡት አነስተኛ ውጤትም የዚህ ማሳያ ነው ባይ ናቸው፡፡

“እውቀት ማጣታችን እንደባቢሎናውያን ቋንቋችንን ቀላቅሎብን ኑሯችን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ሆኖብናል” የሚሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በርካታ የሀገራችን ደራሲዎችና ጋዜጠኞች በአማረኛ፣ በእንግሊዘኛና በሌሎችም ቋንቋዎች አያሌ ጽሑፎችን የጻፉት በንባብ ራሳቸውን በማሰልጠናቸው ነው፡፡ ንባብ ባህል እንዲሆን የንባብ አብዮት መካሄድ አለበት፤ ይህንንም በመቀስቀስ ረገድ



የመገናኛ ብዙኃን ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል ሲሉ ይመክራሉ፡፡

የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የፐብሊሽንግና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ዳንኤል ሀይለ እንደሚገልጹት፤ ድርጅቱ ሀገር ውስጥ ከሚመረቱ 60 እና 80 ግራም ወረቀቶች ውጪ መቶ በመቶ በሚባል መልኩ ለተለያዩ የህትመት ሥራዎች የሚያገለግሉ ወረቀቶችን፣ ቀለምና የተለያዩ ኬሚካሎችን ከውጭ ያስገባል፡፡

በዚህም መጽሐፍ፣ መጽሔት፣ ጋዜጣ፣ ደብተር፣ ደረሰኝ፣ የሎተሪ ትኬት፣ ቼክ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሰርተፍኬትና ሌሎችንም ምስጥራዊና ምስጥራዊ ያልሆኑ ሕትመቶችን እንደሚያዘጋጅ አቶ ዳንኤል ይናገራሉ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ ድርጅቱ ከውጭ በሚያስገባቸው ለህትመት የሚያገለግሉ ግብዓቶችና የማሽነሪ መለዋወጫዎች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ የዋጋ ጭማሪ እየታየ ነው የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ በውጭ ምንዛሬ እጥረትና በሌሎች ተዛማጅ ምክንያቶች የህትመት ዋጋ ጭማሪ ሊያሳይ መቻሉን ይገልጻሉ።

እንደ አቶ ዳንኤል ገለጻ፤ የህትመት ዋጋ መጨመሩ በደንበኞች ላይ ጫና እያስከተለ ነው። በዚህም እንደ ሪፖርተር፣ አዲስ አድማስ፣ ካፒታልና ፎርቹን ያሉ የግል ጋዜጣ አሳታሚ ተቋማት የኮፒ መጠናቸውን ለመቀነስ ተገደዋል። ድርጅቱ ደንበኞቹ ከገበያ እንዳይወጡ በማሰብ ወጪዎችን በመጋራት በሌሎች ሥራዎች ለማካካስ ጥረት እያደረገ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጽሐፍት አገልግሎት የአብያተ መጽሐፍት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ያሬድ ተፈራ በበኩላቸው፤ ተቋማቸው ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 80 ዓመታት በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ በአሁኑ ወቅት በውስጡ ባሉት አምስት ቤተመጽሐፍት እየሰጠ ባለው የ24 ሰዓት አገልግሎት በቀን እስከ 2ሺህ 500 አንባብያንን እንደሚያስተናግድ ይገልጻሉ፡፡

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጽሐፍት አገልግሎት የንባብ ባህልን ለማሳደግ በትምህርት ቤቶች የንባብ ክበባትን የማቋቋምና መጽሐፍትን የመደገፍ፤ በዩኒቨርሲቲዎች የሥነጽሑፍ ምሽቶችንና በንባብ ላይ ያተኮሩ የፓናል ውይይቶችን የማዘጋጀት፣ እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለሚገኙ ታራሚዎች ቆይታቸው የተሻለ እንዲሆን የንባብ ቀናትን በጋራ የማክበርና መጽሐፍት የመደገፍ ተግባር እያከናወነ እንደሚገኝ ያነሳሉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ጎተራ፣ ጎፋ፣ ጀሞና በሌሎች የጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ከኗሪዎች ጋር በመሆን በተከፈቱ ቤተመጽሐፍቶች በርካታ ዜጎች ተጠቃሚ እየሆኑ መሆናቸውን የሚገልጹትት አቶ ያሬድ፤ በመላው ሀገሪቱ የንባብ ባህልን ለማሳደግ በተለያዩ ክልሎች በመዘዋወር በየዓመቱ ከስምንት እስከ አስር የሚደርሱ የንባብ ሳምንታትን በማዘጋጀት የመጽሐፍት ሽያጮችን የማከናወን ሥራ እየተሠራ ነው ይላሉ፡፡

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጽሐፍት አገልግሎት እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ አበረታች ቢሆንም እንደ ሀገር ያለንን የንባብ ባህል ለማሳደግ ወረቀትን በሀገር ውስጥ ከማምረት ጀምሮ ንባብን የዕለት ከዕለት ተግባር አድርጎ የሚወስድ አንባብያን ትውልድ መፍጠር የሚያስችል ሥራዎች መሥራት ያስፈልጋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለማሻሻያው ስኬት ባንኮች የሚጠበቅባቸውን ሊወጡ ይገባል!

በአንድ ሀገር የፋይናንስ ሥርዓት ውስጥ ጉልህ ድርሻ ካላቸው ተቋማት መካከል በዋነኛነት የሚጠቀሱት የንግድ ባንኮች ናቸው። ሀገራዊ የገበያ ሥርዓትን ከማዘመን እና ከማቀላጠፍ ባለፈ፤ እነዚህ ባንኮች በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖራቸው ድርሻ ከፍ ያለ ነው። ይህንኑ አስተዋጽኦአቸውን ታሳቢ በማድረግም መንግሥታት ለተቋማቱ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው ይንቀሳቀሳሉ።

ከዚህ ባሻገርም የእነዚህ ተቋማት ውድቀትም ሆነ ስኬት በአንድ ሀገር አጠቃላይ ኢኮኖሚ ላይ ሊያሳድር ከሚችለው አደጋ አንጻርም፤ ተቋማቱ ከትርፍ ባሻገር ያላቸውን ሀገራዊ ፋይዳ በሚሸከም መንገድ የዕለት ተዕለት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ የሚያስችል ጠንካራ የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓት መዘርጋት እና መቆጣጠር ትልቁ የመንግሥት ኃላፊነት ነው።

ከሁሉም በላይ ለዘርፉ የተቀመጡ ሕጎችን፣ መመሪያዎችን እና የአሠራር ሥርዓቶችን ተቀብሎ ውጤታማ በሆነ መንገድ መተግበር መቻላቸውን መቆጣጠር ፣ ችግር ሲያጋጥም ጠንካራ የእርምት እርምጃ መውሰድ፤የአንድ ሀገር የፋይናንስ ሥርዓትን እና ከዚህ የሚመነጨውን ሀገራዊ ተጠቃሚነት ማጽናት የመንግሥት የሁልጊዜ የቤት ሥራ ነው።

በተለይም የባንክ ኢንዱስትሪው ባላደገበት እና ዜጎች ስለባንክ ሥራ ተገቢውን ግንዛቤ ባልጨበጡበት ሀገራዊ ሁኔታ ውስጥ፤ ዘርፉን በጠንካራ ዲሲፕሊን የመምራቱ ጉዳይ ትኩረት የሚሻ ነው፡፡ ይኼ መሆኑም ዜጎችን ከፍ ሲልም ሀገርን ከከፋ አደጋ የመታደግ ያህል ተደርጎ የሚታይ፤ ለዘርፉ ቀጣይ እድገትም ትልቅ አቅም የመፍጠር ጅማሬ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

በእኛም ሀገር የባንክ ሥራ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የተጀመረ፤ ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም፤ ዘርፉ የዕድሜውን ያህል መጓዝ ባለመቻሉ ዛሬም በብዙ ተግዳሮቶች እየተፈተነ ይገኛል። ፈተናዎቹን በራሱ ጊዜ መሻገር አቅቶትም የመንግሥትን ጣልቃ ገብነት ሲጠይቅ ቆይቷል።

በየወቅቱ በስልጣን ላይ የነበሩ መንግሥታትም፤ ዘርፉ ራሱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳድሮ በስኬት ላይወጣ ይችላል የሚል ስጋት ስለነበራቸው፤ በርግጥም የመጡበት መንገድ ለተወዳዳሪነት የሚያነቃቃ ባለመሆኑ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የፖሊሲ ጥበቃ ተደርጎላቸው ቆይተዋል።

በእነዚህ ጊዜያትም በሀገር ውስጥ የሚገኙ ባንኮች ከአደጋ ነጻ በሆነ መንገድ በሚያካሂዷቸው የባንክ ሥራዎች በብዙ አትራፊ ቢሆኑም፤ በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባውን አስተዋጽኦ በአግባቡ መወጣት የሚያስችላቸውን ቁመና መፍጠር ሳይችሉ ዓመታት ተቆጥረዋል።

በአንዳንድ አጋጣሚዎችም የባንኩን ዘርፍ ተአማኒ እና ፍትሐዊ አገልግሎት ጥያቄ ውስጥ በሚከቱ፤ ከዚያም ባለፈ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንደሚባለው ሀገር የተቋማቱን ድጋፍ በምትፈልግባቸው አስቸጋሪ ወቅቶች የሀገርን ጥቅም በሚጎዱ ተግባራት ውስጥ ተሳታፊ ሲሆኑም ተስተውሏል።

በዚህም ሕገወጥነትን ከማበረታታት ባለፈ ጤናማ ሀገራዊ የፋይናንስ ሥርዓት እውን እንዳይሆን በራሳቸው ፈተና ከመሆን ባለፈ፤ በውስጣቸው ያደገው ሕገወጥነት አጠቃላይ በሆነው የመንግሥት የፖሊሲ ድንጋጌዎች ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሲፈጥር ቆይቷል። በዚህም መንግሥት እና ሕዝብ ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍሉ ሆነዋል።

ይህ በየወቅቱ በአግባቡ ያልተገራው የባንኮች ከሕግ እና አጠቃላይ ከሆነው የፋይናንስ ሥርዓት እና አሠራር ያፈነገጠ አሠራር፤ ዛሬም መንግሥት ተግባራዊ እያደረገ ባለው የማክሮ ፖሊሲ ማሻሻያ ላይ እንዳይደገም የሚመለከተው አካል በቁርጠኝነት ሊንቀሳቀስ ይገባል። ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በጠንካራ እርምጃ ማረም ይጠበቅበታል።

አንዳንድ ንግድ ባንኮቹ በተለይም በገበያ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የውጪ ምንዛሪ የግብይት ሥርዓት ተግባራዊ በተደረገ ማግስት፤ የገበያ ሥርዓቱ በማይፈቅደው መንገድ የዶላር ግዥ ለማካሄድ የሚያደርጉት ጥረት በተሳሳተ መንገድ ተቋማዊ ትርፋማነትን ብቻ ታሳቢ ያደረገ፤ሀገር እና ሕዝብ የሚጎዳ መሆኑን በአግባቡ ሊያጤኑት ይገባል።

በዚህ መልኩ የሚደረግ ያልተገባ ውድድር ፣ ባንኮቹ ነገ ላይ ለሚጠብቃቸው ጠንካራ ፉክክር አቅም ሊፈጥርላቸው የማይችል ፣ ራሳቸውን ለከፋ አደጋ ተጋላጭ የሚያደርጋቸው ነው። ከሁሉም በላይ አሁን ላይ ተግባራዊ እየሆነ ላለው የማክሮ ፖሊሲ ማሻሻያ በራሱ ፈተና ሊሆን የሚችል ነው።

ከዚህ አኳያ የንግድ ባንኮቹን ለመቆጣጠር ስልጣን የተሰጠው አካል፤እየተስተዋለ ባለው ችግር ዙሪያ የማያዳግም ርምጃ በመውሰድ፤ የባንኮቹ የዕለት ተዕለት አሠራር ለሕግ እና መመሪያዎች የተገዛ መሆኑን፤ በዘርፉ የሚደረጉ ውድድሮች የዘርፉን የውድድር መርሆዎች የተከተሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፤ ባንኮችም ለፖሊሲ ማሻሻያው ስኬታማነት የሚጠበቅባቸውን በኃላፊነት ሊወጡ ይገባል!

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ</u>
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

<u>ዋና አዘጋጅ</u>
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

<u>አድራሻ</u>
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

<u>የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ</u>
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

<u>የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር</u>
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

<u>የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ</u>
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

<u>የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች</u>
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

<u>የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል</u>
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

<u>የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ</u>
ስልክ - 011-1-26-43-39

<u>ማከፋፈያ</u> :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በነጻ ገበያ ስም ሕዝብ መዘረፍ የለበትም!!

ዳንኤል ዘነበ

መንግሥት ከሰሞኑ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን ይፋ አድርጓል፡፡የውሳኔውን ቁልፍ ዓላማዎችና ግቦች እንዲሁም ፋይዳ አስመልክቶ በሰጠው መግለጫም፣የውጭ ምንዛሪ መዛባትን ማስተካከልና የረጅም ጊዜ የውጭ ክፍያ ሚዛን ጉድለት ችግሮችን መፍታት፣ የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፉን በማዘመን የዋጋ ንረትን መቀነስና የዕዳ ተጋላጭነትን በመፍታት፣ የሀገር ውስጥ ገቢን በማሳደግና ሀገራዊ የልማት ፍላጎቶቻችንን በሀገር ውስጥ አቅም ለማሳካት ምቹ መደላድል መፍጠር የሚችሉ ግቦች እንዳሉት አሳውቋል፡፡

የፋይናንስ ዘርፉን አካታችነት፣ ተወዳዳሪነትና ጤናማነት ማጠናከር እንዲሁም የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል፣ የአየር ንብረት ለውጥን በመቋቋምና የምግብ ሉዓላዊነትን በማረጋገጥ፣ ጠንካራ፣ አካታችና ዘላቂ የኢኮኖሚ ሥርዓትን መገንባትም ተጨማሪ ግቦቹ መሆናቸው አመላክቷል፡፡

የፖሊሲ እርምጃዎቹ ከአጠቃላይ ሀገራዊ የረጅምና የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶቻችን ጋር ተጣጥመው እንደሚከወኑና የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅ እና የዜጎቻችንን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲተገበሩም ከፍተኛ የክትትልና የድጋፍ ማዕቀፎችን እንደሚዘረጋ እወቁልኝ ብሏል፡፡

«ለዚህም በሁሉም በሚመለከታቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና በመንግሥታዊ ተቋማት በኩል አስፈላጊ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፤ በሁሉም በሚመለከታቸው ተቋማት በኩል የፖሊሲ ትግበራ አፈጻጸም ወጥነት እንዲኖር መንግሥት ጠንካራ የፖሊሲ ማሻሻያ አመራር መኖሩን ያረጋግጣል» ብሏል፡፡ መንግሥት ያሳለፈውን ውሳኔ ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻሉን አስታውቋል።

አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያው የገበያ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባና ኢ-መደበኛ አሠራር በማስቀረት ተወዳዳሪ፣ ግልጽና አመቺ ወደሆነ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት መግባትን የሚያበረታታ እንደሆነ ነው የገለጸው። ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ፣ የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና ሌሎች የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ የወጡ በርካታ የለውጥ እርምጃዎችን ለማጠናከር እንደሚረዳም አመላክቷል።

ለፖሊሲው ስኬታማነት የሚወሰዱ እርምጃዎች ሰፊና በቂ ቅድመ ዝግጅት እንደተደረገም በሕዝቡ በተለይም አነስተኛ ገቢ ባላቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለማቃለል የአንዳንድ መሠረታዊ ሸቀጦችን ዋጋ በጊዜያዊነት ለመደጎምና እንዲሁም የገንዘብ ድጎማ ለመስጠትም መወሰኑን ገልጿል፡፡

ይሁንና በተለይ የማሻሻያው አካል የሆነውን የውጭ መገበያያ ገንዘቦችን (Foreign currency) በገበያው እንዲወሰን የማድረግ ውሳኔ በራሱ ይዞት የሚመጣው ጥሩ ነገርም ቢኖርም፤ሊያመጣ የሚችላቸው ችግሮች ስለመኖራቸው ለክርክር የሚያስቀምጥ አይሆንም። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ የዜጎች የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው ሀገሮች የገበያ ሥርዓቱ እስኪለመድና እስከሚረጋጋ ድረስ ለጊዜው የኑሮ ውድነት ማስከተሉ አይቀርም። በሀገራችን ገና ከጅምሩ የኑሮ ውድነቱን የማባባስ ምልክቶች መታየት ጀምረዋል፡፡

አሁን ላይም ወትሮም በቋፍ ያለው የግብይት ሥርዓት ለከፍተኛ ግመታ (Speculation) ተጋልጧል። በዚህም ምክንያት ምርቶችን መሰወር፣ የግብይት ሰንሰለቱን እንዲበጣጠስ ማድረግ ፣ የሸቀጦችንና አገልግሎቶችን ዋጋ ማናር እንዲሁም የግብይት ሥርዓቱን የማተረማመስ አዝማሚያዎች በመታየት ላይ ናቸው፡፡ የፖሊሲ ማሻሻያ በተደረገ ማግስት ፣ አዲስ ምርት ከውጭ ሳያስገቡ ዶላር ጨምሯል በሚል የዋጋ ጭማሪ ሲያደርጉም እየታዘብን ነው፡፡

በሕዝብ ላይ መቆመር የማይሰለቻቸው ስግብግብ ነጋዴዎች በምድርም በሰማይም ቅቡል ያልሆነውን ድርጊት ለመፈጸም ጊዜ አላባከኑም። ይህም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ያከማል የተባለውን መድኃኒት በጎሪጥ ወደ መመልከት እና 'አሁንም የዋጋ ንረት ይከሰታል' ወደሚል የስጋት ቆፈን ውስጥ እንዲገባ ምክንያት ሆኗል።

በእርግጥ መንግሥትም የፖሊሲ ማሻሻያው በህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ የኑሮ ጫናውን ለማቃለል የተለያዩ እርምጃዎችን ለመውሰድ ማቀዱን ግልጽ አድርጓል። መንግሥት ከዘራዘራቸው የማሻሻያ እርምጃዎች መካከል ለመንግሥት ሠራተኞች የኑሮ ውድነት መደጎሚያ የደመወዝ ጭማሪ ማድረግ ይጠቀሳል። የአንዳንድ መሠረታዊ ሸቀጦችን ዋጋ በጊዜያዊነት ለመደጎም መወሰኑን እንዲሁም በከተማም ሆነ በገጠር ለሚገኙ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ አነስተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች የሚደረገው የሴፍቲኔት እርዳታ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ የሚደረግ መሆኑ ገልጿል።

ይሁንና ፖሊሲው ገና ተግባራዊ ከመሆኑ በስመ ነጻ ገበያ የሚደረገውን የዋጋ ንረት ሕዝቡን እንደ ሰደድ እሳት እየለበለበው ይገኛል። የፖሊሲ ትግበራውን መንግሥት በብልሃት እንዲጓዝ በማድረግ ሊፈጠር የሚችለውን የኑሮ ውድነት ከወዲሁ መቆጣጠር ካልተቻለ ውጤቱ ከዚህም የተሻገረ እንደሚሆን የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

እንደሚታወቀው የገበያው ዘዋሪዎች ሥልጣን፣ ጉልበት፣ ሀብትና ኔትወርክ ያላቸው ናቸው፡፡ ብዙዎቹም በተደራጀ መንገድ ድጋፍና ከለላ አላቸው፡፡ የግብይት ሥርዓቱ ውስጥ ጤነኛ መስተጋብር ሊኖራቸው የሚገቡ ሦስቱ ተዋንያን ማለትም መንግሥት፣ የንግዱ ማኅበረሰብና ሸማቾች መሆን ሲገባቸው ኮንትሮባንድ ከሚነግዱና ከሚያስነግዱ እስከ ጥቁር ገበያ ዘዋሪዎችና ደላሎች ድረስ ከባድ ተግዳሮት አለ ፡፡

ፖሊሲውን ያመጣዋል የተባለው ውጤት እንዲመጣ ከታሰበ ታዲያ በትግበራ ሂደት በተለይ የግብይት ሥርዓቱን ለማስተካከል በጥናት ላይ የተመሠረተ ጠንከር ያለ ሪፎርም አስፈላጊ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሕዝቡን ከስግብግብ ነጋዴዎች ዝርፊያ መታደግ የግድ ነው፡፡ በነጻ ገበያ ስም ሕዝብ መዘረፍ የለበትም፡፡ የመንግሥት በዘመቻና በግርግር መደብሮችን በማሸግና ውክቢያ በመፍጠር ገበያው የበለጠ እንዳይተራመስ፣ ምክንያት አልባ የዋጋ ንረትን ለመከላከል የሚያስችል አሠራር መተግበርና ለዚህም ጠንካራ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ጥራት ያለው አፈጻጸም ማሳየት አለበት፡፡

በፌዴራልም ሆነ በክልልና በከተማ አስተዳደሮች ለታይታ ሳይሆን፣ ሕግና ሥርዓት የተከተለ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ወትሮም በጥቁር ገበያ ቁጥጥር ሥር ውሎ ሸማቾች ለብዝበዛ የተጋለጡበት ብልሹው የግብይት ሥርዓት፣ በዘፈቀደ በሚወሰዱ ዕርምጃዎች ሳይሆን በተጠና መንገድ መስመር እንዲይዝ ማድረግ ይገባል፡፡

በዚህም አለአግባብ በምርቶች ላይ ዋጋ የሚጨምሩና ምርት የሚያከማቹ ሕገ-ወጥ ነጋዴዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ ተጠያቂ የሚሆኑበት አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል። በተጨማሪም መንግሥት ከነጋዴው ጋር ተቀራርቦና ተመካክሮ መስራት ይኖርበታል። ህብረተሰቡ አግባብነት የሌለው የዋጋ ጭማሪ የሚያደርግና ምርት የሚያከማች ነጋዴን በመጠቆምና በማጋለጥ ተባባሪ መሆን ይኖርበታል።

በጥቅሉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያስተዋወቀው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ አካል የሆነው የውጭ ምንዛሬ የገበያ ሥርዓት ትግበራ ጥንቃቄን ይፈልጋል። የፖሊሲውን ተግባራዊነት በጨሉሌዎች ተጠልፎ መንገዱን ከሳተ ከባድ ሀገራዊ ቀውስ እንደሚያስከትል እሙን ነው ። የፖሊሲውን ተግባራዊነት በብልሃት እንዲጓዝ በማድረግ መንገዱን እንዳይስት መንግሥት ፈጣን መፍትሔ በመስጠት ረገድ መንግሥት ትልቅ ኃላፊነት አለበት። በተለይም ፖሊሲውን በህግ በመደገፍ ተጠያቂነት እንዲኖር ማድረግ አለበት።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ፖሊሲ ላይ ለባለድርሻ አካላት በተሰጠ ማብራሪያ ላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ለውጡን ባልተገባ ሕገ ወጥ መንገድ ለመጠቀም በሚፈልጉ ስግብግብ ነጋዴዎች ላይ የሕግ አስፈጻሚ አካላት እርምጃ እንዲወስዱ ኃላፊነት እንደተሰጣቸው ማንሳታቸው የሚታወስ ነው፡፡

በእርግጥም በነጻ ገበያ ስም ሕዝብ መዘረፍ የለበትም፡፡ይህ እንደመሆኑም አስፈጻሚ አካላት የፖሊሲ ለውጡን ተከትሎ በህብረተሰቡ ላይ ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ ከሚያደርጉ ነጋዴዎች ሕዝቡን በመታደግ ኃላፊነቱን ከወትሮ በተለየ መልኩ በትኩረትና በቅንጅት መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ከጉንጭ አልፋ ሙግት ይልቅ መፍትሔ ላይ ቢተኮር

ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ በገበያ እንዲመራ መወሰኑ የምጣኔ ሀብት ሊቃውንትን ለሁለት ከፍሏል። አቶ ኤርሚያስ አመልጋን ጨምሮ እነ ቴዎድሮስ መኮንን (ዶ/ር) ውሳኔውን ደግፈው ሲቆሙ እነ ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገዳ እና አቶ ክቡር ገና ደግሞ በሒደት ሊሆን ሲገባ በአንድ ጊዜ በገበያ እንዲወሰን መደረጉ ተገቢ አይደለም ይላሉ። የእነሱን እሰጥ አገባ ከተለያዩ ምንጮች ቀራርሜ የምመለስበት ሲሆን፤ አሁን ግን ውሳኔው ትክክል ነው አይደለም የሚለው ላይ ጉንጭ አልፋ ሙግት ከማድረግ ይልቅ ውሳኔው ሊያስከትለው የሚችለውን ዳፋ እንዴት መቀነስና ውጤታማ እንዲሆን፤ ምን መደረግ አለበት በሚል አቅጣጫ ማመላከት ላይ ቢተኮር ይበጃል።

ተንሳፋፊ የምንዛሪ ዋጋን ማስተዳደር በተለይ በማደግ ላይ ላሉ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገራት ፈታኝ ሊሆን ይችላል። ሆኖም የሚከተሉትን ስትራቴጂዎችን በመተግበር እንደ ሀገር የሚገጥሙ ፈተናዎችን ቀለል ማድረግ ይቻላል ብዬ አስባለሁ። ከዚህ ውጭ ውሳኔው ትክክል ነው አይደለም የሚለው ክርክር የረፈደበት ስለሆነ እሱ ላይ ችክ ማለቱ ሀገርም ሕዝብም አይጠቅምም።

**1.የገንዘብ ፖሲሲ ተለዋዋጭነት፡-** ማዕከላዊ ባንክ የወለድ ተመኖችን በማስተካከል የዋጋ ንረት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር እና ገንዘቡን ማረጋጋት ይችላል። የዋጋ ግሽበትን በማስተዳደር፣ ማዕከላዊ ባንክ የምንዛሪ ተመን ላይ ያለውን ተለዋዋጭነት ለመቀነስ ይረዳል።

**2.የውጭ ምንዛሪ ክምችት፡-** የውጭ ምንዛሪ ክምችቶችን መገንባት ከምንዛሪ ውጣ ውረድ አንፃር ቋት ሊፈጥር ይችላል። መጠባበቂያዎች ገንዘቡን ለማረጋጋት በውጭ ምንዛሪ ገበያ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

**3.የኤክስፖርት ብዝኃነት፡-** በተወሰኑ የወጪ ንግድ ላይ ያለውን ጥገኝነት መቀነስ ኢኮኖሚውን ከውጭ ድንጋጤ ለማረጋጋት ያስችላል። ሰፋ ያለ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን ማስተዋወቅ የምንዛሪ ውጣ ውረድ በገቢ ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ሊቀንስ ይችላል።

**4.የተሻሻለ የንግድ ግንኙነት፡-** ከበርካታ ሃገሮች ጋር ያለውን የንግድ ግንኙነት ማጠናከር የምንዛሪ ልውውጥ ተጋላጭነትን ይቀንሳል። የንግድ ስምምነቶች የበለጠ የተረጋጋ የኤክስፖርት ገበያ ማቅረብ ይችላሉ።

**5.የፊስካል ፖሲሲ ማስተባበሪያ፡-** የፊስካል እና የገንዘብ ፖሊሲዎችን ማስተባበር የምንዛሪ ተመን ተለዋዋጭነትን ለመቀነስ ይረዳል። ለምሳሌ፣ አስተዋይ የፊስካል አስተዳደር ማዕከላዊ ባንክ ምንዛሪውን ለማረጋጋት የሚያደርገውን ጥረት ሊደግፍ ይችላል።

**6.የፋይናንስ ገበያ ልማት፡-** የሀገር ውስጥ የፋይናንሺያል ገበያን ማዳበር የምንዛሪ ዋጋን ለመከላከል ብዙ መሣሪያዎችን ማቅረብ ይችላል። ይህ ንግዶች የምንዛሪ ተጋላጭነትን ለመቆጣጠር ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ አማራጮችን እና የወደፊት ውሎችን ያካትታል።

**7.የሕዝብ ግንዛቤ እና ትምህርት፡-** የንግድ ድርጅቶችን እና ኅብረተሰቡን ስለ ተንሳፋፊ የምንዛሪ ዋጋ አንድምታ ማስተማር እንደ መከላከያ መሣሪያዎችን መጠቀም ወይም የዋጋ አወጣጥ ስልቶችን ማስተካከል ያሉ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል።

**8.በመሠረተ ልማት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት፡-** መሠረተ ልማትን ማሻሻል ምርታማነትን እና ተወዳዳሪነትን ሊያጎለብት የሚችል ሲሆን ይህም የወጪ ንግድን በማሳደግ እና የውጭ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ገንዘቡን ለማረጋጋት ያስችላል።

**9.ክትትልና ምርምር፡-** የምንዛሪ ተመን እንቅስቃሴዎችን ለመከታተል የሚያስችል ጠንካራ ሥርዓት መዘርጋት እና ጥናትና ምርምር ማድረግ ፖሊሲ አውጪዎች ተንሳፋፊ ዋጋ ያለውን አንድምታ እንዲገነዘቡ እና ምላሽ ሰጪ ስልቶችን እንዲያዘጋጁ ያግዛል።

**10.ለተጎዱ ዘርፎች የሚደረግ ድጋፍ፡-** በምንዛሪ ተመን ተለዋዋጭነት በጣም ለተጎዱት ዘርፎች ማለትም ግብርና ወይም ማኑፋክቸሪንግ ላሉ ዘርፎች የታለመ ድጋፎችን መተግበር በኢኮኖሚው ላይ የሚደርሱትን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለመቀነስ ያስችላል። እነዚህን ስልቶች በማጣመር ሀገራችን በተንሳፋፊ የምንዛሪ ተመን ሥርዓት የሚገጥሟትን ተግዳሮቶችና ዕድሎች በተሻለ ሁኔታ መቆጣጠር ትችላለች።

በሀገር ደረጃ ታሪካዊ የሚባል የመንግሥት ውሳኔዎች ካረፈባቸው ሃገራዊ ጉዳዮች መካከል ከሰሞኑ ሥራ ላይ የዋለው በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ሥርዓትን የሚያቋቁመው ውሳኔን ሊስተካከል የሚችል አለ ለማለት ይቸግራል ይለናል "የኢኮኖሚ ባለሙያዎችን በሁለት አቋም የከፈለው የመንግሥት ውሳኔ" በሚል በሪፖርተር ላይ ባስነበበን መጣጥፉ ዳዊት ታዬ።

በዚህ ውሳኔ ዙሪያ አስተያየታቸውን ካጋሩን በተለያዩ ዘርፎች ላይ ያሉ ኢኮኖሚስቶችና የፋይናንስ ባለሙያዎች በአብዛኛው ይህንን ሃሳብ በመጋራት ውሳኔውን በታሪካዊነት ይፈርጁታል። መንግሥት በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ሥርዓት መወሰኑን ሲሰሙ፣ ‹‹ኢትዮጵያ በታሪኳ ትልቁንና አስፈላጊውን ውሳኔ እንደወሰነች ተሰምቶኛል›› ያሉት የፋይናንስ ባለሙያው አቶ አሰግድ ገብረመድኅን ናቸው። አቶ አሰግድ፣ ይህ እንዲመጣ ብዙ ታግለው የነበረ መሆኑን በመግለጽ ውሳኔው ትልቅ ዕርምጃ ብለውታል።

መንግሥት የውጭ ምንዛሪ ገበያን በነፃ ገበያ ሥርዓት እንዲገበያይ ያሳለፈው ውሳኔ ይፋ ከመደረጉ አምስት ቀን ቀደም ብሎ የኅብረት ባንክ 25ኛ ዓመቱ ክብረ በዓል አስመልክቶ በተዘጋጀ የፓናል ውይይት ላይም ዓለማየሁ (ፕሮፌሰር) ኢትዮጵያ እያካሄደች ባለችው የገንዘብ ፖሊሲ ለውጥ የውጭ ምንዛሪን በአንድ ጊዜ በገበያ ዋጋ የምትወስን ከሆነ አደጋ ይኖረዋል ብለው ነበር። የውጭ ምንዛሪ ለውጡን ቀስ በቀስ እያሳደገች መምጣት አለባት እንጂ በአንዴ ገበያውን መክፈቷ ተገቢ ያለመሆኑን ለማስረዳት ሞክረዋል።

ይህንን ከተናገሩ ከቀናት በኋላ መንግሥት በገበያ ላይ የተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ግብይት መወሰኑን ይፋ ያደረገ ሲሆን፣ ፕሮፌሰሩም ውሳኔውን በመቃወም አቋማቸውን በተለያዩ መገናኛ መንገዶች ሲገልጹ ተስተውለዋል፣ ተደምጠዋል። አሁን ባለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚና አጠቃላይ ሁኔታ አንጻር ይህ ውሳኔ ሊያስከትል ይችላል ያሉትንም ችግር የተለያዩ ጥናቶችን በማጣቀስ አስረድተዋል።

በዚሁ የኅብረት ባንክ መድረክ ላይ የተገኙት ሌላው የኢኮኖሚ ባለሙያ ቴዎድሮስ መኮንን (ዶ/ር) የኢትዮጵያ ያለባትን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍና ኢኮኖሚውን ለማነቃቃት የውጭ ምንዛሪ ገበያውን በነፃ ገበያ ማካሄድ የተሻለው አማራጭ መሆኑን በመግለጽ ከቀድሞ አስተማሪያቸው ዓለማየሁ (ፕሮፌሰር) ለየት ያለ ምልከታቸውን አንፀባርቀዋል።

በዚሁ ጉዳይ ላይ ለሪፖርተር እንደገለጹትም፤ ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ሁኔታ ከችግሯ ለመውጣት የምትወስዳቸው ማናቸውም ዕርምጃዎች ሕመም ያላቸው መሆኑን ነው። ‹‹ሕመም የሌለው መውጫ የለንም። የሚሉት ቴዎድሮስ ሁሉም መውጫዎች ሕመም አላቸው። ነገር ግን አነስተኛ ሕመም የሚያስከትለው አማራጭ መወሰድ አለበት ብለዋል። አሁን መንግሥት የወሰደውን ዕርምጃም የተሻለ ነው ብለውታል።

‹‹ከዚህ ቀደም ብዙ ብር አትመን ብራችንን አርክሰነዋል። በጦርነቱ መንግሥት ብዙ ብር ነው ያተመው። ብር ብዙ ሲታተም ደግሞ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ብርህ ይረክሳል። ስለዚህ ዶላር መወደዱን ልናስቀረው አንችልም። ትክክለኛው ዋጋ 57 ብር አይደለም። ብር ብዙ ስላተምነው ረክሷል። ጥፋት ነበር ማለት ነው። ጥፋት ካጠፋህ የዚያ ነገር ኮንስኪዌንስ ይኖረዋል።

> ተንሳፋፊ የምንዛሪ ዋጋን ማስተዳደር በተለይ በማደግ ላይ ላሉ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገራት ፈታኝ ሊሆን ይችላል። ሆኖም የሚከተሉትን ስትራቴጂዎችን በመተግበር እንደ ሀገር የሚገጥሙ ፈተናዎችን ቀለል ማድረግ ይቻላል

አሁን ኮንስኪዌንሱን ዘሊስት መንገድ የትኛው ነው ብሎ መወሰንን ስለሚጠይቅ አነስተኛ ሕመም ያለውን መርጧል። ስለዚህ መንግሥት ችግሩን አምኖ አሁን የወሰደው ዕርምጃ አነስተኛ ሕመም ያለውና መደረግ የነበረበት ነው›› ሲሉ የኢኮኖሚ ባለሙያ ቴዎድሮስ (ዶ/ር) አስረድተዋል።

ኢኮኖሚውን የማያነቃቃ ውሳኔ ቢሆንም፣ በምንዛሪ ለውጥ ነገሮች ሁሉ ይስተካከላሉ ማለት እንዳልሆነ፣ ጎን ለጎን ብዙ ሊሠሩ የሚገባቸው ነገሮች እንዳሉ ተናግረዋል። በመሆኑም ውሳኔው ሕመም ቢኖረውም መንግሥት ከዚህ ውሳኔ ላይ መድረሱ ትልቅ ዕርምጃ ነው ብለዋል። ነገሮች እስኪስተካከሉ እየተባለ እስካሁን መዘግየቱ የበለጠ ዋጋ እያስከፈለ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

የሰሞኑን የመንግሥት ውሳኔ እንደሚደግፉት የገለጹት የፋይናንስ ባለሙያ አቶ አሰግድ ገብረመድኅን፣ ይህ የመንግሥት ውሳኔ አስደንጋጭ ሊሆን አይችልም ይላሉ። አቶ አሰግድ አክለውም ‹‹የውጭ ምንዛሪ በገበያ ዋጋ ይወሰን በሚል ስንጮህና ስንታገል የነበረ በመሆኑ፣ ዛሬ ይህ ዕውን ሲሆን በመልካም ልንቀበለው የሚገባና በአግባቡ ሥራ ላይ የሚውል ከሆነ ጠቃሚ መሆኑን ማመን ያስፈልጋል፤›› ብለዋል።

ነፃ የኢኮኖሚ ሥርዓትን በሚከተል ሀገር ውስጥ እንቅስቃሴዎች በነፃነት መካሄድ እንደሚኖርባቸው የሚናገሩት አቶ አሰግድ፣ የምርት እንቅስቃሴ መስተጓጎል እንደሌለበት፣ ምርት ማደግ እንዳለበት ነገር ግን ይህ እንዳይሆን እንቅፋቶች በየቦታው መኖራቸውን ጠቁመዋል። ‹‹ግጭቶች አሉ፣ ጦርነቶች አሉ። ስለዚህ የሠላም ማጣታችን ችግር ካልሆነ በስተቀር ኢትዮጵያ በዚህ ሰዓት ከዶላር የምታገኘውን ጥቅም ይዛ እንዲህ ያለውን ነገር ማስተካከል እንደሚኖርባት መታመን አለበት፤›› ብለዋል።

እንደ ዓለማየሁ (ፕሮፌሰር) ያሉ ኢኮኖሚስቶች ሥጋት በአሁኑ ወቅት በሃገሪቱ በቂ ምርትና አቅርቦት የለም፣ የኢትዮጵያ ብር የመግዛት አቅም ተሸርሽሯል፣ በዚህም ምክንያት ማኅበረሰቡ ገንዘብ ባንክ ከማስቀመጥ ይቆጠባል የሚሉት ይገኙበታል። ከዚህም ሌላ ቁጠባም ስለማይኖር ባንኮች ሊያበድሩ አይችሉም፣ ይህ ከሆነ ደግሞ ባንኮችም አይኖሩም የሚለውና የመሳሰሉትን ይዘረዝራሉ። በተጨማሪም፣ ከፀጥታ ጋር የተያያዙ ችግሮችም ይጠቀሳሉ። አሁንም ባለው ሁኔታ የመንግሥት ውሳኔ ከሥጋቱ ይልቅ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ ይህ ሊሆን ይችላል በሚል ሥጋት ውሳኔውን መቃወም ተገቢ አለመሆኑንም አቶ አሰግድ ጠቁመዋል።

ከለውጡ ወዲህ መንግሥት ከወሰዳቸው ትልልቅ ዕርምጃዎችና ውሳኔዎች መካከል በውጭ ምንዛሪ አሠራር ላይ የወሰደው ውሳኔ ድፍረት የተሞላበት ስለመሆኑ የገለጹት የኢትዮጵያ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አበባው ግርማ ደግሞ ውሳኔው ለአምራች ዘርፉ ይጠቅማል ይላሉ። እርሳቸውም የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ ገበያ በነፃ ገበያ መወሰን እንደሚኖርበት በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የተሰማሩ ነጋዴዎች ሲገልጹ እንደነበር ገልጸዋል። በተለይ ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አንጻር ሊኖረው የሚችለው ጠቀሜታ ቀላል እንደማይሆንም እርግጠኛ ነኝ ብለዋል። እሳቸው በሚመሩት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከውጭ ምንዛሪ እጥረት ጋር ተያይዞ በርካታ ችግሮች እንደነበሩ በመግለጽ የሰሞኑ ውሳኔ ግን ከዚያ ችግር ሊያላቅቃቸው የሚችልበት ዕድል ስለመኖሩ ጠቅሰዋል።

ለምሳሌ አንድ ፋብሪካ ለምርቱ ከሚያስፈልገው ጥሬ ዕቃ አብዛኛውን አግኝቶ አምስት በመቶ የምትሆነዋን ጥሬ ዕቃ ለመሙላት የሚያስፈልግ ጥሬ ዕቃ የሚሆን የውጭ ምንዛሪ በማጣት ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት አንዳንዴም ከዚያ በላይ ወረፋ የሚጠብቅበት ሁኔታ አለ። ምርቱን ለማምረት የምትጎለዋን ጥቂት ጥሬ ዕቃ ለመግዛት የሚፈለገው የውጭ ምንዛሪ እስኪገኝ ፋብሪካዎች ለወራት የሚቆሙበት አጋጣሚዎች በተደጋጋሚ ይከሰት እንደነበር የገለጹት አቶ አበባየሁ፤ ይህ ችግር ሁሉ ይፈጠር የነበረው የውጭ ገበያ በነፃ ገበያ ሥርዓት ሲመራ ስላልነበር ነው ይላሉ።

ከውጭ ምንዛሪ አሠራር ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም የተለየች ስለመሆኗ በሥራቸው አጋጣሚ በተለያዩ አገሮች ባደጉት ጉብኝት መታዘባቸውን ያስታወሱት አቶ አበባየሁ የውጭ ምንዛሪ በትንንሽ ኪዎስኮች ጭምር ሲመነዘርና በእነዚያ ሃገሮች የውጭ ምንዛሪ እንደ ችግር አይታይም። ይህም የሆነበት አንዱና ትልቁ ምክንያት የውጭ ምንዛሪ በገበያ ዋጋ እንዲገበያይ ወስነው መሥራታቸው መሆኑን ይጠቅሳሉ። ስለዚህ በየሃገሩ እናይና እንመኝ የነበረውን ነገር እዚህ ለመተግበር መንግሥት የወሰነው ውሳኔ ለእርሳቸውና ለመሰሎቻቸው መልካም ዕድል ይዞ የመጣ ሃገራዊ ኢኮኖሚው ላይም ትልቅ ለውጥ የሚያመጣ እንደሆነ ጭምር ገልጸዋል። እንዲህ ያለው የመንግሥት ውሳኔ ጥቅሙ የላቀ ስለመሆኑ የሚገልጹት አቶ አሰግድ ደግሞ፤ የዚህ ውሳኔ አንዱ ማሳያ ሊብራላይዝድ የሆነ ኢኮኖሚ መፈጠሩን በተጨባጭ የሚያሳይ መሆኑ ነው ይላሉ።

በተለይ የውጭ ባንኮችና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ከመግባታቸው በፊት መንግሥት ይህንን ዕርምጃ መውሰዱ ተገቢና ትክክልም ብለው ያምናሉ። እሳቸውም ይህ እንዲሆን ለዓመታት መታገላቸውን የገለጹት አቶ አሰግድ ዕርምጃው የኢትዮጵያን የንግድ ባሕሪ የሚቀይርና የሚያሳልጥ ነው። በአካባቢው የሚኖራትን የኢኮኖሚ የበላይነት እንዲይዝ የሚያደርግ ነው፤ በተለይ የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች በ2030 ሪጅናል ኢንተግሬሽን የጋራ ገበያ የሚፈጥሩ በመሆኑ በዚህ ገበያ የማይተካ ሚና የሚኖረው አንዱ መገዥ ዶላር ከመሆኑ አንፃር ኢትዮጵያ ገበያ መር የውጭ ምንዛሪ ይፋ ማድረጓ በዚህ ቀጣና ያለውን ገበያ ለመምራት ጭምር ያግዛታል። ከዚህም ሌላ የጠነከረ ኢኮኖሚ እንዲኖራት ደግሞ በዓለም ላይ ያሉ ጠንካራ ከረንሲዎችን መጠቀም በመሆኑ ኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪን ፍላጎትና አቅርቦት ላይ በተመሠረተ የገበያ ሥርዓት መመራት ተወዳዳሪ ገበያ እንዲፈጠር የሚያግዝና በተሻለ ወደ ዓለም አቀፍ ገበያ ለመግባት የሚያስችል ነው ብለዋል።

ሻሎም ! አሜን።

# ወቅታዊ

# ‹‹ክረምቱ እስከሚጠናቀቅ እስከ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሜካናይዜሽን ለማረስ እየሠራን ነው››



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

**አቶ ኢሳያስ ለማ**
**በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት ዘርፍ ሥራ አስፈፃሚ**

**ማሕሌት አብዱል**

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሚባለውንና አብዛኛው የሃገሪቱ ሕዝብ የሚተዳደርበትን የግብርና ዘርፉን ለማሳደግ መንግሥት የተለያዩ የልማት መርሐ-ግብሮችን ቀርፆ በመሥራት ላይ ይገኛል። በተለይም የተበጣጠሰ መሬትን መሠረት ያደረገውን ኋላቀር የአስተራረስ ሂደትን በኩታ ገጠም (ክላስተር) እርሻ ሥርዓት በመለወጥ፤ በተቀናጀ መልኩ የቴክኖሎጂና ሜካናይዜሽን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተጀመረው ጥረት አበረታች ውጤት እያስገኘ ነው።

በተለይም ካለፉት ስድስት ዓመታት ወዲህ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ላይ የተጀመረው ሥራ እንደሃገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ሁነኛ አቅም እየፈጠረ ከመሆኑም ባሻገር ለሌሎች የአፍሪካ ሃገራት አብነት መሆን እየቻለም ጭምር ነው። በዘንድሮ ክረምት ያለውን የዝናብ ወቅት በመጠቀም አርሶአደሩን በክላስተር የማደራጀትና የሚታረሱ መሬቶችን የማስፋት ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቅርቡ ማስገንዘባቸው ይታወሳል። ከዚህ አንፃር ምን እየተሠራ ነው? ስንል በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት ዘርፍ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ኢሳያስ ለማን ጠይቀናል። እንደሚከተለው ይቀርባል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደሃገር የኩታ ገጠም (የክላስተር) እርሻ መስፋፋት ያለውን ፋይዳ ያብራሩልንና ውይይታችን እንጀምር?**

**አቶ ኢሳያስ፡-** ኩታ ገጠም እንደአጠቃላይ ስንመለከተው ከቃሉ ስንጀምር (Agricultural Mechanization Cluster ) የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል ለመተካት የመጣ ነው። የዚህ አደረጃጀት ዋና ዓላማ ሲባል ማሳቸው በድንበር የሚዋሰኑ አርሶአደሮች በጋራ አቅደው በጋራ እንዲሠሩ ማድረግ ነው። ይህ አርሶአደሩን በጋራ እንዲሠራ የማድረግ ስትራቴጂ በተለያየ ጊዜ ተሞክሮ ነበር፤ ሆኖም በሚፈለገው ደረጃ ውጤት አላመጣም። ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ግን ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን ፓይለት በማድረግ የተጀመረው ሥራ አበረታች የሚባል ለውጥ እያመጣ ነው። የክላስተር አደረጃጀት ዋና ዓላማው አርሶአደር የመወሰንና የመደራደር አቅምን ለማጎልበት፤ እንዲሁም ደግሞ በጋራ ሠርቶ በጋራ የማደግ እሴቶችን ከፍ ማድረግ ነው።

ይህም ሲባል ለምሳሌ በተናጠል በሚካሄደው የእርሻ አሠራር አንድ አርሶአደር ዘር ቢፈልግና ቢጠይቅ ለማግኘት አዳጋች ይሆንበታል። ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እንደሚባለው ሁሉ በጋራ ሆነው ቢጠይቁ ግን ይበልጥ ተደማጭ ይሆናሉ፤ ድጋፍ ለሚያደርገው መንግሥትም ሆነ አቅራቢ ድርጅቶች ቀላል ስለሚሆን አርሶአደሩ ማንኛውንም ግብዓት ለማግኘት አይቸገርም። ከዚህ ባሻገር ግን በጋራ መሥራቱ አንዱ ያለው መልካም ተሞክሮ ለሌላው መነሳሳት ምክንያት እንዲሆን ያደርጋል። ቡድን ስለሆኑ በጋራ የሚያቅዱበት፣ የሚያርሱበት፣ ያመረቱትን ደግሞ የሚሰበስቡበት ሁኔታ መፍጠር ያስችላል። እንደአጠቃላይ ከእቅድ ጀምሮ እስከሽያጭ ድረስ ያሉትን ሥራዎች በጋራ የሚሠራበትና የአርሶአደሩን አቅም ማጎልበት የሚያስችል ሥርዓት ነው።

ይህ ሲባል ግን መሬት ማዋሓድ ማለት አይደለም፤ ወይም የቀድሞውን ድንበር አጥፍቶ አንድ ላይ መቀላቀል ማለት አይደለም፤ ይልቁንም ሁሉም የየራሱን መሬት ይዞ በጋራ ያርሳል፤ ተመሳሳይ ሰብል ይዘራል፤ አንድ ላይ ሆኖ ያጭዳል። ገበያም በጋራ ሆነው ነው የሚደራደሩት። የሚደራጁትም ሆነ የሚዘሩትን ሰብል የሚመርጡት ራሳቸው ናቸው። በግዳጅ አናደራጅም፤ የማይፈልጉትንም ዘር እንዲዘሩ አናደርግም። ግን ደግሞ ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ሰብሎች እንዲመርጡ እናደርጋለን፤ ይህ ሲሆን ደግሞ መንግሥት የሚደግፋቸው ሰብሎች ላይ ቢያተኩሩ ምክረ ሃሳብ እንሰጣቸዋለን።

በነገራችን ላይ በክላስተር አሠራር የመጀመሪያ የምንመርጠው ወረዳዎችን ነው፤ ከወረዳው ደግሞ የተወሰኑ ቀበሌዎች ውስጥ ያሉ የአርሶ አደር ቡድኖችን ይለያሉ። በእነዚህ አደረጃጀቶች ከ15 እስከ 30 የሚሆኑና የጋራ መሬታቸው ከ15 ሄክታር ያላነሰ አርሶአደሮችን በጋራ የሚሠሩበትን ሂደት ነው። በአንድ ወረዳ ላይ ኩታ ገጠሞች አስርም 20 ሊሆኑ ይችላሉ። በኩታ ገጠም ውስጥ ጠንካራም ሆነ ደካማ ገበሬ ይኖራል፤ ሆኖም አንዱ ሌላውን እያነቃና እየደገፈ በጋራ የሚሠራበትና የሚያድግበት ሥርዓት ነው።

እንደአጠቃላይ በኩታ ገጠም የምንሠራው እርሻ የሰብል ምርጫቸውን ወስደን ድጋፍ እናደርግላቸዋለን። በተቻለ መጠን የቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን ማሳደግ ትልቁ ሥራ ነው። ይህንን ስናድርግ ከፍተኛ አምራች ለሆኑ አካባቢዎች ቅድሚያ እንሰጣለን። ምክንያቱም ክላስተር የማይሆኑ ቦታዎች ደግሞ አሉ። ለምሳሌ ለዓመት የሚሆን ቀለብ ማምረት የማይችሉና በሴፍትኔት የሚረዱ አካባቢዎች አሉ። እነዚህ አካባቢዎች ላይ ከክላስተር ይልቅ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም ነው የሚያሻው። ክላስተር መሆን የሚችሉት አምራች አካባቢዎችና ቢደገፉ ምርት መስጠት የሚችሉ ናቸው። በዚህ ሂደት አርሶአደሩ ዘርም ራሱ ነው የሚገዛው፤ ምርቱንም የሚሸጠው በራሱ ነው። ግን አንድ ላይ ሆነው ምርት ካመረቱ በኋላ የመደራደር አቅማቸውን ያሳድጋል።

**አዲስ ዘመን፡- እስካሁን ባለው ሂደት አብዛኛው አርሶአደር የተበጣጠሰ መሬት ላይ በሚሠራበት ሁኔታ እንደሃገር ምን አሳጥቶናል? ግብርናው ለኢኮኖሚው እድገት የበኩሉን ሚና እንዳይጫወት የነበረው አሉታዊ አስተዋፅዖ እንዴት ይገለፃል?**

**አቶ ኢሳያስ፡-** አንደኛ ነገር በኢትዮጵያ የመሬት ስሪት መሠረት አብዛኛው መሬት የተያዘው በአርሶአደር ነው። 80 በመቶ የሚሆነው ኅብረተሰባችን የሚኖረው በገጠር ነው። ይህ ሕዝብ ደግሞ ዋነኛ መተዳደሪያው እርሻ ነው። የተለያዩ ሃገሮች የተለያየ ተሞክሮ አላቸው። ለምሳሌ መሬት ለአርሶአደር በመሸጥ የተወሰኑ ሰፋፊ ባለሃብቶችን በመፍጠር ሃገራዊ ምርት ፍላጎትን ለማሳካት ጥረት የሚያደርጉ አሉ። ብዙ ሃገሮች ላይ ይህ አይነቱ አሠራር የተለመደ ነው።

እኛ ሃገር አርሶአደሩ ከመሬት ጋር በተያያዘ ካለው አመለካከት አኳያና ዘርፉ የሚይዘው ሰፊ የሰው ኃይል አንፃር አዋጭነቱ እምብዛም ነው። በነገራችን ላይ ‹‹ጥቂት ሰዎች ናቸው ገበሬ መሆን ያለባቸው›› የሚለው አስተሳሰብ የኢንዱስትሪ አብዮቱን ተከትሎ የመጣ ሲሆን፤ አርሶአደሩ መሬቱን ለቆ ወደ ከተማ የገባበት፤ ብዙዎች ሰዎች በኢንዱስትሪ የሚቀጠሩበት፤ ጥቂት ደግሞ ሰፊ እርሻ ይዘው የሃገሪቱን የምግብ ፍላጎት፤ ኤክስፖርት፣ የተለያዩ አቅም ሊሆኑ የሚችሉበት ብዙ ያደጉ ሃገሮች አሉ።

እንዳልኩሽ ግን እኛ ሃገር ደግሞ አርሶአደሩ መሬት የራሱ በማድረግ ማልማት ነው የሚፈልገው። በመሆኑም መንግሥትም አርሶአደሩ ባለበት በባለሀብት የሚሠራውን ሥራ መሥራት ይቻላል የሚል እምነት አለው። በክላስተር አርሶአደሩን በማደራጀት እስከ ትልቅ አክሲዮን ወይም ድርጅት ድረስ ማሳደግ ይቻላል። ለዚያ ደግሞ ስድስት ደረጃዎችን ማለፍ ይጠይቃል። የመጀመሪያው ነገር ተስማምቶ መሥራት፣ በመቀጠል በጋራ ማቀድና በጋራ መሥራት ነው። ቀጥሎ መሬታቸውን ማዋሓድና ኢንተርፕራይዝ ማድረግ ይችላሉ። በዚህ ሂደት 100 ሄክታር ሊሆን ይችላል፤ እነዚያ ሰዎች ድርጅት አቋቁመው፤ ድርጅታቸው ሕጋዊ ሰውነት አግኝቶ ለሌላ ሰው ሳይሸጡ የሚፈለገውን ግብ ማሳካት ይችላሉ።

ለዚህም ነው እኛም ከዚህ መነሻ ነው በክላስተር የሚፈለገውን ግብ ማሳካት ይቻላል ብለን የጀመርነው። በመሠረቱ የክላስተር አደረጃጀት ለድጋፍም ይመቻል። አስቀድሜ እንደገለፅኩልሽ መንግሥት እያንዳንዱን አርሶአደር ከሚረዳ ክላስተሩን ቢረዳ ይቀለዋል። ነጋዴውም የተመረተውን ምርት በአንድ ጊዜና ቦታ ቢገዛ የተሻለ ይመርጠዋል። በዚህ በክላስተር አሠራር ብዙ ሃገሮች አድገዋል። ጎረቤታችን ኬኒያ ብዙ ሥራዎችን የሠራችው በክላስተር አደረጃጀት ነው። እነብራዚልና ሌሎችም ሃገራት የልማት ኮሪደር እና የተለያየ ስም ሰጥተውት በተመሳሳይ መንገድ ሠርተው ምርታማነታቸውን ማሳደግ ችለዋል።

እንደሚታወቀው የክላስተር አሠራር ምርትን መሠረት ያደረገ አሠራር ነው፤ መንግሥትም ይህን ሥራ ሲጀምር መጀመሪያ በስድስት ሰብሎች፣ በ300 ፓይለት ወረዳዎች ላይ ነበር። አሁን ግን በአብዛኛው የሃገሪቱ ክፍል ላይ እየሄድንበት ነው። በወቅቱ 1ነጥብ 5ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የተጀመረ ሲሆን አሁን 12 ሚሊዮን ሄክታር ደርሰናል። እንዳነሳሽው ከዚህ ቀደም እንደነበረው በተበጣጠሰ መሬት ላይ የሚሠራው የግብርና ሥራ ምርታማነትን ለማሳደግም ሆነ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት ያዳግታል። መንግሥትም ቢሆን 18 ሚሊዮን አርሶ አደርን በተናጠል ከመደገፍ ይልቅ በክላስተር ቢደግፍ የበለጠ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ይችላል። እንዳጠቃላይ በተናጠል ወይም በ0 ነጥብ 5 ሄክታር ላይ የሚታረሰው እርሻ ሃገር እንደማይቀይር ታምኖበትነው ወደዚህ ሥራ የተገባው። በመሠረቱ አርሶአደሩም ቢሆን በጋራ መሥራቱ በተናጠል ከሚያደርገው ጥረት የበለጠ ተጠቃሚ ያደርገዋል፤ የመደራደር አቅሙም ይጎለብታል።

**አዲስ ዘመን፡- መደራደር ሲሉ ምን ማለትዎ ነው?**

**አቶ ኢሳያስ፡-** መደራደር ሲባል ግብይትን ብቻ አይደለም። አስቀድሜ እንደገለፅኩልሽ ግብዓትንም ለመጠየቅ ከግል ይልቅ በጋራ ሲሆን የበለጠ ተቀባይነት አለው። ይህ ደግሞ በተመጣጣኝ ዋጋ ማሽኖችንና ቴክኖሎጂዎችንም ማግኘት ይችላል።አቅማቸውን ካሳደጉ ደግሞ እነዚህን አገልግሎቶች በጋራ መግዛትም ይችላሉ። ወደ ኢንተርፕራይዝ ሲያድጉ የዘር አምራች ድርጅት ይፈጥራሉ። ሃገሪቱም ቢሆን ተመሳሳይ ምርት ከአንድ ቦታ ታገኛለች። ጥራቱን የጠበቀ በተለይ ለፋብሪካ ግብዓት የሚሆን ግብዓት ከማግኘት አንፃር ክላስተር ትልቅ ጠቀሜታ አለው። በተበጣጣሰ መሬት ላይ ግን ሲሆን የተለያዩ ዝርያ ያላቸው የተለያዩ ሰብሎች የሚመረቱ በመሆኑ ውጤታማ መሆን አይቻልም። ለግብይት አይመችም፤ ለኢንዱስትሪውም በቂና ተመሳሳይ ምርት ለማቅረብ አይቻልም። የእኛ ሃገር ተሞክሮ

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# ‹‹ክረምቱ እስከሚጠናቀቅ እስከ...

ከገጽ 7 የዞረ

የሚያሳየውም ለፋብሪካ የሚቀርበው የምርት መጠን ለዓመት የሚበቃ አይደለም። እናም ምርታማነት ማደግ አለበት። ምርታማነትን ለማሳደግ ደግሞ ድጋፎቻችን በቡድን ብንደግፍ ውጤት እናመጣለን ብለን በተመረጡ ሰብሎች ላይ ሥራውን የጀመርነው።

**አዲስ ዘመን፡- በክላስተር የአስተራረስ ዘዴ የተመረጡ ሰብሉች ላይ ማተኮር ለምን አስፈለገ?**

**አቶ ኢሳያስ፡-** የክላስተር እርሻ ሥራ ስንጀምር ለሃገሪቱ የምግብ ዋስትና ወይም የምግብ አቅርቦት ወሳኝ የሚባሉ ሰብሎችን መርጠን ነው። በተጨማሪም ለፋብሪካ ግብዓትነት፣ ለኤክስፖርት የሚፈለጉ ሰብሎች ላይ ነው ትኩረት ያደረግነው። ሁሉንም ሰብል እንደግፍም፤ በሁሉም ሰብል ግን የአርሶአደሩ የመደራጀት መብቱ የተጠበቀ ነው። ምክንያቱም ደግሞ እንደመንግሥት ሃገሪቱ ባላት ውስን ሃብት መደገፍ የምትችለው በተመረጡት ላይ ብቻ በመሆኑ ነው።

ከዚህ አኳያ በክላስተር አሠራር ላይ ሰፊ ሥልጠና ይሰጣል፤ የግብዓት አጠቃቀም ከመነሻ ጀምሮ ምን እድገት አሳየ የሚሉትን ነገሮች ይታያሉ። ከምርት አንፃር ምንአይነት የምርታማነት እድገት መጣ? የሚለውን ለማወቅ ጥናት ያስፈልጋል። እነዚህ ጉዳዮች ሀብት ይጠይቃሉ። በመሆኑም ጊዜም ገንዘብም የሚፈልግ በመሆኑ መጀመሪያ በውስን ቦታዎች ላይ በተመረጡ ሰብሎች ላይ ነው የጀመርነው። አሁን ደግሞ ክልሎችም በራሳቸው አስፋፍተው እየሠሩ ነው። ለምሳሌ ማሽላ በፌዴራል ደረጃ ለክላስተር የተመረጠ ሰብል አይደለም፤ አማራ ክልል ግን አለ። ደቡብ ላይ ደግሞ ቦሎቄ በስፋት የሚመረት ሰብል እንደመሆኑ በክልሎች ክላስተር አደረጃጀት የማካተት ሥራ ተሠርቷል።

እንደየክልሉ ነበራዊ ሁኔታ ሰብሎች እየተመረጡ ክልሎች በራሳቸው ተነሳሽነት እየሠሩ ይገኛሉ። በመሆኑም ለምግብ ዋስትና፣ ለኢንዱስትሪና ለኤክስፖርት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን ሰብሎች ተመርጠው ነው እየተሠራ ያለው። ደግሞም የክላስተር ሥራ በአንድ ጊዜ መሥርተን የምናቆመው ሳይሆን እያንዳንዱ የምርት ክላስተር ኢንተርፕራይዝ እስኪሆን ድረስ ከስድስት እስከ ስምንት ደረጃዎችን ማለፍ የሚጠበቅበት በመሆኑ እዚያ እስኪደርሱ ድረስ የመንግሥት ድጋፍ ይሻሉ። ይህም በተለይ ዘላቂ የምግብ አቅርቦት ከማቅረብ አንፃር ትልቅ ፋይዳ አለው። ከተበጣጠሰ ማሳ የሚሰበሰበው ምርት የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት አያስችልም፤ በሌላ በኩል የማምረቻ ወጪው ከፍተኛ ነው። ይህም አንዳንዴ ከውጭ ከሚገባው በላይ ወጪው የሚበልጥበት ሁኔታ አለ።

**አዲስ ዘመን፡- የኩታ ገጠም እርሻ በመንግሥት ደረጃ ከተጀመረ ወዲህ ምን አይነት ተጨባጭ ውጤት መጥቷል? በቀጣይስ ለማስፋት ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ኢሳያስ፡-** በነገራችን ላይ የክላስተር እርሻ ሲባል ከመደራጀት ባለፈ የዘር ማባዣ ተቋማትን በየአካባቢው ማቋቋም ፣ ያደጉትን ክላስተሮች ወደ ተቋም ከፍ እንዲሉ የመደገፍ ሥራ መሥራት ይጠይቃል። ከዚያ አኳያ የተወሰኑ ክላስተሮች በተሻለ ሁኔታ ላይ አሉ። ለምሳሌ ሄጦሳ ላይ አንድ ክላስተር ወደ ስንዴ የዘር ብዜት ማኅበር አድጓል። ምክንያቱም ያ ክላስተር ጥሩ ሥራ የሠራ እና ጥሩ ቅንጅት ስላለው ሌሎች የዘር አባዥ ተቋማት ከእነሱ ጋር ለመሥራት ይመርጧቸዋል። የተሻለ ግብዓት አጠቃቀም በማምጣት ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ነው ዋናው ዓላማው። ከዚህ አንፃር ጎን ለጎን ከተሠሩ ሥራዎች አንደኛው የሜካናይዜሽን ሥራ ነው።

ለዚህ ደግሞ እንደመንግሥት ከተሠሩ ሥራዎች ውስጥ ከውጭ የሚገቡ እርሻ ማሽኖችን ከታክስ ነፃ ማድረግ ሲሆን፤ በቡድን በማሠራትና በግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አማካኝነት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ላይ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። የሜካናይዜሽን እርሻን ባለፉት ዓመታት ስንመለከት ሁለት ሚሊዮን ሄክታር ነበር፤ ዘንድሮ በክረምቱ እርሻ 3 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመካናይዝድ መልኩ ታርሷል። ክረምቱ እስከሚጠናቀቅ እስከ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሜካናይዜሽን ለማረስ እየሠራን ነው። በክልሎች ድጋፍና ኮላተራል በማስያዝ በአሁኑ ወቅት ከአንድ ሺ በላይ ትራክተሮች ሃገር ውስጥ ገብተዋል። እነዚህ አይነት አገልግሎቶች ክላስተርን ይደግፋሉ። የዘር አቅርቦታችንም ያድጋል ተብሎ ይታመናል።

በክላስተር ተደራጅተው ለሚሠሩ ማዳበሪያና ግብዓቶችንም ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የማድረግ ሥራ ተሠርቷል። ይህንን ጠቀሜታ አርሶአደሩ እየተገነዘበ በመሆኑ የመደራጀት ፍላጎቱ ጨምሯል። አንደኛ ነገር ከ30 አርሶአደሮች ውስጥ ብዙ ደካማ አለ፤ ግን ጥቂት ጠንካሮች በመኖራቸው እነዚያን ተከትለው ያርሳሉ። ስለዚህ በዚያ መሠረት ሞዴሎቹ ሌላ ሞዴል እየፈጠሩ ነው ያሉት። ይህ የክላስተር አደረጃጀት ያመጣውን ለውጥ ሲመለከቱ ደግሞ ሌሎችም አርሶአደሮች አደራጁን ወደሚል ሁኔታ መጥተዋል። በዚህ ሂደት ውስጥ ደግሞ ትልቅ ለውጥ የፈጠርነው ክልሎች የራሳቸው አድርገውታል፤ እስከ ቀበሌ ባለው መዋቅራቸው የራሳቸውን እቅድ በማዘጋጀት የራሳቸውን ሰብሎች መርጠው ማምረት ጀምረዋል።

በዚህም የአትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎች ተካተዋል። እንዲሁም በእንስሳት ተዋፅዖ የተደራጀ አለ። በአጠቃላይ በሰብል ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የግብርና ዘርፎች ላይ የመስፋት ሁኔታ ነው ያለው።

**አዲስ ዘመን፡- ክላስተር በተለይ ስንዴ ላይ ያመጣው እምርታ እና በሃገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ እያበረከተ ያለውን አስተዋፅዖ ቢያብራሩልን?**

**አቶ ኢሳያስ፡-** እንደአጠቃላይ ግብርናው የሃገሪቱ ኢኮኖሚ መሠረት ከሆኑ ዘርፎች ዋነኛው እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ ረገድ ከግብርናው ከሚጠበቁት ነገሮች መካከል የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው። እንዲሁም ፋብሪካዎች የሚፈልጉትን የጥሬ እቃ አቅርቦት በበቂ መጠንና በዘላቂነት ማቅረብ፤ ከውጭ በጥሬና እሴት ተጨምሮባቸው የሚመጡ ምርቶችን መቀነስ፤ የኤክስፖርት አቅምን ማሳደግ ነው። ይህም ሲባል ወደ ውጭ የምንልከውን ምርት በብዛትም ሆነ በጥራት በማሳደግ የውጭ ምንዛሪን ግኝትን ከፍ ማድረግ ነው። የመጨረሻው የሥራ ዕድል መፍጠር ነው።

ከዚህ አንፃር ባለፉት ስድስት ዓመታት ከሠራናቸው ሥራዎች ውስጥ ከውጭ የምናስገባው ምርቶችን መቀነስ ችለናል። እንደሚታወቀው ደግሞ ከዚህ ውስጥ ዋነኛ ከፍተኛ ወጪ የሚወጣባቸው ስንዴና ዘይት ነበሩ። እነዚህን ምርቶች በሃገር ውስጥ ለመተካት ለአስር ዓመት አቅደን ሰፊ ሥራ እየሠራን ነው። ለዚህም የቅባትና የአትክልት ሰብሎች እንዲሁም የእንስሳት ተዋፅዖ ምርቶችን የማስፋት እየተሠራ ነው።

ከስንዴ አኳያ በተለይ ባለው ላይ ምርታማነትን ማሳደግ አንደኛው አቅጣጫ ሲሆን ለዚህም የተሻለ የግብዓት አጠቃቀም ማሳደግ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ሲሠራ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ የክላስተር እርሻን ማስፋፋት ሲሆን ለዚህም የማይታረስ መሬትን መጨመር ነው። ይህ ሲባልም በዝናብም ሆነ በመስኖ የሚመረተውን መሬት ማስፋት ላይ ሰፊ ርብርብ ተደርጓል። በዚህ ረገድ ስንጀምር በመስኖ የሚታረሰው መሬት 20 ሚሊዮን ሄክታር ብቻ ነበር። አሁን 12 ነጥብ 97 ሚሊዮን ደርሰናል። መሬትን በመጨመር ሂደት ደግሞ የመስኖ አማራጭን መጠቀም የሚለው ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ነው። ግን ምርታማነትን በማሳደግ ሰፊ ሥራ የተሠራበት የክላስተር አሠራር ነው። በተለይ በመኮሮኒ ስንዴና በዳቦ ስንዴ ላይ ሰፊ ሥራዎች ተሠርቷል። በእነዚህም ላይ ከ70 በመቶ በላይ የሚሆነው እርሻ በክላስተር እየታረሰ ነው ያለው።

ምርታማነቱን ስንመለከት በክላስተር የሚያርሱ ወደ በአማካኝ 40 ኩንታል ማግኘት ችለዋል። ገና ስንጀምርም እንኳን በመደበኛው 27 ኩንታል ሲመረት በክላስተር እስከ 35 ኩንታል የደረሰበት ሁኔታ አለ። አሁን ደግሞ ወደ ክላስተር እርሻ ማደጉና ለስንዴ ትኩረት በመሰጠቱ ምርታማነታችን ወደ 40 ኩንታል ከፍ ብሏል። እናም በክላስተር ሲሠራ ሁሉም የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ለማሳደግ ጥረት ይደረጋል። እንደአጠቃላይ ስንዴ አሁን ወደ 70 በመቶ አካባቢ በክላስተር የሚታረስበት ሁኔታ አለ። እንደሃገር በአስር ዓመት ሃገር በቀል የልማት መርሐግብር ላይ ያስቀመጥነው መርሐ መሠረት የመጀመሪያ ሥራ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባውን ምርት ቀንሰናል። በተወሰነ ደረጃ ኤክስፖርት ተጀምሯል።

በቀጣይ ደግሞ በሃገር ውስጥ አቅርቦትን ማሳደግ፣ የግብይት ሥርዓቱን ማሻሻል፤ በተለይ እያመረትን ዓለምአቀፍም ሆነ በሃገር ውስጥ ያለውን የዋጋ ንረትና የኢኮኖሚ ጫና ለመቀነስ ግብይት ላይ መሥራት ይገባል ብለን እየተረባረብን ነው። ሌላው ደግሞ በተለይ አሁን የሠራነው ትልቁ ሥራ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ በክልል ፕሬዚዳንቶች መሪነት የተሠራ ሥራ ነው። በቀጣይ ደግሞ ይህ ሥራ መደበኛ ሥራ የማድረግና ሁሉም እንዲሠራውና የግብይት ሥርዓቱ ላይ ያሉ ችግሮችን መፍታት ይገባል፤ ከዚያ ባሻገር ግን ወደ ውጭ የሚላከውን የስንዴ ምርት በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ግኝታችንን ከፍ ማድረግ ይጠበቃል።



> **የግብርና ምርቶች ላይ አሁንም ጥቂት አካላት የሚወስኑበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ አብዛኛው የአርሶአደሩ ምርት መርካቶ ተወስኖ ነው የሚሸጠው፡፡ ይህ ግብይቱ በሕግ ማዕቀፍ የሚመራ ባለመሆኑ አርሶአደሩ ሰርቶ አመድ አፋሽ አድርጎታል**

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ የክላስተር ሥራ የምርምር ተቋማት ሚና እንዴት ይገለፃል?፤ አንዳንድ ቦታዎች ላይ በተለይ በቆሎ ላይ የተሻሻሉ ምርጥ ዘርያዎችና የቴክኖሉጂ እጥረት መኖሩን ሲገለፅ እንሰማለን፤ በተመሳሳይ መጤ ተምችና ግሪሳ ወፍን በመከላከል ረገድ ከምርምር ጋር ያላችሁ ጥምረት ምን ይመስላል?**

**አቶ ኢሳያስ፡-** ዘር ላይ ሁለት አይነት ችግር ነው የሚስተዋለው። አንደኛው እንደተባለው የዘር እጥረት አለ፤ ይህም ሲባል ፍላጎቱ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ነው። ሁለተኛ ግን ሰፊ የገበያ ሥራ በመሠራቱ በጣም ተፈላጊ የሆኑ የዲቃላ ዝርያዎችን ብቻ የመምረጥ ዝንባሌ አለ። በመሆኑም ከምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር የአርሶአደሩን ፍላጎት ለማሟላት እየሠራን ነው። ያም ቢሆን እጥረቱ አለ። ዩኒየኖችና በዚህ ሥራ ላይ የተሠማሩ የውጭ ኩባንያዎች የበኩላቸውን ጥረት እያደረጉ በመሆኑ የተሻለ አቅርቦት ይኖራል ብለን እናስባለን። ከምርምር ተቋማት ጋር ግን በተለይ ዝርያዎችን በመለየት የምሠራቸው ሥራዎች አሉ። ለአብነት መጥቀስ ካስፈለገ አዋሽ ተፋሰስን ተከትሎ የተሠሩ ሥራዎች ከእነዚህ ተቋማት ጋር በመተባበር ነው። ከዚህ አኳያ የወረር ግብርና ምርምር ስምንት የሚሆኑ አዳዲስ ዝርያዎችን አውጥቷል። ከሌሎች ጋር በመሆንም በተለይ ከስንዴ ጋር ተያይዞ ወደ አስር ዝርያዎችን መርጠን ነው ወደ ሥራ የገባነው። በዚህ ሂደት ውስጥ በጋራ ሆነን ነው ስንሠራ የቆየነው። በመሠረቱ እንዲህ አይነት ሃገራዊ ፕሮግራሞች የሚቀረፁት ከምርምር ተቋማት መነሻ በመውሰድና የተሠሩ ሙከራዎችን በማየት ነው። የምንሠራው ተቀናጅተን ነው፤ እያንዳንዱን ሥራ ስንገመግምም በጋራ ነው።

መጤ ተምችና አንበጣን በተመለከተ የተነሳው ጥያቄ በቀጥታ የእኛ ዘርፍ ጋር የሚገናኝ አይደለም፤ የፌዴራል ሥልጣን ነው፤ ይሁንና እነዚህን ለመከላከል እንደሃገር ትልቅ አቅም ፈጥረናል። ከምሥራቅ አፍሪካ አንበጣ መከላከል ድርጅት ጋር አብረን እንሠራለን፤ ዋና መሥሪያ ቤቱም ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ከክልሎች ጋር በመሆንም መድኃኒት ለሚረጩ አውሮፕላኖች ማረፊያ በሌላቸው አካባቢዎች ላይ ቦታ እያዘጋጀን ነው። እኛ የገዛናቸው አውሮፕላኖች ደግሞ በቅርቡ በተደረገው ስምምነት የሚመራ ድርጅት ተፈጥሮ በማሠልጠን የማብቃት ሥራ ይሠራል። በዚህም የግሪሳ ወፍን መከላከል የምንችልበትን አቅም እየፈጠርን ነው። ከክልሎች ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ አቅም ገንብተን የሚያርፍባቸውን ቦታዎች የመለየት፣ ሥራ ይሠራል። እንዲሁም ዓለምአቀፉ የእርሻ ድርጅት የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ያለው በመሆኑ ያንን ተጠቅመን በየጊዜው ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ በመስጠት በራሳችን በአውሮፕላን ጭምር አሰሳ የማካሄድ ሥራ ይሠራል። ይህም የመከሰት ዕድሉን የሚቀንስ ሲሆን ከተሰከተ ደግሞ የመከላከል ሥራ ይሠራል። እንደአጠቃላይ በመከላከል ሃገራዊ አቅም የገነባንበት ሥራ ነው።

በዚህ ዓመት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ በአፋርና በሌሎች አካባቢዎች ላይ የአውሮፕላን ሜዳ እየተሠራ ነው። በሚቀጥለው ዓመት እንዲህ አይነት የአንበጣም ሆነ የግሪሳ ወፍ ወረርሽኝ ቢከሰት ለመከላከል የሚያስችል አቅም እየገነባን ነው። በተጨማሪም መሠረታዊ የሚባሉ አቅርቦቶችን የማሟላት ሥራ እየተሠራ ነው።

በጎረቤት ሃገራትም ሲከሰት ኢትዮጵያ ሳይደርስ እዛው እያለ የመከላከል ሥራዎችን ከኢጋድ ጋር እንሠራለን። እኛ ጋር ያሉት ዘመናዊና የመከላከል አቅማቸው ከፍተኛ የሆነ አውሮፕላኖች ነው ያስገነባነው፤ ድሮኖችንም አስገብተናል። የመኪና መርጫዎችን አዘጋጅተናል። እነዚህን መሣሪያዎች በእርዳታ ከዓለም የምግብ እርሻ ድርጅትና ከሌሎችም አካላት አግኝተናል። እንዲሁም መንግሥት የራሱን በጀት በመመደብ ያሟላንበት ሁኔታ አለ።

**አዲስ ዘመን፡- እንደአጠቃላይ በዘርፉ ሲፈቱ የሚገባቸው ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ኢሳያስ፡-** በተለይ ቴክኖሎጂ ማስረፅ ላይ ጉድለቶች አሉብን። ሁሉንም አርሶአደር ተደራሽ ማድረግ ላይ ክፍተት ያለብን በመሆኑ ከምርምር ተቋማት ጋር ተቀናጅተን እየሠራን ነው። ሀገሪቱ ሰፊ እንደመሆንዋ የተለያየ ሥነ-ምሕዳር ያላት እንደመሆኑ ችግሮቹም በዚያው ልክ ይለያያሉ። ይህንን ማዕከል ያደረገ ሥራ ነው እየሠራን ያለነው። በተመሳሳይ አብዛኞቹ ቴክኖሎጂዎች ከውጭ የሚመጡ መሆናቸው፤ በተለይ ከትራክተር ጀምሮ እስከ ኮምባይነር ድረስ አብዛኞቹ ከውጭ የሚመጡ በመሆኑ የቴክኖሎጂ አጠቃቀማችን ላይ ውስንነት ይታያል። በእርግጥ መንግሥት ከታክስ ነፃ እንዲገቡ አድርጓል። ሆኖም መሣሪያዎችን በቡድን በማደራጀትና ጥቅም ላይ ማዋል ላይ አሁንም ክፍተት አለብን።

በመሆኑም የቴክኖሎጂና የሜካናይዜሽን አጠቃቀም ዝቅተኛ መሆኑ የሚፈለገውን ውጤት እንዳናመጣ አድርጎናል። ወጣቱንም ወደ ግብርናው ዘርፍ እንዳይሳብ አድርጎታል የሚል እምነት አለኝ። ሌላው ግብይት ነው ትልቁ ችግር፤ ምርታማነት የቱንም ያህል ቢጨምርም አሁንም ግብይት ላይ ዋጋው ውድ የሚሆንበት ሁኔታ አለ። ይህ ደግሞ በተለይ አስገዳጅ ሕግ በማውጣት በሰፊው መሥራት ያስፈልጋል። ይህ ሲባልም ልክ ምርታማነትን ለማሳደግ በተሠራው ልክ ግብይት ላይ ያለው ክፍተት ሊታይ ይገባል። አሁን ባለው ሁኔታ ብዙ ቢመረትም ግብይቱ ላይ ካልተሠራ ትልቅ ማነቆ ነው የሚሆነው። የግብርና ምርቶች ላይ አሁንም ጥቂት አካላት የሚወስኑበት ሁኔታ ነው ያለው። አብዛኛው የአርሶአደሩ ምርት መርካቶ ተወስኖ ነው የሚሸጠው። ይህ ግብይቱ በሕግ ማዕቀፍ የሚመራ ባለመሆኑ አርሶአደሩ ሰርቶ አመድ አፋሽ አድርጎታል። ስንዴም ሆነ ሌሎች ሰብሎች በስፋት እየተመረተ ነው፤ አኩሪአተርና ሌሎችም ሰብሎች ላይ ተዓምራዊ የሚባል እድገት ያስመዘገቡ ምርቶች ናቸው፤ ሆኖም ገበያ ላይ ውድነቱ እንዳለ ነው። እዚያ ላይ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እስከታች ባለው ትስስር የምንሠራው ሥራ አለ፤ ሆኖም ችግሩን በዘላቂነት መፍታት አልተቻለም። በመሆኑም ግብርናችንም ሆነ ግብይቱን እኩል ማዘመን ይጠበቅብናል። እንደመንግሥትም ተለይቶ እየተሠራባቸው ናቸው።

እነዚህን ችግሮች መፍታት ከቻልን በዋናነት የምግብ ዋስትናችንን እናረጋግጣለን፤ ሃገሪቱ የተሻለ ምርት በመላክ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ ታገኛለች፤ አቅርቦትና ፍላጎት የሚቀራረብበት ሁኔታ ይፈጠራል፤ ያ ደግሞ ለኅብረተሰቡ የሚፈልገውን ምርት በአቅሙ መግዛት ያስችለዋል። እንደአጠቃላይ ሁለንተናዊ እድገት እናመጣለን። ምክንያቱም ደግሞ አብዛኛው ኅብረተሰባችን አርሶአደር እንደመሆኑ አርሶአደር ሲለወጥ ሃገርም ታድጋለች የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ኢሳያስ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# አዳዲስ የኢንቨስትመንት አሠራር ሥርዓቶችና የሚጠበቁ ውጤቶች

አንተነህ ቸሬ

ባለፈው 2016 በጀት ዓመት በብዙ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ተስፋ ሰጭ ውጤት እንደተመዘገበ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ገልጿል። ኮሚሽኑ የቢዝነስና የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታን በማሻሻል፣ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን በማስተዋወቅና ኢንቨስትመንትን በማሳለጥ፣ የድኅረ ኢንቨስትመንት ድጋፍ በመስጠት፣ የኢንቨስትመንት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ እንዲሁም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አመራርና አስተዳደር ተግባራትን በማከናወን የወጪ ንግድንና ተኪ ምርትን፣ የሥራ ዕድል ፈጠራን፣ የዘርፎችንና የባለሃብቶችን ትስስር እና የክህሎትና ቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማሳደግ ያስቻሉ ተግባሮችን አከናውኗል።

በዚህም ባለፈው የበጀት ዓመት ሦስት ነጥብ 82 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ ተችሏል። 329 አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃዶች ተሰጥተዋል። ፈቃድ ከወሰዱ ባለሃብቶች መካከል ከ75 በመቶ በላይ የሚሆኑት በማምረቻ ዘርፍ የሚሰማሩ ናቸው። ከሁሉም ኢንዱስትሪ ፓርኮች 115 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ተገኝቷል። ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለመግባት ፍላጎት ካሳዩ 70 ድርጅቶች ጋር የመግባቢያ ስምምነቶች ተፈርመዋል። በዘጠኝ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በሚገኙ 205 ፕሮጀክቶች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ተከናውነዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ ወቅታዊ ሀገራዊና ዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታን ከግምት ውስጥ ባስገባና የሀገርን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነት ክለሳዎች ተጠናቀው አዳዲስ ድርድሮች ተደርገዋል። ከአዳዲስ ቀጣናዊና ክልላዊ የንግድና ኢንቨስትመንት ዕድሎች ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችም ተከናውነዋል። የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት አቅሞችና መልካም ዕድሎች በበርካታ ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረሞችና ኤግዚቢሽኖች ላይ እንዲተዋወቁም ተደርጓል።

ኮሚሽኑ በ2017 የበጀት ዓመት አዳዲስ የኢንቨስትመንት አሠራር ሥርዓቶችን በመተግበር የተሻለ ሀገራዊ የኢንቨስትመንት አቅም ለመፍጠር እንደታቀደም ገልጿል። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ወይዘሮ ሐና አርዓያሥላሴ በበጀት ዓመቱ በዘርፉ እስካሁን ከተገኘው ውጤት የተሻለ ስኬት ለማስመዝገብ መታቀዱን አመልክተዋል። እሳቸው እንደሚሉት፣ ኮሚሽኑ የሀገሪቱን እምቅ ሀብት በመጠቀም ጥራት ያለው የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በመሳብ እና የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን በመጨመር፣ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ያለውን ድርሻ የማሳደግ ኃላፊነቱን ለመወጣት ለወቅቱ የሚመጥኑ አዳዲስ አሠራሮችን ይተገብራል።

‹‹በበጀት ዓመቱ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት አዲስ መሠረት ለመጣል የሚያስችል እቅድ ተዘጋጅቷል። አዳዲስ የኢንቨስትመንት ሕግጋት ወደ ሥራ መግባታቸውን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ይዞታ/አሠራር እየተቀየረ መምጣቱን፣ ተለዋዋጭ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ክስተቶች መታየታቸውን.ወዘተ ተከትሎ ኮሚሽኑ እስካሁን ከነበሩት አሠራሮች የተለዩ ሥርዓቶችን በመቅረፅ ወደ ተግባር ገብቷል›› በማለት ያስረዳሉ።

የቢዝነስና የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታን በማሻሻል፣ የኢንቨስትመንት አቅምና ዕድሎችን በማስተዋወቅ፣ ኢንቨስትመንትን በማሳለጥ፣ የድኅረ ኢንቨስትመንት ድጋፍ በማድረግ፣ የኢንቨስትመንት ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አመራርና አስተዳደር ተግባራትን በማከናወን ረገድ የሚተገበሩት አሠራሮች፤ የወጪ ንግድንና ተኪ ምርትን፣ የሥራ ዕድል ፈጠራን፣ የዘርፎችንና የባለሃብቶችን ትስስር እና የክህሎትና ቴክኖሎጂ ሽግግርን የማሳደግ ግቦችን ትርጉም ባለው መልኩ ያሻሽላሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታን በማሻሻል ረገድ በበጀት ዓመቱ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ አዳዲስ የኢንቨስትመንት ሕጎችን ወደ ሥራ የማስገባት ተግባር ነው፤ የሎጂስቲክስ ቅልጥፍናን ለማሻሻል የሚያስችሉ አሠራሮችም ወደ ሥራ ይገባሉ።

‹‹ከኢንቨስተሮች ጋር በምናደርጋቸው ውይይቶች እንደተረዳነው ኢንቨስተሮቹን ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች መካከል ዋናዎቹ የውጭ ምንዛሪና ተያያዥ ችግሮች እንዲሁም የሎጂስቲክስ ሥርዓቱ ናቸው›› ያሉት ኮሚሽነሯ፣ የውጭ ምንዛሪ ችግሩ በብሔራዊ ባንክ እየተሠሩ ባሉ ሪፎርሞች መፍትሔ ያገኛል የሚል እምነት አለን ሲሉም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ የሎጂስቲክስ ሥርዓቱ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማከናወን ማነቆ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱ ነው፤ በቅልጥፍናም ሆነ በዋጋ ረገድ ብዙ ችግሮች አሉበት። ስለሆነም ለዚህ ችግር መፍትሔ የሚሆኑ አሠራሮች ወደ ሥራ ይገባሉ። መንግሥት ኢንቨስተሮች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚሰጣቸው ገንዘብ ነክና ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ልዩ ልዩ ማበረታቻዎች አሉ። ተወዳዳሪነትን መገምገምና ከዚህ የተሻለ ተወዳዳሪ ለመሆን ምን ማድረግ እንደሚገባ ጥናት ሠርቶ ምክረ ሃሳብ የማቅረብ እቅድ ተይዟል። እነዚህ ተግባራት ለኢንቨስትመንት ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ለይቶ የቢዝነስና ኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታውን የማሻሻል እቅድ አካል ናቸው።

ወይዘሮ ሐና ባለፈው የበጀት ዓመት የጅምላና ችርቻሮን ጨምሮ ለብዙ ዓመታት ዝግ የነበሩ የንግድ ዘርፎች ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት እንዲሆኑ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ መፈቀዱን አስታውሰው፣ መመሪያው ከወጣ በኋላ ኮሚሽኑ ቅድመ ዝግጅቶችን (መመሪያው ወደ ሥራ የሚገባበትን ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፣ ለሠራተኞች ሥልጠና መስጠት...) ሲያደርግ እንደቆየም ገልጸዋል። ባለሃብቶች ፍላጎቶችን በማሳየታቸው መስፈርቶቹን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ወደ ሥራ እንዲገቡ እንደሚደረግ ይገልፃሉ። ስለሆነም ከንግድ ዘርፎች መከፈት ጋር ተያይዞ በ2017 በጀት ዓመት አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች እንደሚጠበቁ ጠቁመዋል።

ባለፈው የበጀት ዓመት የተከናወኑ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነት ክለሳዎችን፣ አዳዲስ ድርድሮችን እና ቀጣናዊና ክልላዊ የንግድና ኢንቨስትመንት ዕድሎችን ወደ ተግባር በመለወጥ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ለማግኘትም ታቅዷል። ‹‹ኢትዮጵያ ‹ብሪክስ›ን (BRICS) መቀላቀሏን ተከትሎ ከ‹ብሪክስ› አባል ሀገራት አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ የተጀመሩ እንዲሁም ከአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና (AfCFTA) ተጠቃሚ ለመሆን የሚያግዙ ሥራዎችም ተጠናክረው ይቀጥላሉ።

አብዛኞቹ ኢንቨስትመንቶች በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ያተኮሩ እንደሆኑ የጠቆሙት ወይዘሮ ሐና፣ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስልቶች ከአምራች ዘርፍ ውጭ ያሉትን የኢንቨስትመንት ዘርፎችን ማበረታታትና ማስፋፋት በሚያስችል መልኩ እንደተቀረፁ ይናገራሉ። ‹‹ባለፉት ጥቂት ዓመታት በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በቀጣናው ብዙ ጂኦፖለቲካል ለውጦችን አስተናግደናል። ስለሆነም አዳዲስ የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ዕድሎችን መሠረት ያደረገ የኢንቨስትመንት ስትራቴጂ ያስፈልገናል። የዓለም አቀፍ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰት ሂደት እየተለወጠ መጥቷል። በተለይም የኮቪድ ወረርሽኝን (COVID-19) ተከትሎ የዓለም አቀፍ ንግድና ኢንቨስትመንት የእሴት ሰንሰለት (Global Value Chain) አሠራር እየተለወጠ ነው። ›› ሲሉም አስገንዝበዋል።

ብዙ አምራቾች የምርት ስፍራዎቻቸውን ወደየሀገሮቻቸው የመመለስ አዝማሚያ ውስጥ ናቸው ያሉት ኮሚሽነሯ፣ ይህን ተከትሎም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በዓለም አቀፍ ደረጃ እየቀነሰ ይገኛል ይላሉ። ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣውን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለማቆየትና ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የተሻለ አገልግሎት መስጠትና የሀገራችንን ሀብቶች ማስተዋወቅ አለብን ብለዋል።

‹‹አሁን ሀገሪቱን የምናስተዋውቅበት መንገድ ከ10 ዓመታት በፊት ያስተዋወቅንበት ከሆነ ውጤታማ መሆን አንችልም። ስለዚህ ይህን ዓለም አቀፋዊና ቀጣናዊ ለውጥን ታሳቢ ያደረገ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን እቅድ ያስፈልገናል›› በማለት አዳዲስ የኢንቨስትመንት አቅምና ዕድል ማስተዋወቂያ መንገዶች መዘጋጀታቸውን ያስረዳሉ።

**በበጀት ዓመቱ አዳዲስ ሕግጋትን በመተግበር፣ አዳዲስ የኢንቨስትመንት ምንጮችን በመጠቀም እና የተሻሻሉ የፕሮሞሽን አሠራሮችን ሥራ ላይ በማዋል አራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ እንዲሁም ለ341 ፕሮጀክቶች (ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጭ) አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃዶችን ለመስጠት ታቅዷል**

እንደወይዘሮ ሐና ገለፃ፣ በበጀት ዓመቱ አዳዲስ ሕግጋትን በመተግበር፣ አዳዲስ የኢንቨስትመንት ምንጮችን በመጠቀም እና የተሻሻሉ የፕሮሞሽን አሠራሮችን ሥራ ላይ በማዋል አራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ እንዲሁም ለ341 ፕሮጀክቶች (ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጭ) አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃዶችን ለመስጠት ታቅዷል። አዳዲስ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ወደ ሥራ እንዲገቡ የሚያስችሉ የፈቃድ አሰጣጥ፣ የማበረታቻና የክትትል ሥርዓቶች ይተገበራሉ። ባለሃብቶች አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን እንዲያገኙ በመርዳት እና አዳዲስ ዘርፎችን በማልማት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግም ታቅዷል።

ባለፈው የበጀት ዓመት የኢንቨስትመንት ከባቢን በማሻሻል ረገድ ከተከናወኑ ዐበይት ተግባራት መካከል አንዱ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መፅደቁና ወደ ሥራ መግባቱ ነው። አዋጁ አዳዲስ የቢዝነስና ኢንቨስትመንት ዕድሎችን ይፈጥራል። ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ላይ ተሠማርታ ቆይታለች። በፓርኮቹ ልማት ላይ በተገኙት ውጤቶችና ባጋጠሙት ተግዳሮቶች ላይ ዝርዝር ጥናት ተደርጎ ከፓርኮቹ የተሻለ ውጤት ለማግኘት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ ፀድቋል።

አዋጁ ነፃ የንግድ ቀጣናዎችን፣ የሎጂስቲክስ እና ከማምረት ውጭ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ለማሳለጥ የሚያስችል ማዕቀፍ ነው። ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች በዓለም አቀፍ ደረጃ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ፣ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ያስችላል። የ2017 በጀት ዓመት እቅድም ይህን ተግባር ታሳቢ ያደረገ ነው።

በልዩ ኢኮኖሚ ዞኖችና በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ 45 አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃዶችን ለመስጠት ታቅዷል። በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተመርተው ወደ ውጭ ከሚላኩ ምርቶች መካከል ትልቁን ድርሻ ከያዘው ከአልባሳትና ጨርቃ ጨርቅ ምርት ዘርፍ ባሻገር በሌሎች ዘርፎች የተጀመሩ ሥራዎችን በማጠናከር ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት እቅድ ተይዟል።

ከሥራ ፈጠራና ኤክስፖርት በተጨማሪ የትስስር እና የእውቀት ሽግግር ግቦች በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ለማወቅና ለማጠናከር የሚያስችል የመረጃ አሰባሰብና ትንተና ሥርዓት ይተገበራል። በ2017 በጀት ዓመት በትኩረት ከሚከናወኑ ተግባራት መካል አንዱ የመረጃ አሰባሰብና ትንተና ሥርዓትን የማጠናከር ሥራ እንደሆነ ወይዘሮ ሐና ያስረዳሉ።

‹‹እንደሀገር ከኢንቨስትመንት የምንፈልጋቸው ግቦች ኤክስፖርት፣ ሥራ ፈጠራ፣ ትስስር እና የእውቀትና የክህሎት ሽግግር ናቸው። ከእነዚህ መካከል እስካሁን ድረስ የተሻለ መረጃ ያለን በኤክስፖርትና በሥራ ፈጠራ መስኮች ነው። በትስስርና ሽግግር ረገድ ያለን እውቀትና መረጃ በቂ አይደለም›› ያሉት ኮሚሽነሯ፣ ስለዚህ በቀጣይ ዓመታት ለዚህ መሠረት የሚሆን የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት ሊኖረን ይገባል ብለዋል። ‹‹ለሀገራችን ዘላቂ እድገት በሚሆን መልኩ ትክክለኛ እውቀትና ክህሎት እየተላለፈ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ለዚህም የመረጃ አሰባሰብና ትንተና ሥርዓትን የማጠናከር ሥራ ትኩረት ያገኛል›› በማለት ያብራራሉ።

በክትትልና ቁጥጥር ረገድ ደግሞ፣ ከዚህ ቀደም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ባሉ ፕሮጀክቶች ላይ ይበልጥ ከማተኮር በመሻገር በበጀት ዓመቱ ከፓርክ ውጭ ያሉትን ጨምሮ በ142 ፕሮጀክቶች ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ለማድረግ ታቅዷል። ተኪ ምርቶችን የማምረት አቅምን ማሳደግ፣ ከክልሎች ጋር ያለውን ቅንጅት ማጠናከር እና ፕሮጀክቶችን ወደ ምርት ማሸጋገርም በበጀት ዓመቱ ትኩረት የሚቸራቸው ሌሎች ተግባራት ናቸው።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

## ጎሜ

# ሙስና በፀረ-ሙስና ይስቃል

**ይቤ ከደጃች .ውቤ**

> **ዜጋውና መንግሥት ለሀገር ሕልውና ሲታገል፤ በጎን ተሸሽገው ሙስናቸውን የሚያሳድዱ የውስጥ አርበኞችና ጥቅም አሳዳጆች አሉ፡፡ ይህም አጋጣሚው ተጠቅመው ሀገር እየቦረቦሩና እየመዘበሩ ያሉት ሙሰኞች ናቸው**

ኢሕአዴግ በትረ መንግሥቱን ከጨበጠ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የፌዴራል ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተቋቋመ። ዓላማው ስሙም እንደሚናገረው ሙስናን ማጥፋት ነው፤ ግን ኮሚሽኑ ሲቋቋም ሙስናን ከማጥፋት ይልቅ ለማስፋፋት የተቋቋመ ይመስል ሙስናን በሀገሪቱ ሰፍቶ ተንሠራፍቶ አገኘነው።

በወቅቱ ፀረ-ሙስና ስሙን ታቅፎ ጽሞናን ተደግፎ እያየ እንዳላየ እየሰማ እንዳልሰማ ሆኖ ተገኘ። በሙስና የደለቡ ባለሥልጣናትን እያዩ እንዳላዩ በማለፍ የተወሰኑ በሙስና ተዘፍቀው ተገኙ የተባሉ መናኛ ካድሬዎች በየጊዜው እንዲከሰሱ ይደረግ ነበር። ከእነዚህ ውስጥ ብዙዎቹ በፖለቲካ ተቃርኖ በመታከክ የተከሰሱና የታሠሩ ነበሩበት። እነታምራት ላይኔ እነ ስዬ አብርሃ በስኳር ሙስና ስም ተከሰው ነበር። ዋና ዋና ሙስና ላይ ሲዋኙበት የነበሩ የሚከሰሱ ስላልነበሩ የልብ ልብ ተሰምቷቸው እስከመጨረሻው በድርጊታቸው ቀጥለውበታል። እነሱ የገኘው መደብ አካል ናቸዋ! ተብሎ ታለፉ። ‹‹ሰማይ አይታረስ ንጉሥ አይከሰስ›› የሚለውን ብሂል በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ንጉሦች ዘመን ተተግብሮ ዓየነው። ለነገሩ የላይኞቹን ቢነካ ኖሮ ፀረ ሙስና ራሱ ውሃ ውስጥ እንደገባ ሳሙና ይሟሟ ነበር።

ሙስና ቃሉ የግዕዝ ነው፤ አማሰነ ሲባል አባከነ አጠፋ ከሚለው ቃል ተመሳሳይ ነው። ሙስና በአማርኛ ጉቦ የሚለው ቃል ነው። ቦጋለ አሰፋ የሕዝባዊ ወያኔ አርነት ትግራይ እና የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ የንግድ ኢምፓየር በሚል ርዕስ በ1996 ዓ.ም ባወጡት መጽሐፍ፤ የሕወሓት 56 ሁለገብ ድርጅቶች በሥሩ ያሉ ንዑስ ድርጅቶች ሳይጨመሩ ከ3ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ነበራቸው።

**ማን እንደዘረፈኝ ... ልቤ እያስተዋለ**

**የለመደው አፌ ... የመንግሥት ያለህ አለ!**

የሚለው ሥነ ቃላዊ ግጥምም ዘራፊዎቹ መንግሥት ነን ባዮቹ እንደነበሩ ያሳየናል።

የቀድሞው ፌዴራል የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ይሠሩ የነበሩ ሠራተኞች በአንድ ወቅት እንደነገሩኝ፤ ለሚሠሩት የስኳር ፕሮጀክት መረጃ የሚሰጥ ቢጢሌ መጽሔት (ቡክሌት) እንዲያዘጋጁ በመመሪያ ትዕዛዝ ይወርድላቸዋል። መጽሔቱን ለመዘጋጀት ተጉ። በዚህ መሐል የተወሰኑ የፋብሪካዎቹ ፕሮጀክት ግንባታዎች በሚካሄድባቸው ቦታዎች አንድ ሁለቱን ለመጎብኘት ጓጉ። ቢጎበኙ ለሥራው እንደሚረዳቸው ለሚመለከታቸው ጠየቁ፤ መጀመሪያ በተሰጣችሁ ትዕዛዝ መሠረት ጽሑፉን ጨርሱና ትሄዳላችሁ ተባሉ። ጽሑፉን እንደጨረሱ ተጨማሪ የመስክ ሥራ ሲጠይቁ የጻፋችሁት በቂ ስለሆነ አያስፈልግም ተባሉና ቢጢሌ መጽሔቱም ታትሞ ተሠራጨ።

መናገር የፈለኩት ስለ መስክ መሄድና መቅረት፣ ስለ መጽሔት መታተምና መሠራጨት አለመሆኑ ይሰመርበት። በአካል የሌሉት መዘዘኞቹ አስር የስኳር ፋብሪካ ግንባታዎች ለሚዲያ ፍጆታ ተብለው ብቻ እንዲዘገቡ ተፈልገው ነው። ቢጢሌ መጽሔቷን ታትማ ወጥታ በወቅቱ ሳነባት የሚያጓጉ ነገሮች ነበሩዋት። ኢትዮጵያ በስኳር ፋብሪካዎቹ ግንባታ ምርታማ ውጤታማ እንደምትሆን ይጠቅሳል። ከንጉሡ ጊዜ ጀምሮ በቡና ላኪነት ትልቁን የውጪ ምንዛሪ የምታገኘው ሀገራችን በስኳር የውጪ ንግድ ገቢ፤ የቡናን ቀዳሚ የውጪ ገቢ ቦታ ትረከባለች የሚል ሀሳብ ነበረው። እነ ኩባን በስኳር ኤክስፖርት ትፎካከራለች ትቀድማች፤ ብዙ ዜጎች የሥራ ዕድል ያገኛሉ፤ ብዙ ከተሞች ይስፋፋሉ ይመሠረታሉ የሚሉ ሕልሞችን (ዕቅዶችን ለማለት ስለ ከበደኝም እንደሆነ እወቁልኝ) ይዛ ነበር። ሕልሞቹ ሕልም ሆነው እልም ብለው ቀሩ። የስኳር ፕሮጀክቶቹ እንደ ስኳር ሟሙ። የወቅቱ ባለሥልጣኖች በስኳር ሙስና ተዘፈቁ። ተደብቆ እየዳኸ የነበረው ሙስና ፤ ቀና ብሎ ከመሄድ አልፎ በአደባባይ መሮጥ ጀመረ።

አሥር ስኳር ፋብሪካዎች ይከፈታሉ ተብሎ፤ ለግንባታዎቹም ከውጪ ገንዘብ በብድር መጣ። በተመረጡት ቦታዎች ገበሬዎች እንዲለቁ፤ እንዲፈናቀሉ ተደረገ፤ ሕዝቡ ቅር እያለው ማለት ነው። የአባ ሳሙኤል ዘዋልድባ ገዳምም ፋብሪካው ከሚመሠረትበት አንዱ ነበር። ገዳሙና መንግሥት መስማማት አልቻሉም። ገዢዎቹ እንገነባለን ሲሉ ከሕዝቡ ጋር ሳይመካከሩ ስለነበር፤ ገንዘቡም ባከኖ ቀረ። ሌሎቹን የሙስና ጉዳዮች ብናነሳ ቦታ አይበቃንም። ሜቴክ ብቻ የዘረፈው ብር በራሱ ምትክ የለሽ ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ሲነገረን የነበረው፤ ባለ ሁለት አኀዝ ዕድገት አስመዘገብን ተብሎ ነበር። የተመዘገበው ዕድገት ግን አልታይ ያለን ጥቁር ሰሌዳ ላይ ተጽፎ ምቀኞች አጥፍተውት ይሆን እንዴ? ብለን ለረጅም ዓመታት ስንጨነቅ ኖረናል።

አንዳንዶች ለሙስና እንደ ኢሕአዴግ ሥርወ መንግሥት ምቹ ዘመን አልነበረም ይላሉ። ከደርግ ዘመን ጋር ሲያነፃፅሩት ማለት ነው። በደርግ ጊዜ የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ የሚል ነገር ነበር። ዓላማው ጉቦን መከላከል ነበር፤ አልፎ አልፎ ጉቦ ነገሮች ቢኖሩም ተስፋፍቶና ተንሠራፍቶ የተገኘው በኢሕአዴግ ዘመን ነው ብለው ይናገራሉ።

ተቋማትን ነፃና ገለልተኛ አድርጎ ከማደራጀት፣ ብቁ አመራሮችንና ባለሙያዎችን ከመመደብ፣ ሕግና ሥርዓት በማስፈን ግልጽነትና ተጠያቂነትን ከማስፈን አኳያ ትልልቅ ሥራዎችን ማቀድ ተገቢ ነው። የዘፈቀደ አመራር ለብልሹ አሠራሮች ምክንያት በመሆኑ በርካታ ችግሮች አጋጥመዋል። ኢትዮጵያ ከማንም ጫና መላቀቅ የምትችለው በሥርዓት ስትመራ ብቻ ነው። በመንግሥት መሥሪያ ቤት ብቻ እየዞሩ ገቢህ ስንት ነው? ምን አለህ? ብቻ ብሎ መዝግቦ ፀረ-ሙስና እየሠራሁ ነው ብሎ ካሰበ ውጤት እንደማይመጣ ያለፈው ልምዳችን ምስክር ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር) ሙስናን አስመልክቶ ሲናገሩ ‹‹ሌብነት ነቀርሳ ነው፣ ሌባ ሰው ምንም ቢሆን ዋጋ የለውም። ለራሱም ለልጆቹም ዋጋ የለውም፣ ልንዋጋውና ልናቆመው ይገባል፤›› ማለታቸው ለማቆም መረባረብ እንዳለብን ማሳያ ነው።

በርግጥ ያለንበት ወቅት ስለሙስናም ስለ ሕልውና የምናስብበት ነው። እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል የሚሉ ቡድኖች እኛ ሀገር ካልመራን ዐሻራ እንነቅላለን፣ አቧራ እናቦናለን፣ እናሸብራለን፣ እንበታትናለን ብለው ተነስተዋል። ለሀገር የማያስቡ የራሳቸውን ጥቅም የሚያሳድዱ መሆናቸውን ማሳያ ይሆናል። በየቦታው ሁከትና እግት እየፈጠሩ ብር እየጠየቁ ነው። እነዚህ ሌቦች ናቸው እንዴ ሀገር የሚመሩት? የተነገደበት ሀገር ወዳዱ የትግራይ ሕዝብንም እያየው ነው። ከድህነት ማጥ እናወጣለን ብለው፤ ልጁን ለጦርነት እየማገዱት አባትና እናትን ኀዘንና ጭንቀት ድህነትና አዘቅት፣ ድርቅ ውስጥ ከተቱት።

ከለውጡ ዓመታት ወዲህ አመርቂ ሥራዎችን ተሠርተዋል። ሙስና ግን እንዳለ ነው። በሙስና ምክንያት ቆሞ የነበረው የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ሥራ እንኳ ተነቃቃ፤ ውጤታማ ሆነ። የግድቡ ወደ ፍፃሜው መድረሱ በራሱ ኩራት ነው። ኤሌክትሪክ በማመንጨት የበለጠ የውጪ ገቢ እየሰበሰብን ነው። ክረምቱን ጠብቆ ሲከናወን የነበረው የአረንጓዴ ዐሻራ ዘመቻ የሃገራችንን ስም በዓለም አቀፍ ደረጃ እያስጠራ ነው። ሌሎች ብዙ አመርቂ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። ሆኖም ከቀበሌ እስከ ላይኛው እርከን ሙስና አሁንም እየተከተለን ነው። እያንዳንዷን ጉዳይ ለማስፈጸመም እጅን ኪስ ውስጥ መክተት ግድ ሆኗል።

ሙሰኞች በዚህ ብቻ አያበቁም። የእነሱ ሆድ እስኪጠረቃ በረባ ባልረባው ሁከትና ብጥብጥ እንዲነሳ በማድረግ በጨለማ ሕዝቡን ሲዘርፉት ይታያሉ። ለውጡን ሊያናውጡ የሚፈልጉ በየቦታው ሁከት ሊፈጥሩ እየተፍጨረጨሩ ነው። ዜጋውና መንግሥት ለሀገር ሕልውና ሲታገል፤ በጎን ተሸሽገው ሙስናቸውን የሚያሳድዱ የውስጥ አርበኞችና ጥቅም አሳዳጆች አሉ። ይህም አጋጣሚው ተጠቅመው ሀገር እየቦረቦሩና እየመዘበሩ ያሉት ሙሰኞች ናቸው።

እነኚህን ከጎናችን ያሉት ሙሰኞችን ከወዲሁ እርምጃ ለመውሰድ ጥረት ማድረግ ይገባል። ተገልጋዩን ከኪሱ እያጎደሉ ራሳቸውን እያደለቡ ነው። እነኚህ ፉኖና ሸኔ ማለት ናቸው። ዜጋው መንግሥትን ላይ ቅሬታ እንዲሰማው የሚታገሉ። በሩቅ ጫካ የሚታገሉትን ብቻ ሳይሆን ከጎናችን ሆነው በሙስና የሚወጉን መውጋት አለብን።

ባለፈው ሐምሌ 5 ቀን 2016 ዓ.ም. የፌዴራል የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ባቀረበው ሪፖርት ሙስናን መከላከል በዓመቱ 2.1 ቢሊዮን ብር፣ እንዲሁም 46.4 ሚሊዮን ካሬ ሜትር የከተማና ገጠር መሬት ከሙስናና ምዝበራ ወንጀል መታደጉን ይፋ አድርጓል። የ175 ሺሕ አመራሮችንና የሥራ ኃላፊዎችን ሀብት ምዝገባ ማከናወኑን ያመለከተው ኮሚሽኑ በግዥ፣ በንብረት ማስወገድ፣ ገቢ አሰባሰብ በመሳሰሉ የመንግሥት ተቋማት የሥራ ክዋኔዎች ሒደት ሊፈጸሙ ይችሉ የነበሩ በርካታ የሙስና ነክ ወንጀሎችን መታደግ ስለመቻሉ ይዘረዝራል። በዚህም ሙስና መከላከል ላይ ጥሩ መሥራቱን ያትታል።

እኛ ግን መች ተነካና ይቀራል ገና እንለዋለን። ከወንጀል መታደጉን እናደንቃለን። ግን ሙስና ኮሚሽን በሙስና የወደቁትን ሰዎች እያነሳ እስከ መቼ ይቀጥላል? በሙስና የወደቁትን አንሱ የሚል መ.ያ.ድ. ያለ ይመስላል። መች ነው የሚከሳቸው? ሕዝብ እየከሰሰ ነው። ስለዚህም ሙሰኞች ፍርድ አደባባይ ቆመው የእጃቸውን እንዲያገኙ ሕዝብ ይፈልጋል።

የወረዳ አመራሮችም መሬት አስተዳደር ወሳኝ ኩነቶች፣ ገቢዎች ቢሮዎችና መብራት ኃይል እየተባለ የሚታመው መብራት ኃይል፣ የኢሚግሬሽን፣ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች በሙስና አንጋፋ መሆኑን ያስመሰከረው ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ ሳይዘነጋ ሚኒስትር መሥሪያ ቤቶች ሌሎችም ተገልጋይ በማጉላላት የሚታሙ ራሳቸውን ሊፈትሹ ይገባል። ገቢዎች ሚኒስቴር ባወጣው መረጃ ባለፉት ወራት ሐሰተኛ ደረሰኝ ብቻ እየሸጡ የሃገር ሀብት ወደ ኪሳቸው ሲያስገቡ የነበሩ 63 ድርጅቶችን አጋልጦ ነበር።

በገቢዎች ሚኒስቴር አዳማ ቅ/ጽ/ቤት 1ነጥብ5 ሚሊዮን ብር ጉቦ ለመቀበል ተስማምተው የቅድሚያ ክፍያ 500 ሺህ ብር ሲቀበል እጅ ከፍንጅ መያዙን ሰምተናል። በተመሳሳይ በሚኒስቴሩ ምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት 5 ሚሊዮን ብር ለመቀበል ተስማምተው የመጀመሪያ ክፍያ 200ሺህ ብር ሲቀበሉ እጅ ከፍንጅ መያዛቸውንም አድምጠናል።

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት 200 ሺህ ብር ሲቀበል እጅ ከፍንጅ መያዙን በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት መረጃው ደርሶናል። እንዲሁም በገቢዎች በሚኒስቴሩ በመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽቤት ሁለት ኦዲተሮች 12 ሚሊዮን ብር ጉቦ ለመቀበል ተስማምተው የመጀመሪያ ክፍያ 100 ሺ. ብር ለመቀበል በሂደት ላይ እያሉ እጅ ከፍንጅ ለመያዝ መቻሉን አድምጠናል።

ከላይ በተወሰዱት እርምጃዎች ያልተማሩ የውስጥና የውጭ ሌቦች ዛሬም በተቀናጀ መንገድ የሀገርና የሕዝብ ሀብት የሆነውን ከፍተኛ የታክስ ገንዘብ ለድርጅቱ እንዲቀር በማድረግ ይህን ለሚሠሩበት ውለታ 3ነጥብ7 ሚሊዮን ብር ወደ ግላቸው ሊያስገቡ ሲሉ በቁጥጥር ስር ውለዋል።

እንዲሁም ሰሞኑን በወጣ ዜና በወላይታ ዞን ዳሞት ወይዴ ወረዳ ከኮንትሮባንድ ነጋዴዎች ጋር በመተባበር ወንጀል ሲፈጽም በመገኘት የተጠረጠረ የወረዳው ፖሊስ አዛዥ በቁጥጥር ስር ሆኖ ምርመራ መቀጠሉን የዞኑ ፖሊስ አዛዥ ም/ኮ/ር ንጋቱ ጌታቸው አስታውቀዋል።

ከመንግሥትና ከሕዝብ የተሰጠውን ኃላፊነት ወደ ጎን በመተው ከሕገ ወጥ ነጋዴዎችና ኮንትሮባንዲስቶች ጋር በመተባበር ከወላይታ ሶዶ እስከ ሞያሌ ድረስ የሌብነት መስመር በመዘርጋት የዞኑንና የወረዳውን ሕጋዊ ነጋዴዎች እንዲዳከሙ ከማድረጉም በላይ መንግሥት የጀመረውን የብልፅግና ጉዞ የሚያደናቅፍ ተግባር መፈጸሙን የወረዳው አጠቃላይ የፖሊስ አመራርና አባላት በተገኙበት በተደረገ የግምገማ መድረክ በመረጋገጡና በሙስናና ብልሹ አሠራር የተዘፈቀ መሆኑ ገልጸዋል።

ከዚሁ ጎን የትራንስፖርቱም ዘርፍ መንቀራፈፍ ይታይ። የተሳፋሪውን ጋጋታ እንደ ሠርግና ምላሽ የሚቆጥሩ አሽከርካሪዎች ከታሪፍ ውጪ በእጥፍ እያስከፈሉ ነው። «መኪና የለም ከፈለክ ተሳፈር፤ ካልፈለክ ሌላው ይሳፈራል» እያሉ ተሳፋሪውን የሚያመናጭቁ በዝተዋል። አዲስ አበባ ያለው የትራንስፖርት ችግር እንዳለ ሆኖ ወደ ተለያዩ ገጠራማ አካባቢዎች መሳፈር የሚፈልጉ በእጥፍ እንዲከፍሉ እንደሚጠየቁ በመናኸሪያዎች የሚታይ ነው። እንዳይጠየቁም 50 ብር የሚያስከፍለውን መንገድ እጥፍ ክፍያ አስከፍለው የ50 ብር ደረሰኝ ይሰጣሉ። ሁነቱ የሙስና ጎዳና ስለሆነ የሚመለከታቸው ይመልከቱት።

ሙስናው በየቦታው የበዛው የሚመለከተው አካል ስለማይመለከተው ይመስለኛል። የፌዴራል ኦዲተር መሥሪያ ቤት በሚያቀርበው ሪፖርት የባከኑ ገንዘቦች ተሰምተዋል። ፀረ ሙስና በዚህ ረገድ ድምፁ ምንም አይሰማም። በየመሥሪያ ቤቱ ገንዘብ አላግባብ ሲወድም የየቢሮው ኦዲተሮችና የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ‹ሠራተኞች› ተጠያቂ መሆንም አለባቸው። ተጠያቂ ካልሆኑና ኃላፊዎች ብቻ ቢያዙ አሠራሩ ‹‹ከመረቁ አውጡልኝ ከሥጋው ያመኛ ነኝ›› እንደሚሉት ብሂል ይሆናል።

በሕግ ብያኔ ሰው በሁለት ይከፈላል፤ የተፈጥሮ ሰውና በሕግ ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ተቋም። ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሕጋዊ ሰውነት አለው። ኮሚሽኑ ካሸለበበት ይንቃ፤ ሳስበው ሙስና በፀረ ሙስና እየሳቀ ይመስለኛል። አንድ ወዳጄ ሙስናን ለምን ቦልድ አደረከው (አደለብከው) ብሎ ጠየቀኝ ያው ሙስና እየደለበ ፀረ ሙስና እየሳሳ ስለሆነ ነው አልኩት። ኮሚሽኑ ከፌዴራልና ከክልል ኦዲተር መሥሪያ ቤቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ያጠናክር። ለተለያዩ ሕዝባዊ አገልግሎቶች ከሕዝብ ገንዘብ ሲሰበሰብ ነበር፤ የሕዝቡን ተሳትፎ የአስፈፃሚዎችን ትጋት ማበረታታት ይገባል። ነገር ግን ገንዘቡ ለሚፈለገው ዓላማ መዋሉን አለመመዝበሩን የሚፈትሹ ደግሞ ይንቁ።

**በአጠቃላይ ጸረ ሙስና ይጧጧፍ!**

## የዘመን ጥበብ

# ቀታሪ ግጥም

**በአንለይ ጥላሁን ምትኩ**

በዚህ ምጥን ሥነ-ጽሑፋዊ ዳሰሳ ጽሑፍ ሁለት ጉምቱ የኪነጥበብ ሰው የሆኑት ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው በ‹‹ውስጠት›› እና አሰፋ ጉያ በ‹‹የከንፈር ወዳጅ›› የግጥም መድብሎቻቸው ያካተቷቸውን ‹‹ሰው እና ሚዛን የለሽ ሚዛን›› ግጥሞችን እንቃኛለን። መቃኛችን ቃል ነው።

ጉድ እኮ ነው!

ከላይ ጎባባውን ሰማይ፣ ከታች ደግሞ ከእግሩ ስር የወደቀችው መሬት ታኮም ሆነ ድሆ የሚኖረው፣ የራሱ ባለፅዳ የሆነውን ሰው ቀጥለው በቀረቡ ሁለት የተለያዩ ግን የሰውን(የግለሰብን) ኃያልነት የሚያሰናኙ ግጥሞች ውስጥ ኃይሉን አጮልቀን እንመለከታለን። ምልከታው ምናባዊ ነው። በዚህም በእኔ እና ከእኔ በቅርብና በሩቅ (ከቦታና ከዘመን አንፃር) ያለ አንባቢ የጋራ የኪነት ቤት የምንሠራበት ነው። ጉዳዩ ቀታሪ ነው። በቀላሉ የሚጨበጥ አይደለም። ምክንያቱ ደግሞ አንድም የቋንቋ፣ ሌላም የሕይወት ልምድ ማነስ ምናባችንን ይቧጥጣል።

ያም ሆኖ ጥረታችን ከንቱ እንዳይቀር ቀታሪ የሚለውን ቃል በማፍታታት እንጀምር።

[ቀታሪ፡- ስሩ ቀተረ ነው። ቀተረ፡- እኩል ለመሆን ተከታተለ፡- ተቀታተረ፡- ተመለካከተ፡- ተወዳደረ፡ -ተተካከለ፡-ተመዛዘነ፡-ተፎካከረ፡-ተፈላለገ (አስ) ከባለ ቀትር አትቀታተር። (ከሣቴ ብርሃን ተሠማ÷የአማርኛ መዝገበ ቃላት÷ገፅ ፫ ፻ ፹ ፬÷2008 ዓ.ም) ግጥም ምንጩ ሕይወት ነውና (ቋንቋው(መንገዱ) አዕምሮን፣ ስሜቱ ልብን እና መልዕክቱ ልቦናን ይቀትራል። ) አዕምሮን፣ ልቦናንና ልብን የቀተረ ከምናብ የሚፈለቀቅ የፅነነ የጥበብ ውጤት ነው። መቀተሩ ከልማድ ጋር የሚደረግ ግብግብ ነው። ፈጠራ ደግሞ ልማድን መሻገር ይጠይቃል። ከልማድ ያልተሻገረ ግጥም ነፃ አያወጣም። አይታኘክም-የተመጠጠ ነውና። ]

...

**ሰው**
**የሴሎች ሴሎች ክምችት**
**የቃላት ርችት፡--**
**ጭንቅላታም፣**
**በባሰ ይባስ ዓይነቱ ነገር ያዢ**
**ፍጥረትን ገዢ**
**ሳያሠልስ**
**እሱው አንጋሽ እሱው ንጉሥ።**

(ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው፣ውስጠት፣1981 ፣ገፅ 78)


በግጥሙ፣ ሰው የነገሮች ቅጥልጥላት ውጤት ነው። ይህም ‹‹የሴሎች ሴሎች ክምችት›› በሚለው አሰነኛኘት ተገልጿል። ‹‹የሴሎች ሴሎች...›› የሚለው አገላለፅ ብዛት ያላቸው ነገሮች የተከማቹበት መሆኑን አመላካች ሲሆን ሰው የብዙ ሰዋዊ ጉዳዮች ውጤት መሆኑን ለማመልከት የገባ ነው። ይህን አጠቃቀም በመደብ ብንወስደው የበርካታ መደቦች ክምችት መሆኑን የሚገልፅ ነው። ሴሎቹ ምንድን ናቸው? ስሜት፣ ድምፅ፣ ቃላት፣ ሃሳብ፣ እሳቦት፣ እሳቤ፣ እውቀት፣ሥርዓት፣ እምነት፣ ባሕል፣ ሃይማኖት፣... ከረቂቅ ወደ ተጨባጭ ወይም ከጥቃቅን ወደ ግዙፍ ነገር እያደገ የሚሄድ ‹‹የሴሎች›› ድምር ውጤት ነው። ግጥሙ ላይ ሂደቱ በየስንኞቹ ተገልጿል። ከጥቃቅን ነገር የጀመረው ማንነት እያደገ ሄዶ የፍጥረት አለቃ እስከመሆን ያድግና አንጋሽና ንጉሥ ማዕረግ ባለቤት ይሆናል።


የግጥሙ አሰነኛኘት ሰው በቋንቋ አማካኝነት የሠራውን ዓለም አጠቃላይ ምስል የሚያሳይ ነው። የመጀመሪያው ስንኝ ስለ ድምፆች ክምችት በየፈርጁ ያለውን የክምችት አቅም ወይም ብቃት ገላጭ ነው። ሁለተኛው ስንኝ ደግሞ የድምፆች ክምችት ውጤት የሆነው ቃል በርችት መልክ በአንደበት ለአደባባይ ሲበቃ ያለውን ሰዋዊ ባሕሪ እና ተግባር የወከለ አሰነኛኘት ነው። በዚህም የሰው ልጅ የልሳን ባለቤት መሆኑን እና በዚህ ብቃቱ የሚከናወነውን ርችታዊ ተግባር (በፍንዳታ የተወከለው አብሳሪ፣ ትርጉም) ያለው መሆኑን ለማመልከት ነው።

ቀጥሎ ደግሞ ‹‹ጭንቅላታም›› በሚል የተገለፀው ሰዋዊ ተግባር አሰላሳይ፣ ንቁ፣ በአዕምሮው የሚመራ መሆኑን ለማመልከት የገባ ነው። ይህም ተግባር በቋንቋ ላይ የተመሠረተ ነው።

‹‹በባሰ ይባስ ዐይነቱ ነገር ያዢ›› ደግሞ ነገር እና ተግባር መራጭ፣ የላቀ(የባሰ) ጉዳይ ባለቤት መሆኑን ወካይ ሆኖ የገባ ነው። በዚህም ‹‹በባሰው ይባስ ባይ›› በመሆኑ ክልከላን የሚጥስ፣ ኃላፊነት ወስዶ ነገሮችን የሚፈፅምና የሚመጣውን መከራ ወይም ኃላፊነት ለመወጣት ወሳኝ ተደርጎ ተገልጿል። እዚህ ላይ ‹‹ነገር ያዢ›› የሚለው ሐረግ ወግ፣ ሕግ አዋቂ የሚል ፍቺ ያለው ሲሆን አንድም የቋንቋን ሥርዓት ሠሪ፣ አንድም ደግሞ የኑሮውን ወግ፣ ባሕል አጥብቆ ያዥ መሆኑን ገላጭ ሆኖ ተሰናኝቷል። ስለሆነም መራጭና የሚስማማውን ነገር የሚተገብር (ያዢ) ነው።

‹‹ፍጥረትን ገዢ›› የሚለው አምስተኛ መስመር ላይ ያለው አሰነኛኘት ደግሞ ሰው በዘረጋው ወግ፣ ሥርዓት ወይም ሕግ አማካኝነት በዙሪያው ያሉ ፍጥረታትን የሚያስተዳድርበት አቅም የተላበሰ መሆኑን ጠቋሚ ነው። በዚህም ሰው በራሱ መፍጨርጨር የኃይል የበላይነቱን የያዘ፣ ገዢ ማንነት ያለው ነው። ይህ ሚናው ደግሞ ‹‹ሳያሠልስ›› የሚተገበር ነው። ይህም ሰውን ከምንም ነገር ተፅዕኖ የሚያላቅቅና ከራሱ ሥርዓት ውጪ ከምንም ነገር ነፃ የሆነ መሆኑን ማሳያ ነው። አሰነኛኘቱ የአረጋጋጭነት ሚና ያለው ነው። በዚህም ምክንያት ‹‹ሳያሰልስ›› የሚገዛ ነው።




በመጨረሻም ሰው ‹‹እሱው አንጋሽ እሱው ንጉሥ›› መሆኑን በመግለፅ ግጥሙ ይቋጫል። በዚህም የሁሉም ሰዋዊ ተግባር ምንጬም አመንጪም እሱ ሆኖ ተበስሯል። ይህም ሰው ከራሱ ውጭ በሆነ ሥርዓትም ሆነ ሕግ የማይመራ፣ ማንነቱም ያልተቀረፀ መሆኑን አረጋጋጭ በሆነ አገላለፅ የተሰናኘ ነው። በዚህም ምክንያት የሰውን ማንነት የሚገልፁ ነገሮች በሙሉ በራሱ በሰው የተሠሩ፣ የተዘረጉ የማንነቱ ድር ናቸው። ስለሆነም በግጥሙ ውስጥ ዙፋኑም ዳኛውም ራሱ ሰው በመሆኑ ሕልውናውን በራሱ ዐሻራ የሚቀርፅ ሆኖ ተስሏል።

በመቀጠል ‹‹ሚዛን የለሽ ሚዛን››ን እንቃኝ፡-

**ሚዛን የለሽ ሚዛን**
**ርዝመትስ በእጥረት ተመተረ**
**ፈሳሽስ በጠጣር ተሰፈረ**
**ውፍረት - በቅጥነት...**
**ክብደትም በቅለት... ተመዘኑ፤**
**ልስላሴ በሻካራ...**
**ሙቀትም በቅዝቃዜ... ተወሰኑ፤**
**መደመር በመቀነስ ተጨመረ**
**ድልም በሽንፈት ተበሠረ፤**
**ሚዛኑስ በምን ሚዛን ተከወነ?**
**ውጤቱስ በማን ተበየነ???**
**መስከረም 1982**

(አሰፋ ጉያ፣ የከንፈር ወዳጅ፣ 1984፣ ገፅ 36)

‹‹ሚዛን የለሽ ሚዛን›› የሕይወት ተቃራኒ መልኮች ያላቸውን እርስ በርስ ግንኙነት እና አንዱ ለሌላው ስፍር ወይም ልክ ማሳያ ሆነው የገቡበት ግጥም ነው። ለአብነትም ድል እና ሽንፈት፣ መደመር እና መቀነስ፣ ውፍረት እና ቅጥነት፣ ክብደት እና ቅለት፣ ልስላሴ እና ሻካራ፣ ሙቀት እና ቅዝቃዜ፣ ፈሳሽ እና ጠጣር እንዲሁም ረጅም እና አጭር በግጥሙ የልክ ማሳያ ተደርገው የቀረቡ ናቸው። ስለሆነም በየራሳቸው የቆሙ ጉዳዮች ቢሆኑም አንዱ ለሌላው ሕልውና እውን መሆን ያለውን አስተዋፅዖ ነጋሪ አሰነኛኘት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የእነዚህን ጥምረት እና እውን መሆን የሚከውነው አካል የተጠየቀበት አሰነኛኘት ነው።

ግጥሙ ስለ ሚዛን ወይም ልኬት የሚያትት ቢሆንም መስፈርቱ እውን እንዲሆን ያደረገውን አካል ማንነት ይጠይቃል። ሚዛኑን ሚዛን ያደረገው ምንድን እንደሆነ ይጠይቃል። የግጥሙ የመጨረሻ አሰነኛኘት በመስፈርት የማይሰፈር ሚዛን መኖሩን ጠቋሚ ነው። ይህም የሰውን ልጅ እምቅ አቅም አመላካች ከመሆኑም ባሻገር ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያፀደቃቸው፣ የፈጠራቸው፣ የሚጠቀምባቸው እራሱ ሰው መሆኑን ገላጭ ነው። ይህም ሰው ጥልቅ እና ነፃ ማንነት ያለው መሆኑን አብሳሪም ነው። የሚራቀቀው፣ የሚመረምረው የራሱን ማንነት ፍለጋ እንደመሆኑ መጠን እይታው በሰፋ ቁጥር መዳረሻውና በዙሪያው ያሉትን ተጨባጭና ረቂቅ ነገሮችን የሚመዝንበት ወይም የሚመለከትበት መንገድም እየተለጠጠ መሄዱን ነጋሪ አሰነኛኘት ነው።

ሰው ተግባር ላይ የተመሠረተ ሕይወት ስለሚመራ እና ድርጊቱ ደግሞ በምርጫ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የሚያስገኘው ውጤት ወደ መርሕ እየተለወጠ ማንነቱን ያፀናል። ይቀርፃል። ሁኔታው በነፃነት ላይ የተመሠረተ ነው። በግጥሙ የመጨረሻ ሁለት ስንኞች ላይ በጥያቄ መልክ የቀረበውም ይኸው ጉዳይ ነው። ‹‹ሚዛኑስ በምን ሚዛን ተከወነ?

**ውጤቱስ በማን ተበየነ???**‹‹

በማለት የሰፈረው የአመፅ ድምፅ ነው። እንቢተኝነቱ ተግባራቱን ከዘረዘረ በኋላ የሚያሽሟጥጥ መሆኑ ላይ ነው። ሽሙጡ አድጎ በንቅት ድምፀት ‹‹ይህን ሁሉ ዝባዝንኬ ሚዛን አድርጎ የወሰነውና ውጤቱን የሚለካው ማን ነው?›› በሚል ይተካል። ይህ የአመፅ ድርጊት ስለሆነ ከማንም ምንም ዓይነት ምላሽ አይጠብቅም። ዓላማውም ጉዳዩ ትኩረት እንዲያገኝ እና ሰው ነፃነቱን አሳልፎ እንዳይሰጥ ለአንክሮ የቀረበ በመሆኑ ነው።

በአጠቃላይ ሁለቱ ግጥሞች በጥቅሉ የሰው ልጅ ወይም እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱ ባለዕዳ መሆኑን አስረግጠው የሚገልፁ ናቸው። ይህም ሰው መሆንን አፅዳቂ አገላለፅ ነው። ኃላፊነቶቹ የመነጩት ከውስጡ ሲሆን ድርጊቱ የሚያስከትለው ውጤት ዞሮ የሚያርፈው ራሱ ሰው ላይ ነው። የሚራቀቀውም ሆነ ሕግ የሚያወጣው በራሱ ላይ ነው። ሁኔታው የሰውን ላብ ወይም የዘመናት ድካም ዋጋ የሚሰጥ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የረድኤት ድርጅቶች አውደ ርዕይ

**አስናቀ ፀጋዬ**

በኢትዮጵያ የሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖችና ባዛሮች በአብዛኛው ሸማቹን ከነጋዴው የሚያገናኙ ናቸው። በባዛርና ኤግዚቢሽን ነጋዴው ያሉትን ምርቶችና አገልግሎቶች ለሸማቾች የማስተዋወቅ እድል ይፈጠርለታል። በተመሳሳይ ሸማቹም በአንድ ቦታ ላይ ተገኝቶ የተለያዩ ምርቶችን ከነጋዴው የመግዛት እድል ይፈጠርለታል።

ከንግድ ውጪ የሆኑና ማህበራዊ ይዘት ያላቸው ባዛሮችና ኤግዚቢሽኖች ሲዘጋጁ ግን እምብዛም አይታይም። የሚዘጋጁትም በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ሆኖም ከተለመደው ባዛርና ኤግዚቢሽን ወጣ ያለና በተለይ በአካል ጉዳተኞችና ሌሎች ድጋፍ በሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማገዝ የሚንቀሳቀሱ የእርዳታ ድርጅቶችና በጎ አድራጎት ማህበራት የሚሳተፉበት አውደ ርዕይ በነሐሴ አጋማሽ ይካሄዳል።

አቶ ናትናኤል ዘርይሁን በታሜሶል ኮሚዩኒኬሽን ‹‹አዲስ ነገር በአዲስ ዓመት›› ኤክስፖ የማርኬቲንግ ዳይሬክተር ሆነው ያገለግላሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፣ በኢትዮጵያ በአብዛኛው የሚካሄዱ ባዛሮችና ኤግዚቢሽኖች ንግድን መሰረት ያደረጉና ሸማቾችን ከአምራቾች የሚያገናኙ ናቸው። ይሁንና የንግድ ባዛርና ኤግዚቢሽኖችን ማህበራዊ ይዘት ካላቸው ጋር ቀይጦ ማካሄድ ይቻላል።

ይህም ህብረተተሰቡ ከንግድ ባለፈ በባዛርና ኤግዚቢሽኖች ከሚቀርቡና በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ከሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ጋር በሁለንተናዊ መልኩ ግንኙነት ለመፍጠር ያስችለዋል። ከዚሁ ጎን ለጎን የእርዳታ ድርጅቶቹና ማህበራቱ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በገንዘብ፣ በእውቀት፣ በጉልበትና በሌሎችም መንገዶች ለመደገፍ አጋጣሚዎች ይፈጠሩለታል።

እንደ ማርኬቲንግ ዳይሬክተሩ ገለፃ ‹‹አዲስ ነገር በአዲስ ዓመት›› ኤክስፖ መካሄድ ከጀመረ ሀያ አመታትን አስቆጥሯል። ይሁንና ዘንድሮ ከነሐሴ 16 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የሚካሄደው ከዚህ በፊት ሲካሄዱ የነበሩ ኤክስፖዎችን በደንብ በማጤን አዲስና ማህበራዊ ይዘት ያላቸው ባዛርና ኤግዚቢሽኖች እንዲካተቱበት ተደርጓል። ሰዎች በቀላሉ የሚፈልጓቸውን ነገሮች ሊያገኙ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ኤክስፖው በመንደር ይከፋፈላል። በነዚህ መንደሮች ውስጥ ማህበራዊ ይዘት ያላቸውና እንደ ጤና፣ ትምህርት፣ እውቀት፣ ልጆች፣ ስፖርት፣ መዝናኛና ሌሎችም እንዲካተቱ ይደረጋል።

ኤክስፖው በመንደር ተከፋፍሎ መካሄዱ ተሳታፊዎች በመደበኛነት ከሚያደርጓቸው የንግድና ባዛር እንቅስቃሴዎች በተጨማሪ ማህበራዊ ይዘት ባላቸው መንደሮች ውስጥ ገብተው የጤና ሁኔታቸውን ለመረዳት፣ ትምህርታዊ መረጃዎችን ለማወቅና የትምህርት ቁሳቁሶችን ለልጆቻቸው ለመግዛት፣ እውቀትን ለማሳደግ የሚረዱ መፃህፍትን ለመሸመትና ከእውቀት ጋር የተያያዙ ውይይቶችንና ክርክሮችን እንዲያደርጉ ብሎም ልጆቻቸውን ለማዝናናት፣ ለማቆየትና ስፖርታዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ለማስቻል እድል የሚሰጥ ነው።

በዚህ አውደ ርዕይ በአካል ጉዳተኞችና ሌሎች ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማገዝ የሚንቀሳቀሱ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የራሳቸውን መንደር በነፃ ወስደው ገቢ እንዲያሰባስቡና ለጎብኚዎች ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ እድል ተመቻችቷል። በዚሁ መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶቹና ማህበራቱ ጥሪ ተደርጎላቸው ምዝገባ እያካሄዱ ይገኛሉ።

ማርኬቲንግ ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፤ በኤክስፖው ‹‹የበጎ ስራ መንደር›› በሚል ስያሜ 50 የሚሆኑ መንደሮች በበጎ አድራጎት ስራ ለተሰማሩ ድርጅቶችና ማህበራት ይዘጋጃሉ። በዚህ መንደር የሚገቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ለአካል ጉዳተኞችና ሌሎች ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ከሚያሰባስቡት ድጋፍ በተጨማሪም በጎፋ ገዜ ወረዳ በመሬት መንሸራተት ምክንያት ቤተሰቦቻቸውን ላጡ የመልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ እንደሚያሰባስቡ ይጠበቃል።

እንዲህ አይነቱ ማህበራዊ ይዘት ያለው ኤክስፖ ደግሞ የራሱ ጠቀሜታ አለው። ከዚህ ውስጥ አንዱ ሰዎች ከተለመደው የንግድ ኤክስፖ ባሻገር በማህበራዊ ህይወት ላይ ያሉ ኤግዚቢሽኖች መልካቸው ምን እንደሆነ እንዲገነዘቡ ያደርጋል። በማህራዊ ህይወት ላይ አተኩረው ከሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ጋርም እጅና ጓንት ሆነው እንዲሰሩ እድል ይፈጥራል። ይህም አካል ጉዳተኞችና ሌሎች



**አቶ ናትናኤል ዘርይሁን፤**

ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላል።

በሌላ በኩል ኤክስፖው ማህበረሰቡ የሚፈልገውን ማህበራዊ እንቅስቃሴ በአንድ በተወሰነ መንደር ውስጥ እንዲያገኝ ያስችለዋል። ማህበራዊ ህይወትንም ያንፀባርቃል። መንደር የሚለው ፅነሰ ሃሳብ በራሱ ኢትዮጵያ ከመንደር ጀምራ ሀገር ሆና እንደተሰራች ያመላክታል። በዚህ ኤክስፖም ይህንኑ ማህበራዊ ህይወት ለማንፀባረቅ ነው የታቀደው። በቀጣይ ደግሞ ትንሷ ፈረንሳይ፣ ትንሷ መርካቶ በማለት የዛ አካባቢ ተወላጆች በጋራ ወደ ንግዱ አለም ገብተው እንዲሳተፉ ጥሪዎች ተላልፈዋል።

በኤክስፖው የሚዘጋጀው መንደር ውስጥ አንድ ሰው ለአዲስ አመት ምን ይፈልጋል የሚለው መነሻ ከግምት ውስጥ ገብቶ ነው ጤና፣ ትምህርት፣ ልጆች፣ ስፖርት፣ መዝናኛና ሌሎች ልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች እንዲካተቱ የሚደረገው። ስለዚህ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትም በኤክስፖው መንደር ውስጥ ገብተው ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ፋይዳ ያስተዋውቃሉ። ከማህረሰቡ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያጠናክራሉ። ለሚደግፏቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ገቢ ለማሰባሰብም እድል ይፈጠርላቸዋል።

በተጨማሪም ወጣቶች ተደራጅተው ስፈራቸውን ማስጠራት የሚችሉበትን፣ ስራ የሚሰሩበትን ሁኔታ ለመፍጠርና ለወጣቱ የተሻለ እድል ለመስጠት ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ትላልቅ ሃሳብ ይዘው የመጡ ነገር ግን በአቅም ምክንያት ምርትና አገልግሎታቸውን ለማህበረሰቡ ማድረስ ላልቻሉ ወጣቶች በኤክስፖው ቦታዎች በነፃ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። ይህንንም እድል ብዙዎች እንደሚጠቀሙበት ይጠበቃል።

# ዓለም አቀፍ

## ከምድር በታች ያለው ግዙፉ የእስራኤል ሆስፒታል ለጦርነት ጊዜ ራሱን ማዘጋጀት ጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በሰሜናዊ እስራኤል በምትገኘው ሃይፋ ከተማ ከምድር በታች የሚገኘው ግዙፉ ሆስፒታል ለጦርነት ጊዜ ራሱን ማዘጋጀት ጀመረ።

ሆስፒታሉ በኮንክሪት ግንቡ ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ አልጋዎችን የመያዝ አቅም አለው። ቀዶ ሕክምና ክፍሎች፣ የእናቶች ማዋለጃ ክፍል እና የመድኃኒት ማከማቻ መጋዘኖች አሉት።

ለጊዜውም ቢሆን ግን ታካሚዎች የሉትም።

ራምባም ሜዲካል ማዕከል ይህን ያስገነባው እአአ ከ2006ቱ የእስራኤል-ሄዝቦላ ጦርነት በኋላ ነበር።

ይህ ከምድር በታች በርካታ ወለሎች ያሉት ግንባታ በሰላማዊ ጊዜ ለመኪና ማቆሚያነት የሚያገለግል ሲሆን፤ ግንባታው የተከናወነው አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በሦስት ቀናት ውስጥ ወደ ሆስፒታል እንዲቀየር ተደርጎ ነው።

መስከረም 26/2016 ዓ.ም. ሐማስ እስራኤል ላይ ድንገተኛ ጥቃት መፈጸሙን ተከትሎ ከምድር በታች ያለው ወለል ወደ ሆስፒታልነት ለመቀየር በተጠንቀቅ ላይ ሆኖ ቆይቷል።

አሁን ላይ በመካከለኛው ምሥራቅ ያለው ውጥረት ማየሉን ተከትሎ መኪና ማቆሚያ ወደ ሆስፒታልነት እየተቀየረ ነው። ሆስፒታሉ ከሁለት ሺህ በላይ አልጋዎች አሉት።

እስራኤል መጠነ ሰፊ የሆነ ጥቃት ቢከፈትባት በሰሜናዊ የሀገሪቱ ክፍል ከሚገኙ ሆስፒታሎች ታካሚዎችን ከምድር በታች ወስዶ ማከም ከመቻሉ በተጨማሪ፤ በጦርነት የሚቆስሉ ተጎጂዎችን የመርዳታ አቅም አለው።

Okokok

የሐማሱ መሪ እስማኤል ሃኒያ እና የሄዝቦላ ከፍተኛ አዛዥ ፉአድ ሹክሪ ባለፈው ሳምንት መገደላቸውን ተከትሎ ኢራን እና ሄዝቦላ እስራኤል ላይ የበቀል እርምጃ እንደሚወስዱ አስታውቀዋል።

ይህን ተከትሎ በሃይፋ የሚገኙ ሐኪሞች ከሌባኖስ ድንበር በቅርብ ርቀት የምትገኘው ከተማቸው ጥቃት ሊፈጸምባት እንደሚችል ግምት አላቸው።

“መቼ ነው የሚፈጸመው (ጥቃቱ)? ማንም አያውቅም” የሚሉት የራምባም ሜዲካል ማዕከል ዳይሬክተር የሆኑት ዶ/ር አቪ ዌይስማን ናቸው።

ሃይፋ ከሌባኖስ ድንበር ያላት ቅርበት ለሄዝቦላ ሮኬት ተጋላጭ ያደርጋታል። ለዚህም ይመስላል የከተማዋ ነዋሪዎች በጭንቀት ውስጥ እንደሚገኙ ዶ/ር አቪ የሚናገሩት።

ተማሪዎች ሳይቀሩ የከማዋ ነዋሪዎች ሊያጋጥም በሚችል የድንገተኛ ጥቃት ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ተደጋጋሚ



ልምምዶችን ያደርጋሉ።

የከተማዋ ነዋሪ የሆኑ ጥንዶች በዚህ መሰል ሰቆቃ ውስጥ መኖር ምን እንደሚመስል ስሜታቸውን ለቢቢሲ አጋርተዋል።

“የሆነ ሰዓት ላይ እንደሚፈነዳ ቦምብ ነው። በየትኛውም ሰዓት ልሞት እችላለሁ? ጥቃት ሲፈጸም ቤተሰቦቼ ጋር መድረስ እችላለሁ? እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ” ስትል ሴቷ ትናገራለች።

ወንዱ ደግሞ “ሰዎች ይፈራሉ፤ እኔ ግን መፍራት አቁሜያለሁ” ይላል።

ግለሰቡ በከተማዋ በሚገኘው ቡና መሸጫ ሱቁ ቡና እያፈላ በአካባቢው ያለውን ውጥረት በመላመዱ ፍርሃቱ መጥፋቱን ይናገራል።

የከተማዋ ከንቲባ ዮኖ ያሃቭ ግን በስጋት እንቅልፍ አጥተው እንደሚያድሩ ይናገራሉ።

እአአ 2006 በነበረው ጦርነት ከተማዋን ይመሩት የነበሩት የሃይፋ ከተማ ከንቲባ፤ ያለባቸው ኃላፊነት እረፍት እንደሚነሳቸው ይናገራሉ።

“በመካከለኛው ምሥራቅ ሰዎችን በመግደል እና በውድመት ላይ ብቻ የተጠመዱ መሪዎች አሉ” ሲሉ ከንቲባው ይናገራሉ።

ምንም እንኳ የሃይፋ ዶክተሮች ለጦርነት ጊዜ ሆስፒታላቸውን ዝግጁ በማድረግ ቢጠመዱም በመካከለኛው ምስራቅ ውጥረት ለመቀነስ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች እንደቀጠሉ ናቸው።

## የዴሞክራቷ እጩ ካማላ ሃሪስ አጣማሪ አድርገው የመረጧቸው ቲም ዋልዝ ማን ናቸው?

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዴሞክራቷ እጩ ካማላ ሃሪስ በ2024 ምርጫ በምክትል ፕሬዝዳንትነት የሚያጣምሯቸውን የሜኔሶታ አስተዳዳሪ ቲም ዋልዝን መርጠዋል፡፡

ሁለቱ ተወዳዳሪዎች የህዳሩን ምርጫ አሸናፊ ይወስናሉ ከሚባሉ የፍልሚያ ግዛቶች አንዱ በሆነው የፊላዴልፊያ ግዛት ለመጀመሪያ ጊዜ በጋራ የምርጫ ቅስቀሳ አድርገዋል፡፡

በነብራስካ የተወለዱት የ60 ዓመቱ ቲም ዋልዝ ቀደም ሲል በመምህርነት እና በወታደርነት ሀገራቸውን አገልግለዋል፡፡

ወደ ፖለቲካው ከገቡ በኋላ ከ2007 እስከ 2019 በኮንግረሱ በተለያዩ የሥራ ኃላፊነት ሰርተዋል። በ2019 እና በ2022 የሚኒሶታ አስተዳዳሪ ሆነው ለሁለት ጊዜ መመረጥ ችለዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜም የዴሞክራት አስተዳዳሪዎች ህብረት ሊቀመንበር ናቸው፡፡



በ17 ዓመታቸው በሀገሪቱ መከላከያ ናሽናል ጋርድ ውስጥ የተቀላቀሉት ቲም በጦሩ ውስጥ ለ24 ዓመታት አገልግለዋል። ከሚሊታሪ ህይወት ራሳቸውን ካገለሉ በኋላ በአሜሪካ ደቡብ ዳኮታ እና ሚኒሶታ እንዲሁም በቻይና በሚገኙ ትምህርት ቤቶች አስተምረዋል፡፡

ወደ ፖለቲካው ዓለም መሳብ የጀመሩት ማሳቹስቴት ግዛት ሴናተር ጆን ኬሪ በ2004 የፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ቅስቀሳ ቡድን ውስጥ በበጎ ፈቃደኝነት ከተቀላቀሉ በኋላ ነበር፡፡

በግዛት አስተዳዳሪነት ዘመናቸው የኮሌጅ የትምህርት ወጪን መሸፈን ለማይችሉ ተማሪዎች ድጋፍ እንዲደረግ እንዲሁም በሚኒሶታ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የቁርስ እና የምሳ ምገባ በነጻ እንዲጀመር ያስቻሉ ናቸው፡፡

በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አቋማቸው የኢራቅ እና አፍጋኒስታን ጦርነት ላይ የፈንድ ድጋፍ እንዲደረግ በኮንግረሱ እና በሌሎች ማዕቀፎች ቅስቀሳ በማድረግ ይታወቃሉ፡፡

በተጨማሪም በአሁናዊው የሩስያ ዩክሬን ጦርነት ለዩክሬን ድጋፍ ማድረግ የሩሲያን ተጽእኖ ለመግታት ወሳኝ ነው ብለው የሚያምኑ ሰው ናቸው።


ሃሪስ በአጣማሪነት ሊመርጧቸው እንደሚችሉ ከተዘረዘሩ ከሰባት በላይ እጩዎች ቲምን ለምን እንደመረጧቸው ተንታኞች ሲናገሩ፤ ሰውየው በመከላከያው እና በሲቪል አገልግሎት በነበራቸው አበርክቶ በዜጎች ዘንድ ተወዳጅ በመሆናቸው ምክንያት እንደሆነ ይጠቅሳሉ፡፡

ከዚህ ባለፈም ወግ አጥባቂ ከሚባሉ ፖለቲከኞች እና መራጮች ጋር ቲም ያላቸው ወዳጅነት ዴሞክራቶችን በምርጫው ሊያግዝ የሚችል ነው፡፡

ከዚህ ባለፈም የዴሞክራት እና ሪፐብሊካኖች በእኩል ቁጥር በሚገኙባት ሜኔሶታ ያለቅሬታ ማስተዳደር መቻላቸው ጥሩ የፖለቲካ ልምድ እንዲያካብቱ እንዳገዛቸውም ይነገራል፡፡

በተጨማሪም ቲም ከሰዎች ጋር ያላቸው መልካም ግንኙነት እና በንግግር የማሳመን ተጽእኗቸው በምርጫው ወሳኝ እጩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው ተብሏል ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው፡፡

# ስፖርት



# የብሔራዊ ስታዲየም ምዕራፍ ሁለት ግንባታ በቅርቡ ይጀመራል

**ብርሃን ፈይሳ**

የብሄራዊ ስታዲየም ምዕራፍ ሁለት ሎት አንድ የግንባታ ስምምነት በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እና በቻይና ኮንስትራክሽን ኮሚዩኒኬሽን ካምፓኒ (CCCC) መካከል ከትናንት በስቲያ ተደርጓል፡፡ ይህ የግንባታ ምዕራፍ በአንድ ዓመት ውስጥ የሚጠናቀቅ መሆኑም ታውቋል፡፡

ግንባታው በ2008ዓ.ም የተጀመረው ብሄራዊ ስታዲየም የመጀመሪያ ምዕራፍ ግንባታው የተጠናቀቀ ቢሆንም፤ ስራውን ለማስቀጠል ከተቋራጩ ጋር በተፈጠረ ልዩነት ምክንያት ተቋርጦ መቆየቱ ይታወሳል፡፡ ከሰሞኑም የምዕራፍ ሁለት ግንባታውን ለመቀጠል የሚያስችል ስምምነት በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እና በቻይና ኮሚዩኒኬሽን ኮንስትራክሽን ካምፓኒ (CCCC) መካከል ተደርጓል፡፡ የባህልና ስፖርት ሚኒስትሯ ሸዊት ሻንካ እና የተቋራጩ ማናጀር ሚስተር ታኡ ፊርማም ስምምነቱ ተፈጽሟል፡፡ ይህ የግንባታ ምዕራፍ የሚካሄደው በሁለት ተከፍሎ ሲሆን፤ ስምምነቱም የመጀመሪያውን ሎት ለማከናወን የሚያስችል መሆኑ በፊርማ ሥነሥርዓቱ ላይ ተጠቁሟል፡፡

ምዕራፍ አንድ ስራው ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቀው የግንባታው ቀሪዎቹን ስራዎች በዚህ አንድ ዓመት ውስጥ በማጠናቀቅ ወደ ሎት ሁለት የሚሸጋገርም ይሆናል፡፡ በስምምነቱ መሰረትም በስታዲየሙ ውስጥ እንዲሁም ውጪ የሚቀሩ ግንባታዎች ይከናወናሉ፡፡ ይኸውም ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የእግር ኳስ ሜዳ፣ ማሟሟቂያ፣ የመሮጫ መም፣ የ60ሺ ወንበር ገጠማና ሌሎችንም የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡ የቴክኖሎጂ ስራዎች እንዲሁም በስታዲየሙ ውስጥ ያሉ ዘርፈ-ብዙ ክፍሎች የማጠቃለያ፣ የኤሌክትሪክና ፍሳሽ ማስተላለፊያ መስመሮች ዝርጋታ



የግንባታ ስምምነቱ በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲሁም በቻይና ኮንስትራክሽን ኮሚዩኒኬሽን ካምፓኒ (CCCC) መካከል ተፈጽሟል፤

እንዲሁም ከስታዲየሙ ውጪ 3ሺ500 ሰዎችን የመያዝ አቅም ያለው ሜዳ፣ ቅጥር ግቢ ማስዋብ፣ የመኪና ማቆሚያ፣ የእግረኛ መንገዶችና ሌሎች ግንባታዎችም ይከናወናሉ፡፡

ስራው በውጪ ምንዛሬ የሚከናወን ሲሆን፤ የሁለተኛ ምዕራፍ ሎት አንድ ስራዎችን ለማጠናቀቅ የሚያስችለው 50 ሚሊዮን ዶላርም ከዩናይትድ አረብ ኤሜሬትስ መንግሥት ተገኝቷል፡፡ ይህም ገንዘብ በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ጥረት የተገኘ መሆኑም ነው በስምምነት ሥነሥርዓቱ ላይ የተጠቀሰው። የጣሪያ፣ ለንግድ ሥራ የሚውሉ ክፍሎች እና የሌሎች ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታን የሚመለከተው ሥራ ደግሞ በሎት ሁለት የሚቀጥል ሲሆን፤ ይኸውም በኢትዮጵያ ገንዘብ የሚከናወን ይሆናል፡፡

የብሄራዊ ስታዲየም ስትራክቸራል ዲዛይን አዘጋጅና አማካሪ ድርጅት የሆነው ኤችኤም ኢንጂነሪንግ ማኔጂንግ ዳይሬክተር መሰለ ኃይሌ፤ ከዚህ ቀደም የምዕራፍ ሁለት ግንባታ ጨረታ ቢወጣም በውጪ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት መቋረጡን ያስታውሳሉ፡፡ ችግሩን ለመቅረፍም ሁለተኛውን የግንባታ ምዕራፍ ለሁለት በመክፈል በውጪ ምንዛሬ እና በሀገር ውስጥ ገንዘብ የሚካሄድ ይሆናል። የሎት አንድ ግንባታ ውስጥ የተካተቱ ስራዎች ዓለም አቀፍ የስፖርት ተቋማትን መስፈርት አሟልቶ የሚካሄድ ሲሆን፤ የአንድ ዓመት የጊዜ ገደብም ተቀምጦለታል፡፡ የሎት ሁለት ስራዎችን ጨምሮ በአጠቃላይ የስታዲየሙ ግንባታ ተጠናቆም እአአ በ2029 የአፍሪካ ዋንጫን ለማስተናገድ ያስችላል በሚልም ይጠበቃል፡፡

በርካታ ግንባታዎች በሚከናወኑባት ኢትዮጵያ ሜዳዎቿ ከደረጃ በታች በሚል ዓለም አቀፍ ውድድሮችን እንዳያካሂዱ መታገዳቸው ይታወቃል፡፡ ይህንን ተከትሎም የብሄራዊ ስታዲየም ግንባታ ይኸው እጣ ፋንታ እንዳደርሰው ያሰጋል፡፡ በኢትዮጵያ 13 ስታዲየሞች (ብሄራዊ ስታዲየምን ጨምሮ፣ ባህርዳር፣ ሃዋሳ፣ አሶሳ፣ ሰመራ፣ አምቦ፣ ነቀምት፣...) ግንባታ ውስጥ የተሳተፈው የኤችኤም ኢንጂነሪንግ አማካሪ ድርጅት በበኩሉ ሁሉም ደረጃቸውን ጠብቀው መካሄዳቸውን ያረጋግጣል። በዓለም አቀፎቹ ተቋማት በልኬት የሚቀመጡትን እያንዳንዱን መስፈርት በመጠበቅ ግንባታዎች ስለሚከናወኑ በዚህ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች የሉም። ነገር ግን በበጀት እጥረት ምክንያት አንዳንድ ስራዎች የሚከናወኑት በግማሽ ነው፤ ይህም ማለት አህጉር እና ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ለማከናወን የሚያስችሉ እንዳልሆነም ዳይሬክተሩ ይጠቁማሉ፡፡

በተጨማሪም እንደ አፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ያሉ ተቋማት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የተቀመጠ መስፈርት ሳይኖራቸው ነበር ‹‹ያሟላል፣ አያሟላም›› የሚሉት፡፡ ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ መስፈርት አያሟሉም ከተባሉት ስታዲየሞች ባነሱ ሜዳዎች ውድድር መደረጉም ለዚህ ማሳያ ይሆናል፡፡ በየጊዜው የሚጨመሩ ማሻሻያዎችም ከዚህ ይካተታል፡፡ ነገር ግን ካፍ እአአ ከ2023 አንስቶ የራሱን መስፈርት በማዘጋጀቱ የብሄራዊ ስታዲየም ግንባታም ይህንኑ ያማከለና አዳዲስ ማሻሻዎችን ጭምር ያካተተ እንደሚሆንም ዳይሬክተሩ አረጋግጠዋል፡፡